# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 82ኛ ዓመት ቁጥር 051 ጥቅምት 21 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



# «የተሻለች አገር ለመገንባት መሠረቱ ላይ ትኩረት አድርገን መሥራታችንን እንቀጥላለን»

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር)

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- የነገዋ ኢትዮጵያ በሁለንተናዊ መልኩ የተሻለች እንድትሆን መሠረቱ በሆኑት ሕፃናት ላይ ትኩረት አድርገን መሥራታችንን እንቀጥላለን ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ተናገሩ። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የወዳጅነት ፓርክ ምዕራፍ ሁለት የሕፃናትና ወጣቶች መዝናኛ ፓርክ ጅማሮን ጎብኝተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በዚሁ ጊዜ እንደተናገሩት፤ ለቀጣዩ የአገራችን ዕድገት መሠረት ለመጣል ልጆች ላይ ትኩረት አድርገን ካሁኑ መሥራት ይኖብናል ብለዋል።

በተለያዩ ቦታዎች ላይ አሁን የምናየው ችግር ልጆች ላይ ካለመሥራት የመጣ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በቀጣይ አገራዊ ግንባታ በአዕምሮና በሥነልቦና የዳበረ ትውልድ ለመገንባት ጥረታችንን እንቀጥላለን ብለዋል።

ልጆች አገራቸውን እያደነቁና እየወደዱ ጊዜያቸውን ማሳለፍ ከቻሉ በቀጣይ ለአገር ግንባታ ያላቸው ጠቀሜታ ከፍተኛ ይሆናል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ አገር የሚመሠረተው በጠንካራ ትውልድ ነው፤ ጠንካራ

«የተሻለች አገር... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## አፍሪካውያን ከአንዳንድ ምዕራባውያን አገራት ጫና ስመላቀቅ ከምንጊዜውም በላይ በትብብር ሊሠሩ ይገባል

**አብዱረዛቅ መሐመድ**

አዲስ አበባ፡- አፍሪካውያን አገራት ራሳቸውን ከአንዳንድ ምዕራባውያን አገራት የእርዳታና ያልተገባ ጫና ነፃ ለማውጣት ከምንጊዜውም በላይ በትብብር የሚሠሩበት ጊዜ አሁን ነው ሲሉ አፍሪካውያን ወጣቶች ተናገሩ።

ኢትዮጵያ ባዘጋጀችው የመጀመሪያው የአፍሪካ ወጣት መሪዎች ጉባዔ ለመታደም ወደ አዲስ አበባ የመጡና የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ያነጋገራቸው ወጣቶች፣ አፍሪካውያን አገራት ራሳቸውን ከምዕራባውያን እርዳታ የሚያላቅቁበትና በተለያዩ ጊዜያት መልኩን እየቀያየረ የሚደርስባቸውን የውጭ ጫና ለመቋቋም በቅንጅት የሚሠሩበት ጊዜ አሁን ነው ብለዋል።

አፍሪካውያን ወጣቶች ተቀራርበው በጋራ ጉዳዮቻቸው ዙሪያ ሊነጋገሩና ያለምንም የውጭ እርዳታ አህጉሪቷን ወደፊት ሊያራምዱ ይገባል ያለው ታንዛኒያዊው ጃክሰን አኪም ፔምባ ሲሆን፤ ከዚህ አንጻር ኢትዮጵያ ያዘጋጀችው «የአፍሪካ ወጣቶች ጉባዔ» አፍሪካውያን በችግሮቻቸው ዙሪያ እንዲነጋገሩና ልምድና ተሞክሯቸውን እንዲለዋወጡና በራሳቸው አቅም ወደፊት እንዲራመዱ ምቹ ሁኔታዎችን የሚፈጥር ትልቅ መድረክ

አፍሪካውያን ከአንዳንድ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - በሃይሉ አብርሃ

## በአዲሱ ምዕራፍ ሁለት የወዳጅነት ፓርክ ጥንዶች በአንድ ላይ ተሞሽረዋል

**ጌትነት ምህረቴ**

አዲስ አበባ፡- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና ቀዳማዊት እመቤት ዝናሽ ታያቸው ትናንት በተመረቀው ሁለተኛው ምዕራፍ የወዳጅነት ፓርክ ከተሞሸሩ ጥንዶች ጋር ቆይታ አድርገዋል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድም ለሙሽሮቹ መልካም ጋብቻ እንዲሆንላቸው ተመኝተዋል።

ሙሽሮቹም በሚያምረው መናፈሻ በመሞሸራቸው የተሰማቸውን ደስታ የገለጹ ሲሆን፣ ሠርጋቸውን ልዩ እንዳደረገውም ተናግረዋል።

ሙሽሮቹ በአሸበረቀውና በተዋበው ፓርክ ሠርጋቸውን ማካሄዳቸው ወደር የሌለው ደስታ እንዳጎናጸፋቸው በመግለጽ፤ ይህን ታሪካዊ ሠርግ ላዘጋጀው አካል ምስጋና አቅርበዋል፡፡

ፓርኩ ለአንድ ሣምንት ለጎብኚዎች ክፍት ሆኖ እንደሚቆይ ተገልጿል፡፡







## ኢትዮጵያዊነትን ስማጽናት እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ እንደመከላከያ መሆን አለበት

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያዊነታችንን ለማጽናት እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ልክ እንደመከላከያ ለአገሩ ዘብ የሚቆምና የሚቆረቆር መሆን እንዳለበት ተገለጸ፡፡

በኮር ዳዊት ጌታሁን አነሳሽነት ኢትዮጵያዊነት ይቀጥላል የበጐ ፈቃደኞች ስብስብ «ኢትዮጵያዊነታችንን እንዴት እናጽና?» በሚል መሪ ሀሳብ ትናንት

ኢትዮጵያዊነትን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## የመከላከያ ሠራዊት የትግራይን ሕዝብ ከአሸባሪው ሕወሓት ጫና ስማላቀቅ መሥዋዕትነት እየከፈለ መሆኑን የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አስታወቀ

በኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት
FDRE Government Communication Service

**- ሕዝቡ ከመንግሥት ጎን በመሆን እያደረገ ላለው አስተዋጽኦም ምስጋና አቅርቧል**

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የትግራይ ሕዝብ አሸባሪው ሕወሓት ከጫነበት ቀንበር ነፃ እንዲሆን የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት መሥዋዕትነት እየከፈለ ነው ሲል የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አስታወቀ፡፡ የትግራይ ሕዝብ

የመከላከያ ሠራዊት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








አቶ ሙህዲን ናስር

# ወጣቶች በአገራዊ ምክክሩ በንቃት እንዲሳተፉ ጥሪ ቀረበ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ወጣቶች ፌዴሬሽን ወጣቶች እንደ አገር በሚካሄደው አገራዊ ምክክር ላይ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የሚያግዙ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን እያከናወነ መሆኑን አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ ወጣቶች ፌዴሬሽን ቢሮ ኃላፊ አቶ ሙህዲን ናስር በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በአገራዊ ምክክር መድረኩ በጉልህ እንዲሳተፉ ከተቀመጡት አካላት መካከል ወጣቶች ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛሉ፡፡ በመሆኑም ወጣቱ በሂደቱ ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆንና የሚጠበቅበትን አገራዊ አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ፌዴሬሽኑ ከብሔራዊ ምክክር ኮሚሽንና ከሌሎችም ባለድርሻ አካላት ጋር በቅርበት እየሠራ ነው ብለዋል፡፡

አገራዊ ምክክሩ ለወጣቶች የሚኖረው ፋይዳ ምንድነው የሚለውን ለማስገንዘብ የምምክር መድረኮችን በማዘጋጀት የግንዛቤ ፈጠራ ሥራ መከናወኑን ያስታወሱት አቶ ሙህዲን፤ በቀጣይ በሚካሄደው አገራዊ ምክክር ላይ ወጣቶች የሚኖራቸው ሚና ምን መምሰል አለበት በሚለው ላይ በመወያየት መሠረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ መግባባት ላይ መደረሱንም ጠቁመዋል፡፡

በተጨማሪም በአገራዊ ምክክሩ ምንድነው የሚሠራው፣ ለወጣቶች ብሎም ለአገር የሚኖረው ጥቅም ምንድነው በሚለው ላይ በመነጋገር የአጭርና የረጅም ጊዜ እቅዶችን አውጥተው በንቃት ለመሳተፍ አስፈላጊውን የቅድመ ዝግጅት ሥራ ማከናወናቸውንም ጨምረው ገልጸዋል፡፡

በምክክሩ ላይ በከተማ ብቻ ሳይሆን ገጠር ድረስ ያሉ ወጣቶች እንዲሳተፉ ለማድረግ አስፈላጊውን የሥልጠናና ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ እየሠሩ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ በቀጣይነትም ኮሚሽኑ በሚያስቀምጠው አቅጣጫ መሠረት ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ እንደሚገባም አቶ ሙህዲን ተናግረዋል፡፡

አገራዊ ምክክሩ አሁን ካለንበት ሰላም ማጣት ለመውጣትና ውስጣዊ ተግባቦቶቻችንን በመጨመር በቀጣይነትም አገራዊ መግባባትና መተማመን በዘላቂነት እንዲሰፍን ትልቅ ሚና እንደሚኖረው ጠቁመው፤ እንደአገር ሰላም ሲሰፍን የመጀመሪያው ተጠቃሚ ወጣቶች መሆናቸውን ያህል ሰላም ሲታጣም ግንባር ቀደም ተጎጂ የሚሆነው ወጣቱ ነው፡፡

በመሆኑም ከፍረጃ ነፃ ሆኖ እንደ አገር ተነጋግሮ መግባባት ላይ መድረስ የሚቻልበት ዕድል እንዲፈጠር ወጣቶች በአገራዊ ምክክሩ ላይ ንቁ ተሳታፊ በመሆን የሚረከቧትን አገር ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን የበኩላቸውን ታሪካዊ ኃላፊነት መወጣት እንዳለባቸው ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# በጦርነቱ ምክንያት የተዛቡ ሴክተሮችን በማስተካከል አገራዊ ኢኮኖሚው እንዳይጎዳ መሥራት ይገባል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- አገራዊ ኢኮኖሚው እንዳይጎዳ በጦርነቱ ምክንያት የተዛቡ የኢኮኖሚ ሴክተሮችን ማስተካከል የመንግሥት የትኩረት አቅጣጫ መሆን እንዳለበት ተጠቆመ፡፡

በፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት የምጣኔ ሀብት ተመራማሪ ዶክተር ጀማል መሐመድ የሰሜኑ ጦርነት ውጤት በኢኮኖሚው ላይ ከፍተኛ ጉዳት ማድረሱን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ገልጸዋል፡፡ የተዛቡ የኢኮኖሚ ሲስተሞችንና ሴክተሮችን ማስተካከል ዋና የመንግሥት ትኩረት መሆን አለበት ሲሉም መክረዋል፡፡

ዶክተር ጀማል እንዳሉት፤ 2014 ዓ.ም በጦርነቱ ምክንያት የኢኮኖሚው ተጽእኖ ምን ያህል ከባድ ዓመት ሊሆን እንደሚችል ትንበያ ተሰጥቶ ነበር፡፡ ዓመቱ ለኢትዮጵያውያን ከባድ ዓመት ነበር፡፡ የጦርነቱ ውጤትም የዋጋ ግሽበት፣ የምርት እጥረትና የሥራ አጥ ቁጥር መብዛትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

በየቦታው ያሉ የግጭት ሁኔታዎች በኢኮኖሚው አገሪቷን ችግር ውስጥ ከተዋል ያሉት ዶክተር ጀማል፤ ችግሩ የጦርነት ቀጣና ውስጥ ባለው ሕዝብ ላይ ብቻ ሳይሆን የሁሉንም ኢትዮጵያዊ ቤት ያንኳኳ እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ በተለይ ሥራ አጥነት፣ የዋጋ ንረትና የምርት እጥረት በሰፊው ሊከሰት ይችላል ያሉት ዶክተር ጀማል፤ ይህ የሆነውም እዚያ ያለውን ከፍተኛ የሰው ኃይል ለማንቀሳቀስ ከተለያዩ የኢኮኖሚ ሴክተሮች ሀብት ተቀንሶ ወደ ጦርነት ስለሚወሰድ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

ጦርነቱ ባለባቸው አካባቢዎች ወጣቶች ጦርነት ውስጥ መግባታቸውን፤ ብዙ የኢኮኖሚ ዕድሎችና መሠረተ ልማት ላይ ሊውሉ የሚችሉ ከፍተኛ የሆነ የመንግሥት ሀብት ለጦርነቱ መዋሉን፤ ይህም ምጣኔ ሀብቱን እንደሚፈትነው ተናግረዋል፡፡

የምርት እጥረት ሲከሰት ከፍተኛ የዋጋ ንረት ይከሰታል ያሉት ዶክተር ጀማል ይህ አሁን ባለው የኢትዮጵያ ሁኔታ ተጨባጭ ማሳያ እንደሆነ አስታውቀዋል፡፡ የዋጋ ንረቱ ሲከሰት ደግሞ ኢኮኖሚው ያልተረጋጋ እንደሚሆን፤ ባለመረጋጋቱም በገበያው ላይ ያሉ ነጋዴዎች ላይ ተጽዕኖ ሲደርስ ከኢንቨስትመንት እንዲወጡ እንደሚያደርግ ገልጸዋል፡፡

በዚህ ምክንያት አብዛኞዎቹ እንደ መኪና፣ መሬትና ቤት በመሳሰሉ ቋሚ ዕቃ ላይ ኢንቨስት የማድረግ ሥራ



ዶክተር ጀማል መሐመድ

ላይ መሰማራታቸውን ጠቅሰው፤ ይህም ከፍተኛ የሆነ የቤት ዋጋ ንረትን አስከትሏል ብለዋል፡፡ የቤት ኪራይ፣ የኑሮ ውድነቱና ምርታማ በሆኑ ሴክተሮች ላይ ተጽእኖ አሳርፏል ሲሉም ገልጸዋል፡፡

ጦርነቱ ባለባቸው አካባቢዎች የትምህርት፣ የግብርናና የጤና ሁኔታ በራሱ ሌላኛው ተጽዕኖ እንደሆነ ዶክተር ጀማል ጠቁመዋል፡፡ ችግሩ ለቀጣይ ትውልድ ጭምር እንደሚተርፍ ገልጸዋል፡፡

እንደ ዶክተር ጀማል ገለጻ፤ ኢኮኖሚው እንዲሻሻል ጦርነቱ እየተጠናቀቀ በሄደባቸው አካባቢዎች ጸጥታን በፍጥነት የማስከበር ሥራ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ካልሆነ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች በፊት ወደነበሩበት ቶሎ አይመለሱም፡፡ በጦርነቱ ምክንያት የተዛቡ የአስተዳደር ሥርዓቶችን መቆጣጠርና እንቅስቃሴዎች እንዲጀመሩ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የተዛቡ ሲስተሞችንና ሴክተሮችን ማስተካከል ዋና የመንግሥት ትኩረት መሆን አለበት፡፡

በጦርነቱ ወቅት የተዛቡ ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶችን የመመለስ ሥራም እንደሚያስፈልግ አመላክተዋል፡፡ የተጎዱ ሴክተሮችን ለይቶ የማነቃቃት ሥራ ይጠበቃልም ብለዋል፡፡

ጦርነቱ ሊፈጥረው የሚችለው አንዱ ጉዳይ የሰው ኃይል እጥረት በመሆኑ የሰው ኃይል ግንባታ ላይ ትኩረት ተደርጎ መሥራት ተገቢ መሆኑን የጠቀሱት ዶክተር ጀማል፤ ትምህርት ቤቶች፣ ጤና ጣቢያዎች የተጎዱ በመሆናቸው በእነዚህ ላይ በመረባረብ አገርን ሊፈትኑ ከሚችሉ ችግሮች ከወዲሁ መከላከል እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

# «አሸባሪውን ሕወሓት በመጋለብ ሉዓላዊነታችንን ለመዳፈር የሚሞክሩትን አካላት በተባበረ ክንድ እንመክታለን»

- አቶ ሙሉጌታ አበበ

የአዲስ አበባ ከተማ ፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሰብሳቢ

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- አሸባሪውን ሕወሓት በመጋለብ ሉዓላዊነታችንን ለመዳፈር የሚሞክሩትን አካላት በተባበረ ክንድ እንመክታለን ሲል የአዲስ አበባ ከተማ ፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት አስታወቀ፡፡

የምክር ቤቱ ሰብሳቢ አቶ ሙሉጌታ አበበ እንደገለጹት፣ የአሸባሪው ሕወሓት ጉዳይ የውስጥ ጉዳይ በመሆኑ የሌላው የውስጥ ጉዳይ ጣልቃገብነት አያስፈልግም፡፡ ሆኖም ሕወሓትን ፈረስ አድርገው እየጋለቡ በአሸባሪው ጀርባ ታዝለው ወደ ኢትዮጵያ መግባትና ኢትዮጵያን ለማፍረስ የሚፈልጉ የውስጥም ሆነ የውጭ ኃይሎች አሉ፡፡

ነገር ግን ኢትዮጵያውያን የአባቶቻችን ልጆች በመሆናችን ለጣልቃ ገብነቱን በተባበረ ክንድ እንመክታለን ሲሉ አስጠንቅቀዋል፡፡

ሕወሓትን አጥብቀው የሚጠሉትና አምርረው የሚታገሉት ስለአሰራራቸው፣ ስለገረፋቸው እና ስለአሰቃያቸው ብቻ ሳይሆን በመጨረሻው ሰዓት በሚወዷት ኢትዮጵያ ስለመጣባቸው መሆኑን የተናገሩት ሰብሳቢው፤ በኢትዮጵያ ላይ የመጣውን ደግሞ የሚሸከም ትክሻ እንደሌላቸው ገልጸዋል፡፡

ሆኖም የአሸባሪው የትሕነግ ቡድን ጉዳይ የውስጥ ጉዳይ በመሆኑ ቡድኑን በቤተሰብ ውስጥ እንደ አፈንጋጭ ልጅ ማየት እንጂ ማንም ጣልቃ እንዲገባብን አንፈቅድም ያሉት አቶ ሙሉጌታ፤ አሸባሪው አፈንጋጭ ቡድኑ የቤተሰብ ልጅ እንደመሆኑ መጠን ዋጋ የሚያስከፍል ቢሆንም ልክ እስከሚገባ ድረስ ይቆነጠጣል ብለዋል፡፡

ሆኖም ሕወሓትን ፈረስ አድርገው እየጋለቡ በአሸባሪው ጀርባ ታዝለው ወደ ኢትዮጵያ መግባትና ኢትዮጵያን ለማፍረስ ለሚፈልጉ ለውስጥም ሆነ ለውጭ ኃይሎች ግን ዕድል አንሰጥም ሲሉ ተናግረዋል፡፡

አቶ ሙሉጌታ እንደገለጹት፤ የሰሜኑ የአገራችን ክፍል ጦርነት የታሪክ ጠባሳ ነው፡፡ እንዲሆን የማይመኝ ነው የሆነው፡፡ ከምኞት በዘለለ መከልከል አልተቻለም፡፡ ያለው አማራጭ አንድ እና አንድ ብቻ ነው፡፡ ኢትዮጵያ እንድትፈርስ መፍቀድ ወይስ ኢትዮጵያን ማዳን፡፡ ሆኖም ኢትዮጵያውያን ኢትዮጵያ ከምትፈርስ ይልቅ ቀድመው መስዋዕት ለመሆን ስለሚመርጡ ኢትዮጵያን የማዳን ሥራ እየሠሩ ይገኛሉ፡፡

ኢትዮጵያ ስትፈርስ ቆመን ከምናይ ይልቅ እኛ




ቀድመን ሕይወታችንን እንሰጣለን ያሉት ሰብሳቢው፤ ጀግናው የኢትዮጵያ ሕዝብ እጅግ በተወሳሰበ ፈተና ውስጥ እያለፈ የመጡበት ሲመስለው ከፈተናዎቹ ለይቶ ጠላቶቹን ማደባየት የሚያውቅ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል በተቃጣው አውዳሚ ጦርነት ያላዘነ ኢትዮጵያዊ እንደማይኖር የገለጹት ሰብሳቢው ሆኖም ጦርነቱ እንዳይገጥመን ብንፈልግም አገራችንን ከመፍረስ ለመታደግ አስፈላጊውን ሁሉ መስዋዕትነት እየከፈልን እንገኛለን ብለዋል፡፡

የጥፋት ቡድኑ እንዲታረም ከበቂ በላይ ዕድል ቢሰጠውም በኢትዮጵያ ህልውና እና ዕጣ ፈንታ ላይ ስለመጣ አንቅረን ተፍተነዋል ያሉት አቶ ሙሉጌታ፤ በአሸባሪነት ፈርጀነውም እየታገልነው እንገኛለንም ነው ያሉት፡፡

አሸባሪውን ቀጥረው ፍላጎታቸውን በተዘዋዋሪ ለማስፈጸም የሚታትሩ አንዳንድ አገራት እንዲታረሙም ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ኢትዮጵያ ይህንኑ የምጥ ዘመን አሸንፋ ብሩህ ዘመን እንደሚመጣላት በማመን ከጎኗ የቆሙት ትውልደ ኢትዮጵያውያንና ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ፣ ዲፕሎማቶችና የዓለም አቀፍ ተቋማት መሪዎች ውለታቸው የማይዘነጋ ነው ያሉት የምክር ቤቱ ሰብሳቢው፤ በአንፃሩ በተቃራኒው ኢትዮጵያን በተለያየ መንገድ የወጉት የእናት ጡት ነካሾች እና ታሪካዊ ጠላቶች ወደ ልቦናችሁ እንዲመለሱ አሳስበዋል፡፡



አቶ መስፍን አበበ

# ከወጪ ንግድ ከ959 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ተገኘ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ሦስት ወራት ከወጪ ንግድ ምርቶች 959 ነጥብ 7 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር መገኘቱን የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የሚኒስትሩ አማካሪ አቶ መስፍን አበበ ገለጹ።

የሚኒስትሩ አማካሪ አቶ መስፍን አበበ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባለፉት ሦስት ወራት ከወጪ ንግድ ምርቶች 1 ነጥብ 1 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 959 ነጥብ 7 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ተገኝቷል። በዚህም ለማሳካት ከታቀደው 85 ነጥብ 6 በመቶ ማሳካት ተችሏል።

ይህን ለማድረግ በሩብ አመቱ ከተሠሩ ሥራዎች ውስጥ አንደኛ በውልና በኢንቨስትመንት እርሻ የሚለሙ የቅባትና የጥርጥሬ ምርቶች አመቺ የውጪ ንግድ ግብይት አሠራር ሥርዓት ተዘርግቷል። ሁለተኛ የአገር ውስጥ ምርቶች በዓለም አቀፍ ገበያ ዋጋ መሠረት ኮንትራት ተገብቶ እንዲላኩ የተጠናከረ ድጋፍና ክትትል በመደረጉ ነው።

ባለፉት አመታት ተርፈው በላኪዎች እጅ የሚገኙ ምርቶች ላይ የቆጠራ ሥራ በማድረግ ለውጭ ገበያ እንዲላኩ ተደርጓል። ይህም ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በገቢ የ53 ሚሊዮን ዶላር ጭማሪ አለው ብለዋል።

ባለፉት ሦስት ወራት ከቅባት እህሎች 58 ነጥብ 6 ሚሊዮን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 52 ነጥብ 9 ሚሊዮን ዶላር ተገኝቷል ያሉት አማካሪው፤ ይህም ከባለፈው አመት የ5 ነጥብ 9 ሚሊዮን ዶላር ቅናሽ አሳይቷል ብለዋል።

እንደ አቶ መስፍን ገለፃ፤ የቅባት እህሎች በቂ አቅርቦት አለመኖር፣ ገበያ በመጠበቅ ምርቶችን መያዝ፣የዓለም አቀፍ የገበያ ዋጋ መቀዛቀዝና የኮንትሮባንድ ንግድ ለገቢው መቀነስ ምክንያት ናቸው። ሌላው አብዛኞዎቹ የቅባት እህሎች ለአገር ውስጥ ኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃነት እየዋሉ በመሆኑ ለውጭ ገበያ በብዛት እየተላኩ አይደለም ብለዋል።

ከቅባት እህሎች ሰሊጥ፣ ኑግና የዱባ ፍሬ ለውጭ ገበያ የቀረቡ ሲሆን፣ ለውዝ በተጠናቀቀው በጀት አመትና በአሁኑ አመት እየተላከ አይደለም። ምክንያቱም ለውዝ ከአመራረቱ ጀምሮ የሚከሰት አፍላ ቶክሲን የተባለ ፈንገስ በውስጡ በመያዙ ነው።

ለቀጣይ በተቻለ መጠን ይህንን ለማሻሻል ገበያዎችን ከማስፋት አኳያ፣ የአሠራር ሥርዓቶችን ዘርግቶ ተግባራዊ ከማድረግና ከላኪዎቻችን ጋር ውይይት በማድረግ ምርቶቹ በአግባቡ እንዲላኩ ሰፊ ሥራዎች እየተሠራ ነው። በበጀት አመቱም የተሻለ ለውጥ ይመጣል ሲሉ ተናግረዋል።

የቅባት እህሎቹ መዳረሻ እሥራኤል፣ የተባበሩት አረብ ኤሜሬት፣ ሲንጋፖር፣ ቱርክና ቬትናም ሲሆኑ ለነዚህ አገሮች ወደ 32 ሺህ ሜትሪክ ቶን ተልኳል ብለዋል።

ከግብርና ዘርፎች የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ክትትል የሚያደርግባቸው የቅባት እህል፣ የጥራጥሬ ምርት፣ ጫት፣ የብርዕና አገዳ ሰብሎች፣ ዕጣንና ሙጫ እና የቁም እንስሳት ናቸው።

ከጥራጥሬ ሰብል 50 ነጥብ 5 ሚሊዮን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 40 ነጥብ 7 ሚሊዮን ዶላር ተገኝቷል። ከተፈጥሮ ሙጫና ዕጣን ደግሞ 1 ነጥብ 1 ሚሊዮን ለማግኘት ታቅዶ 175 ሺህ ዶላር ገቢ ተገኝቷል።

ከጫት መቶ ሚሊዮን ዶላር ይገኛል ተብሎ 80 ነጥብ 9 ሚሊዮን ዶላር ተገኝቷል። ከብርዕና አገዳ ሰብሎች 940 ሺህ ዶላር እናገኛለን ተብሎ 725 ሺህ ነጥብ 9 ዶላር ተግኝቷል። ሆኖም እነዚህ እገዳ ላይ ናቸው ብለዋል፡፡ የሰብሎቹ የእገዳ ምክንያት የተትረፈረፉ ምርት ባለመሆናቸውና የአገሪቱ ዋነኛ ምግብ በመሆናቸው ነው ብለዋል።

በ2014 ሩብ አመት 906 ነጥብ 3 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ የተገኘ ሲሆን፣ በተያዘው ሩብ አመት 959 ነጥብ 7 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ማግኘት ተችሏል። በአገራችን ከፍተኛ የሆነ የግብርና ምርት ስለሚኖር፣ የምርት መዳረሻዎች መበራከት፣ የግል አምራቾች ያመረቱትን ምርት በቀጥታ ወደ ውጭ እንዲልኩ ፍቃድ በመሰጠቱ የአሁኑ አመት ከባለፈው ሩብ አመት ከፍ ተደርጎ እንዲታቀድ ምክንያት ፈጥሯል ብለዋል።

# «የሲሚንቶ እጥረት ለፕሮጀክቶች መጓተትና ለተጨማሪ ወጪ ዳርጎናል»

- የኮንስትራክሽን ባለሙያዎች

# «ፋብሪካዎቹ በሙሉ አቅማቸው እንዲያመርቱ ጥረት እየተደረገ ነው»

- የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- በሲሚንቶ እጥረት ምክንያት ፕሮጀክቶችን በተያዘለት የጊዜ ገደብና የዋጋ ተመን ባለመጨረሳቸው ምክንያት ለፕሮጀክቶች መጓተትና ለተጨማሪ ወጪ መዳረጋቸውን በግንባታ ዘርፍ የተሰማሩ ባለሙያዎች ገለጹ።

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በበኩሉ፣ ሕገ ወጥ የሲሚንቶ ንግድን ከመቆጣጠር ጎን ለጎን የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ዕቃዎችን ከውጭ በማስገባት በሙሉ አቅማቸው እንዲያመርቱ ጥረት እየተደረገ መሆኑን አስታውቋል።

ሰሞኑን በአዲስ አበባ የአንድ ኩንታል ሲሚንቶ ዋጋ ከአንድ ሺህ 800 ብር በላይ ከመድረሱ ጋር ተያይዞ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በኮንስትራክሽን ሥራ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎችን አነጋግሮ ነበር።

የአተም ኮንስትራክሽን ጠቅላላ የሥራ ተቋራጭ የሳይት ሥራ አስኪያጅ አቶ ሄኖክ ልዑልሰገድ እንደገለጹት፤ ለትላልቅ ሕንፃ ግንባታዎች ሲሚንቶ በተፈለገ ጊዜ አለመገኘቱ የግንባታ ፕሮጀክት መጓተት ችግር እየፈጠረባቸው ነው።

ይህ ደግሞ በሙሉ አቅም እንዳንሠራ ስላደረገን ሠራተኞችን እንድንቀነስ አስገድዶናል ያሉት አቶ ሄኖክ፤ በዚህ የተነሳ በቀን ሥራ የተሰማሩ ሠራተኞች ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እያሳደረ ይገኛል ሲሉ ጠቁመዋል።

መንግሥት መመሪያ በማውጣትና ቁጥጥር በማድረግ ብቻ አሁን ያለውን የሲሚንቶ አቅርቦት እጥረት መቅረፍ አይችልም ያሉት አቶ ሄኖክ፣ አዲስ መመሪያ ቢወጣም በተጨባጭ ግን መደበኛ የግንባታ ፍቃድ ካላቸው ከጥቂት ኮንትራክተሮች በቀር ጥቃቅን ግንባታ ያላቸው ተቋራጮች በብዙ የግብይት ሰንሰለት ያለፈውን ሲሚንቶ ከተራ ተጠቃሚዎች ጋር አንድ ኩንታል በአንድ ሺህ 800 ለመግዛት እየተገደዱ መሆናቸውን አመላክተዋል።

በተመሳሳይ መልኩ፣ የብሉ ቢዩልደርስ ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ አቶ አለምነው ሽፈራው፣ መንግሥት በቅርቡ የሲሚንቶ መሸጫ ተመን ቢያወጣም ከነጋዴዎችም ሆነ ከፋብሪካዎች ሲሚንቶ እየተገኘ



አለመሆኑን የተናገሩ ሲሆን፤ በሲሚንቶ ዋጋ መናር ቀደም ሲል እስከ 3500 ብር የሚሠራው የአንድ ሜትር ኪዩብ አርማታ ዋጋ ዛሬ ላይ በሦስት እጥፍ አድጎ እስከ 12 ሺህ ብር መድረሱን ጠቁመዋል። በሲሚንቶ እጥረትና በተወሰነ መልኩ በብረት ችግር የግንባታ ፕሮጀክት ከአንድ ዓመት በላይ እንደሚዘገይም አመላከተዋል።

የመንግሥት ተቆጣጣሪ አካላትንም ማጥራት ያስፈልጋል ያሉት አቶ አለምነው፤ በተጨማሪም ትላልቅ ኢንቨስተሮች የሲሚንቶ ፋብሪካዎችን እንዲገነቡ ማበረታታትና ጥሬ ዕቃዎች የሚገኙባቸው ቦታዎችን መለየት እንደሚገባቸውም መክረዋል።

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ ተወካይ ወይዘሮ ቁምነገር እውነቱ ጉዳዩን አስመልክተው በሰጡን ምላሽ፤ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ እድገት ጋር ተያይዞ እየተስተዋለ ያለውን የሲሚንቶ እጥረት ችግር ለመፍታት ብዙ ጥረት ተደርጓል ብለዋል።

ምንም እንኳ የአፈጻጸም ችግር ቢኖርም የሲሚንቶ መሸጫ ላይ መመሪያ ወጥቶ 908/2014 ወጥቶ ከሐምሌ 5 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ መደረጉን ጠቁመዋል።

ለሲሚንቶ ዋጋ መናርና ከገበያ መጥፋት አንዱ ምክንያትም የሲሚንቶ ፋብሪካዎች በማሽን ብልሽት፣ በጸጥታ ችግር፣ የድንጋይ ከሰል አቅርቦት ችግር ምክንያት በሙሉ አቅማቸው እያመረቱ አለመሆኑን ገልጸዋል።

ደርባንና ኢስት የሲሚንቶ ፋብሪካዎች በጥገና ምክንያት ሥራ ያቆሙ ሲሆን፣ ኢትዮ የሲሚንቶ ፋብሪካ በከሰል ድንጋይ እጥረት ምክንያት ለጊዜው ማምረት ማቆማቸው በገበያው ለተከሰተው የሲሚንቶ እጥረት በማሳያነት የሚጠቀሱ ናቸው ብለዋል።

የብልሽትና የጥሬ ዕቃዎች አቅርቦት ችግርን ለመፍታት የሲሚንቶ ፋብሪካዎች አስፈላጊ ጥሬ ዕቃዎችን በውጭ ምንዛሪ እንዲያስገቡ ሚኒስቴር መስሪያቤቱ የትብብር ደብዳቤ መጻፉን ጠቁመው፤ በሌላ በኩል ደግሞ ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ግብይቱን የሚረብሹ አካላት ላይ ከክልሎች ጋር በመቀናጀት እርምጃ እየተወሰደ ይገኛል ብለዋል።

በአሁኑ ወቅትም ዳንጎቴ፣ ናሽናል፣ ሐበሻ፣ ሙገር፣ ካፒታል ሲሚንቶ ፋብሪካዎች ምርት በማሰራጨት ላይ መሆናቸውንም ጠቁመዋል።

ያም ሆኖ ግን ሕገወጦች ሆን ብለው ሲሚንቶን በመደበቅ እና በማሸሽ እንዲሁም ሆን ብለው ዋጋን በማዛባት አላግባብ ለመክበር በሚያደርጉት ጥረት ኅብረተሰቡ መጎዳት ስለሌለበት መንግሥት አስፈላጊውን እርምጃ በመውሰድ ላይ መሆኑንና ይህንንም አጠናክሮ እንደሚቀጥል ወይዘሮ ቁምነገር ተናግረዋል።

# «አገራዊ ምክክሩ ችግሮቻንን በመቅረፍ ሁለንተናዊ ለውጥ እንድናመጣ ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል»

- አቶ ኤፍሬም ማዴቦ- የፖለቲካ ተንታኝ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- አገራዊ ምክክሩ ችግሮቻችንን መፍታት የሚችልና በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ አውቀውም ሆነ ሳያውቁ ያጠፉ ግለሰቦች እና ድርጅቶች ላጠፉት ጥፋት እርማት የሚወስዱበት እንዲሁም ለአገር ሁለንተናዊ እድገት ሁሉም ዜጋ በጋራ እንዲነሳሳ የሚያነቃቃ መሆኑን የፖለቲካ ተንታኝ አቶ ኤፍሬም ማዴቦ ገለጹ።

የፖለቲካ ተንታኝ አቶ ኤፍሬም ማዴቦ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ከ2020 ጀምሮ በበርካታ ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ ፈተናዎች አልፋለች፡፡ ድርቅ፣ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ እንዲሁም የአሸባሪው ሕወሓት ወረራ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ችግሮቹም ለኢትዮጵያ አጠቃላይ የልማት እቅዶች አፈጻጸም ከፍተኛ ፈተና ሆነው ቆይተዋል።

ብሔራዊ ምክክሩ ኢትዮጵያን ያጋጠሟት ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ ችግሮች በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተቋማት ላይ ያስከተሉት ተጽዕኖ በስፋት ሊዳሰስ እንደሚገባ ጠቅሰው፤ ብሔራዊ ምክክሩ በኢትዮጵያ የሚከሰቱ አላስፈላጊ ግጭቶችን በማስወገድ ሁለንተናዊ እድገት ማምጣት የሚችል ነው ብለዋል።

የምክክር ሂደቱም ውጤታማ ሆኖ ችግሮችን በየደረጃው ለመፍታት እንዲችል የሁሉም ኢትዮጵያዊ ንቁ ተሳትፎ እንደሚያስፈልግ እና ይህንን ዕድል የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት በአግባቡ ሊጠቀምበት እንደሚገባም አሳስበዋል።

አሁን ላይ በኢትዮጵያ እየተፈጠሩ ያሉ ግጭቶችና የውጭ ጫናዎች አገራዊ ምክክሩ የያዘውን አላማ ማስቆም የሚችሉ አይደሉም ያሉት አቶ ኤፍሬም፤ ይህ የሚሆነው የኢትዮጵያውያን ተሳትፎ የሚታይበት ከሆነ ነው። ስለዚህ መንግሥት በኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲ እንዲሰፍን የምክክር ኮሚሽኑን ከተጽዕኖ ነፃ ማድረግ ይኖርበታል ብለዋል።

የአገራዊ ምክክሩ ዋናው ግብ ቀጣዩን ትውልድ ማዳን ነው:: ለነገው ትውልድ ታስቦ የሚሠራ ከሆነ የሚያነታርክና የማያግባባ ነገር አይገጥምም። ስለዚህ ኢትዮጵያ ለትውልድ የምታወርሳቸው ዕሴቶችን የምታሸጋግርበት ሆኖ እንዲጠናቀቅ ርብርብ ልናደርግ ይገባል ብለዋል::

በኮሚሽነርነት የተመረጡ ሰዎች አገራዊ ምክክሩ እንዲካሄድ ኃላፊነት ተሸከሙ እንጂ አወንታዊ አስተዋፅዖ ማበርከት ከሁላችንም የሚጠበቅ ተግባር ነው ያሉት አቶ ኤፍሬም፤ ምክክሩ የማያግባቡን ነገሮች ላይ ለመግባባት ዕድል ከመስጠቱም ባሻገር በአግባቡ ከተጠቀምንበት ጥሩ ባህል እንድንገነባ ይረዳናል ብለዋል::

በውጭ አገራት ጣልቃ ገብነት እና ልርዳችሁ ባይነት የሚካሄዱ አገራዊ ምክክሮች በአብዛኛው ለአገሬውና ለዕዳ ተሸካሚው ሕዝብ መዘዝ ይዘው የሚመጡ ናቸው ብለዋል::



አቶ ኤፍሬም እንዳሉት፤ ከአውሮፓ አገራት ፖላንድ በአገራዊ ምክክር ስኬት ተጠቃሽ ናት፤ ከዚህ ውጪ ያሉት አብዛኞቹ በኤዥያ፣ አፍሪካ እና በላቲን አሜሪካ ውስጥ ያሉት አልተሳካላቸውም:: ሆኖም ከአፍሪካ ውስጥ ደቡብ አፍሪካና ቱኒዝያ ተረጋግተው እንዲቀጥሉ ያስቻለና ጥሩ የሚባል ነው:: ከነዚህ አገራት ነባራዊ ሁኔታዎችን ያገናዘበ ትምህርት መውሰድ መልካም ነው።

የለውጡ መንግሥት የምክክር ኮሚሽኑን፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ተቋማትን፣ መሠረተ ልማቶችን በማሟላት ረገድ የሚያደርገው እንቅስቃሴ ሊበረታታ እንደሚገባም ተናግረዋል።

# «የተሻለች አገር ለመገንባት መሠረቱ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ትውልድ ያላት አገር ችግሮችንም ተቋቁማ ለማለፍ አትቸገርም ብለዋል።

ትውልዱን ትኩረት አድርገን መሥራት ከቻልን የበለጠ ፍሬያማ እንሆናለን፤ መንግሥት ትውልድን በመሥራት አገር ለማሻገር ሥራ ትኩረት ሰጥቷል። በቀጣዩ ትውልድ ላይ መሠረት ለመጣል አላማ አድርገን ለምናከናውናቸው ሥራዎች የወዳጅነት ፓርክ የሕፃናትና ወጣቶች መዝናኛ ስፍራ አንዱ ምሳሌ ይሆናል ሲሉ ተናግረዋል።

በፓርኩ ውስጥ የሚዝናኑ ልጆች በዘመናዊ መንገድ እንዴት ፈተናዎችንና ችግሮችን ማለፍ እንደሚችሉ እየተማሩ አካላቸውንና አዕምሯቸውን ማዳበር ይችላሉ። በዚህ አግባብ ካየነው ተመሳሳይ ፕሮጀክቶችም በየክልሎቹ መገንባትና ቀጣዩ ትውልድ ላይ መሥራት ይገባል ሲሉ አስረድተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳስታወቁት፤ ፈተናዎችን የሚቋቋም ጠንካራ ትውልድ መገንባት የሚቻለው ከታችኛው የዕድሜያቸው ክልል አንስቶ ነው፤ ለዚህ ደግሞ ሕፃናት ማንበቢያ፣ ማሰቢያ እንዲሁም አካላዊና አዕምሯዊ ብቃታቸውን የሚያዳብሩባቸው ስፍራዎች በብዛት ያስፈልጓቸዋል።

መንግሥትም ቀጣዩ ትውልድ ላይ መሠረቱ ላይ መሥራት ይገባል በሚል ካሉት ዩኒቨርሲቲዎች በተጨማሪ አዲስ ሳንገነባ ጥራታቸውን እያሳደገ በተመሳሳይ ጊዜ ደግሞ በርካታ የሕፃናት መዋያዎችንና ትምህርት ቤቶችን እየገነባ ይገኛል ብለዋል።

በዚህ አግባብ በሺዎች የሚቆጠሩ የሕፃናት ቅድመ ትምህርት ቤቶች መገንባታቸውን የገለጹት ዶክተር ዐቢይ፤ ከዚህ ባለፈ ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ጋር በተያያዘ ዘጠኝ ሚሊዮን ሕፃናትን መመገብ ተችሏል ሲሉ አስረድተዋል።

ከመዋዕለ ሕፃናትና በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከተከናወኑ ሥራዎች ባለፈ እንደ ወዳጅነት ፓርክ ምዕራፍ ሁለት ዓይነት ፓርኮች ለትውልድ ግንባታ ያላቸው ሚና ከፍተኛ መሆኑን ገልጸዋል።

ፓርኩ በከተማዋ መሃል የሚገኝና ዜጎች ልጆቻቸውን ለማዝናናት ሲፈልጉ በቅርበት የሚያገኙት ደረጃውን የጠበቀ ስፍራ መሆኑን ጠቁመዋል። ልጆች ከተፈጥሮ ጋር ተግባብተው ጊዜያቸውን የሚያሳልፉበት ስፍራ በመሆኑ ሕፃናት ላይ ላይ መሠረት አድርገን እየሠራን ነው ብለዋል።

የወዳጅነት ፓርክ ሁለተኛው ምዕራፍ ስፖርትን፣ ጨዋታንና ማኅበራዊ መስተጋብርን ያቀናጀ ነው። ልጆች እየተጫወቱ ሳይንስና ቴክኖሎጂን ይለማመዳሉ። ወጣቶች ያነባሉ፣ ደግሞም ስፖርት ይሠራሉ። ወላጆችና አያቶች ከልጆቻቸው ጋር መጥተው ማኅበራዊ ልምዳቸውን ይለዋወጣሉ ሲሉ ገልጸዋል።

አዲስ ተጋቢዎች በሥርግ ዐጸዱ ጋብቻቸውን ይመሠርታሉ። የነገዋ ኢትዮጵያ የተሻለች እንድትሆን የተሻለ ትውልድ እያፈራን እንቀጥላለን ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ እንዳስታወቁት፤ የወዳጅነት ምዕራፍ ሁለትን ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ለአንድ ሳምንት በነፃ መጎብኘት ይችላል።



ፎቶ በገባቦ ገብሬ

# ኢትዮጵያዊነትን ለማጽናት ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በኢትዮጵያ ሆቴል በተዘጋጀው መርሃ ግብር የተገኙ ኢትዮጵያውያን ችግሮቻችንን በይቅርታና በውይይት በመፍታት ጥንት አባቶቻችን የነበራቸውን ኢትዮጵያዊ አንድነት መመለስ ይገባል ብለዋል።

ኮር ዳዊት ጌታሁን በመድረኩ መክፈቻ ላይ እንደገለጹት፤ በተፈጠረው ችግር ልባቸው የደማ፣ አዕምሯቸው የተነካና ብዙ ችግሮች የደረሰቡባቸው የኅብረተሰብ ክፍሎችን በማረጋጋት ከኢትዮጵያዊነት ጋር ማጽናት አለብን። ዘረኝነትና ጎጠኝነት ገዳይ የሆነ ካንሰር ነው። ስለዚህ ከዚህ አስተሳሰብ በመውጣት በልዩነታችን ውስጥ አንድነታችንን አጥብቅን ኢትዮጵያን ማጽናት ያስፈልጋል።

በህዳሴው ግድብ ዙሪያ የምዕራቡን ዓለም በአረብኛ ቋንቋ በመሞገት የሚታወቀው መሐመድ አልአሩሲ፤ ብዙዎች ዓለማችን ላይ አገራቸውን የሸጡ፣ ለአደጋ ያጋለጡ እንዲሁም አገራቸውን የተቀሙ ብዙ አገራት አሉ። ኢትዮጵያ ግን እስካሁን ራሷን አስከብራ ኖራለች፣ አሁንም እየቀጠለች ነው፤ ትቀጥላለችም። ኢትዮጵያ የብዝሃ ቋንቋ፣ የብዝሃ እምነቶች፣ የፖለቲካም ይሁን የሌሎች አስተሳሰቦች ባለቤት አገር ነች። እነዚህን አስተሳሰቦች በአንድነት አቀናጅትን ወደ ልማት ማምጣት የሁሉም ኢትዮጵያዊ ድርሻ ነው ሲል ገልጿል።

አልአሩሲ፣ «አገር እንደ መልካም ቤት ናት፤ መልካም ቤት ጌታ፣ ጠባቂ፤ ቤተሰብም አለው። ይህ ቤተሰብ በመልካም ሥነምግባር ታንጾ ካደገ ሥርዓት ያለው መልካም ቤት ይሆናል። ከቆሸሸም ሥርዓት የሌለው ቤት ይሆናል። ስለዚህ ከፍ ብለን ያን ቤት ስናየው በሰማይ ላይ እንዳሉ ከዋክብቶች የሚያበራ ይሆንና ሁሉን የማረከ ይሆናል። ስለዚህ እናት የሆነችው አገራችን በአንድነት እንገንባ» ሲል ገልጿል።

አገራችን ብዙ ፈተናዎች አሉባት፤ እንዴት ማሸነፍ እንዳለብን ዘዴውን መቀየስ ያለብን እኛ ነን። ችግሮች የሚጠነክሩት በተናጠል ነው፤ በአንድነት ግን ማሸነፍ እንደሚቻል አልአሩሲ ተናግሯል።

ብርጋዴር ጄኔራል ካሳዬ ጨመዳ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያን ለማጽናት ኃይላችን አንድነታችን ነው። የውጭ ጠላቶቻችን ኢትዮጵያ እንዳትለወጥ በውስጣችን ያሉ ተላላኪዎችን ፈጥረው ሊበትኑን ፈለጉ። ይህ ግን አይቻልም፣ ኢትዮጵያን ለማጽናት ልክ የመከላከያ ቀን እንደተከበረው ሁሉ በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች መድረክ ተዘጋጅቶና በአደባባይ ኢትዮጵያዊነት እንዲሰበክ ማድረግ ያስፈልጋል። ኢትዮጵያዊነት እንዲያብብ የትምህርት፣ የኃይማኖት ተቋማት በአስተምሯቸው ኢትዮጵያዊነትን ሊሰብኩ እንደሚገባ በአጽዕኖት ገልጸዋል።

መምህር ታዬ ቦጋለ ኢትዮጵያዊነትን ለማጽናት እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ እንደመከላከያ መሆን አለበት። መከላከያ ለአገር መስዋዕትነት የሚከፍሉት ብሔር ብሔረሰቦች ወጥተው በኢትዮጵያ ጥላ ስር አገራቸውን በማስቀደም ነው። ስለሆነም ለአገር መቆም መሠረታዊ አሀድ የሆነውን መከላከያ ፈለግ መከተል አስፈላጊ ነው። ከታላቁ ኢትዮጵያዊነት ተራራ ላይ ወርደን ለውጭ ኃይሎች ፈረስ መሆን አያስፈልገንም ብለዋል።

ማንኛውንም ዓይነት የብሔር፣ የአስተሳሰብና የአመለካከት ልዩነት በሰለጠነ መንገድ በውይይት ለመፍታት መዘጋጀት፣ ከጦርነቱ መገባደድ በኋላ ያለውን የተስፋ ጊዜ ስለኢትዮጵያ ተብሎ ያለፈውን ሁሉ በይቅርታ ትቶ የወደፊቱን መልካም አጋጣሚ ለመጠቀም መዘጋጀት፣ የተሳሰርንበትን ኢትዮጵያዊነታችንን ለማጽናት ከወዲሁ በማሰብ ለአገራችን መጻኢ ዕድል ተስፋዎቿ የአሁኑ ትውልዶች መሆናችን መረዳት የሚሉት የምክክሩ ማጠንጠኛ ሀሳቦች ነበሩ።

ከየክልሉ የተወከሉ የኢትዮጵያዊነት ይቀጥላል በጐ ፈቃደኛ ወጣቶች ኢትዮጵያ ትናንት ነበረች፣ ዛሬም አለች፣ ነገር ግን ያሉ ችግሮችን በውይይት በመፍታት ኢትዮጵያዊነትን ማጽናት አለብን ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

# አፍሪካውያን ከአንዳንድ ምዕራባውያን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መሆኑን አስረድቷል።

መድረኩ አፍሪካውያን ወጣቶችን የሚያነቃና ከውጭ ጫናዎች ለመላቀቅ ሙሉ አቅም እንዳላቸው የሚያሳይ መሆኑን የጠቀሰው ወጣቱ፤ አፍሪካውያን አገራት ለብዙ አህጉራት የሚተርፍ ሀብት እንዳላቸውም አስታውሷል።

እንደ ፔምባ ገለጻ፣ የውጭ እርዳታና ጫና አፍሪካን ወደፊት እንዳትራመድ አድርጓታል፤ በውጭ አገራትና ተቋማት ጥገኛ የምንሆንበት ጊዜ ማብቃት አለበት፤ ለዚህ ደግሞ የወጣቱ ሚና ከፍተኛ ነው። አፍሪካውያን ወጣቶች ይህን በመገንዘብ አህጉሪቷን ወደፊት ለማራመድ በጋራ ሊሠሩ ይገባል።

አፍሪካውያን መሪዎችም የአፍሪካን ችግር በአፍሪካውያን ለመፍታትና ከምዕራባውያን ጫና ነፃ ለመውጣት ከምንጊዜውም በላይ በቁርጠኝነት እንዲሠሩ ጥሪውን አቅርቧል።



ጃክሰን አኪም ፔምባ

ፔምባ የኢትዮጵያን ወቅታዊ ሁኔታ ሲገልጽ፣ አንዳንድ ምዕራባውያን አገራትና ተቋማት በሌሎች አገራት ፖሊሲያቸውን ተግባራዊ ማስደረግና ፍላጎታቸውን ማሳካት ፈልገው አልሳካ ሲላቸው በአገራቱ የውስጥ ጉዳይ ላይ ጣልቃ ለመግባት ያስችለኛል ያሏቸውን መንገዶች ሁሉ ይጠቀማሉ፤ ከእነዚህም አንዱ የውሸት ፕሮፓጋንዳዎችን ማስተጋባት ነው ብሏል።

«ከዚህ በፊት አንዳንድ የአፍሪካ አገራት እንዳየነው የውጭ ኃይሎች በገቡባቸው አገራት ሁሉ ችግሮች ተፈጥረዋል፤ ስለዚህ ችግሮቻችንን በራሳችን አቅም ከመፍታት ውጪ የእነሱን እርዳታ ልንሻ አይገባም፤ የአፍሪካውያን ችግሮች በአፍሪካውያን ብቻ ሊፈታ ይገባል» ሲል አጽንዖት ሰጥቷል።



ፋዲመቱ ኢዮዋ ዑስማኑ

ካሜሮናዊቷ ፋዲመቱ ኢዮዋ ዑስማኑ በበኩሏ፣ ከምዕራባውያን እርዳታና ጫና ነፃ ለመውጣት አፍሪካውያን ወጣቶች ከምንጊዜውም በላይ አንድ ሊሆኑና በትብብር ሊሠሩና፤ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል ብላለች።

በርካታ አፍሪካውያን አገራት የምዕራባውያን አገራት ጫናዎችን ጨምሮ በርካታ ተግዳሮቶችን እያስተናገዱ መሆኑን የጠቀሰችው ፋዲመቱ፤ እነዚህን ችግሮች ከመጋፈጥ አንጻር አፍሪካውያን አገራት ተሞክሮዎቻቸውን ሊለዋወጡና በጋራ ሊሠሩ እንደሚገባም አሳስባለች።

የኢትዮጵያን ወቅታዊ ሁኔታ በተመለከተ፣ በአገሪቱ እየሆነ ስላለው ነገር በዜናና በሌሎችም አማራጮች እየሰማች እንደሆነ ገልጻ፤ «በኢትዮጵያ ላይ የሚደረጉ የውጭ ጫናዎችን በመቃወምና ለኢትዮጵያ አጋርነታችን ለማሳየት እንደአፍሪካዊ ወጣት ድምጻችን እያሰማን ነው»ብላለች።

አፍሪካውያን ወጣቶች ኢትዮጵያ ያለችበትን ሁኔታ በመረዳት ለኢትዮጵያ ድምጻቸውን እንዲያሰሙ ጥሪ ያቀረበችው ወጣቷ፤ ኢትዮጵያ በቅርቡ አሁን ካለችበት ችግር እንደምትወጣና ዘላቂ ሰላሟ እንደሚመለስ ተስፋ እንዳላትም አስታውቃለች።



አልዳው አብደላህ

አፍሪካን እየፈተኗት ካሉ ዘርፈ-ብዙ የውስጥና የውጭ ችግሮች ለማላቀቅ አፍሪካውያን አንድ ሊሆኑ ይገባል ያለው ደግሞ ሱዳናዊው አልዳው አብደላህ ሲሆን፤ በኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ሌሎችም ጉዳዮች ጠንካራ ትብብር እንደሚያስፈልግም አብራርቷል።

«እንደ አህጉር በትብብር ከሠራን የማንፈታቸው ችግሮች አይኖሩም» ያለው ወጣት አልዳው፤ ለአፍሪካዊ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሄዎች መፈለግ እንደሚገባም ጠቁሟል።

ወጣት አልዳው ጎረቤታሞቹን ኢትዮጵያና ሱዳን እንደምሳሌ በማንሳት፣ ኢትዮጵያ ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ያላትና በአገሪቱ ትልቅ የገበያ ዕድል ያለ ሲሆን፣ ሱዳን የምታመርታቸውን የግብርና ምርቶች ወደ ኢትዮጵያ መላክ ትችላለች፤ በሱዳን ደግሞ የኤሌክትሪክ ኃይል እጥረት ያለ ሲሆን፣ ሱዳን ይህን ችግር ለመፍታት የኤሌክትሪክ ኃይልን ከኢትዮጵያ መግዛት ትችላለች ብሏል።

ሌሎችም አገራት ልምድና ተሞክሯቸውን እንዲለዋወጡና ያሏቸውን ተፈጥሯዊ ሀብቶች በመተሳሰብ እንዲጠቀሙ ጥሪውን ያቀረበው ወጣቱ፤ አረንጓዴ አሻራና ሌሎችም ኢትዮጵያ ውጤታማ የሆነችባቸው ፕሮጀክቶች ወደ ሌሎች የአፍሪካ አገራት ማስፋፋት እንደሚገባም ተናግሯል።

# የመከላከያ ሠራዊት የትግራይን ሕዝብ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ከመከላከያ ሠራዊት ጎን በመሆን እያደረገ ላለው አስተዋጽኦም ምስጋና አቅርቧል።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ትናንት ባወጣው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ የመከላከያ ሠራዊቱ መሥዋዕትነት የታሰበውን ግብ እንዲያሳካ የትግራይ ሕዝብ የማይተካ ሚና እየተጫወተ ይገኛል።

የትግራይ ሕዝብ የመከላከያ ሠራዊቱን በመንከባከብ፣ ስንቅ በማቀበል፣ ስለተደበቁ ጀሌዎችና የጦር መሣሪያዎች መረጃ በመስጠት፣ መንገድ በመምራት እና አካባቢውን በመጠበቅ ከሠራዊቱ ጋር ተሰልፏል ያለው መግለጫው፤ ለዚህም መንግሥት ምስጋናውን ያቀርባል ብሏል።

መግለጫው እንደገለጸው፤ የትግራይ ሕዝብ ከመከላከያ ሠራዊቱ ጋር ያለው ቅንጅት አሸባሪውን ሕወሓት አስደንግጦታል። በዚህም የተነሣ «ምስለኔዎች ሊያስተዳድሩህ እየመጡ ነው» የሚል ውዥንብር እየነዛ ነው።

ነገር ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሕወሓት ጋር የታገለው የምስለኔ አስተዳደር እንዲቀር ነው ያለው የመንግሥት ኮሙኒኬሽን መግለጫ፤ የምስለኔ አስተዳደርን በክልሎች ላይ እንደገና የዘረጋው አሸባሪው ሕወሓት መሆኑንም አስታውሷል።

የትግራይ ሕዝብ በራሱ ልጆች እንጂ በማንም ሊተዳደር አይገባም ያለው መግለጫው፤ ፌዴራላዊ ሥርዓቱም ይሄንን አይፈቅድም፤ አሸባሪው ሕወሓትም ይሄንን ያውቃል፤ ይደብቃል እንጂ ሲል አብራርቷል።

በመሆኑም የትግራይ ሕዝብ የአሸባሪው ሕወሓትን የምስለኔ ቴአትር፣ በምስለኔነት ለኖረው ሕወሓት ትቶ፣ ከመከላከያ ሠራዊቱ ጋር የጀመረውን ትብብር እንዲያጠናክር መንግሥት ጥሪውን አቅርቧል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ኢትዮጵያ በሀሰት ፕሮፖጋንዳ የሚደነግጥ ልብና የሚዝል ክንድ የላትም!

ኢትዮጵያ ነፃነቷንና ሉአላዊነቷን ጠብቃ የዘለቀች ጥንታዊት አገር ነች፡፡ በየዘመናቱ ሉአላዊነቷን ለመዳፈር የመጡ የውጭ ወራሪዎችን አሳፍራ ስትመለስ የቆየች የአይበገሬነት ተምሳሌትና የጥቁር ሕዝቦች መኩሪያ አገርም ናት፡፡ ይህም አኩሪ የነፃነት ተጋድሎ ዛሬም በልጆቿ ደምና አጥንት ተከብሮ ይገኛል፡፡

ኢትዮጵያ በየዘመኑ ለነፃነቷ ዋጋ የከፈለች አገር ናት። የኢትዮጵያን ሉአላዊነት ለመዳፈር የመጣውን የጣሊያን ወራሪ ኃይል አሳፍራ በመመለስም ከራሷ አልፋ ለሌሎች ጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ተምሳሌት ሆና የዘለቀች አገር ናት። ይህ የሆነው ደግሞ ኢትዮጵያውያን ለነፃነታቸውና ለሉአላዊነታቸው ሲሉ ማንኛውንም ዓይነት መስዋዕትነት ለመክፈት ዝግጁ የሆኑ ሕዝቦች ከመሆናቸው የሚመነጭ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ስትፈተን የቆየችው በውጭ ወራሪዎች ብቻ ሳይሆን በውስጥ ባንዳዎችም ጭምር ነው፡፡ አሸባሪው ትህነግን የመሳሰሉ ከጥንስሳቸው ጀምሮ ኢትዮጵያን ለማፈራረስ ቆርጠው የተነሱ ቡድኖች ከውጭ ወራሪዎች ጋር በማበር የአገሪቱን ሉአላዊነት አሳልፈው ለመስጠት ሌት ተቀን ሲሠሩ ቆይተዋል፡፡ ኢትዮጵያ ከወራሪው የሶማሌ መንግሥት ዚያድ ባሬ ጋር ጦርነት በገባችበት ወቅት አሸባሪው ትህነግ ከወራሪው ጎን በመሰለፍ ኢትዮጵያን ሲወጋ መቆየቱን የታሪክ ድርሳናት እማኞች ናቸው፡፡ ዛሬም የተጣባው ክፉ አመል አልለቅ ብሎት የውጭ ኃይሎች አደግዳጊ ሆኖ የኢትዮጵያን ሉአላዊነት አሳልፎ ለመስጠት በብርቱ እየደከመ ይገኛል፡፡

ሆኖም በዴሞክራሲያዊ ምርጫ አገር የማስተዳደሩን ኃላፊነት የወሰደው የኢትዮጵያ መንግሥት የአገሪቱን ሉአላዊነት የማስጠበቅም ሆነ ልማትን የማረጋገጥ በቂ አቅም አለው፡፡ መንግሥት በሚያስተዳድረው የግዛት ክልሉ ውስጥ የሚነሱ የጸጥታ ችግሮችን የማረምና ሕዝብ በሰላም ወጥቶ እንዲገባ የማድረግ ኃላፊነትንም ጭምር በአደራ ተቀብሏል፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ የጸጥታም ሆነ የልማት ጉዳዮችን በበላይነት የመምራትና የመቆጣጠር ኃላፊነት የኢትዮጵያ መንግሥት ብቻ ነው ግዴታም አለበት፡፡ ከዚያ ውጪ የሚመጣ አካል የኢትዮጵያን ሉአላዊነት በግልጽ የሚዳፈርና የሕዝቦችንም ነፃነት የሚጋፋ ነው፡፡

የአንዳንድ የውጭ ኃይሎች ተላላኪ ሆኖ የቆየው አሸባሪው ትህነግ በስልጣን በቆየባቸው ጊዜያት ከኢትዮጵያውያን ፍላጎት ይልቅ የውጭ ኃይሎች ፍላጎት አስፈጻሚ ሆኖ ቆይቷል፡፡ የአድዋ ድል በፈጠረባቸው የሞራል ስብራት ምክንያት ኢትዮጵያ የሚለው ስም የሚያርዳቸው የውጭ ኃይሎች የኢትዮጵያን የነፃነት ተጋድሎ ለማኮሰስ በተላላኪያቸው ትህነግ አማካኝነት በርካታ ሴራዎችን ሲሠሩ ቆይተዋል፡፡ ኢትዮጵያ የሚለው ስም በመገኛኛ ብዙኃን ጭምር እንዳይጠራ ከማድረግ ባለፈ አገሪቱን በተለያዩ ልዩነቶች በመከፋፈልና በማናቆር በሂደት ኢትዮጵያ ተዳክማ እንድትበታተን በብርቱ ሲሠሩ ቆይተዋል፡፡

ሆኖም የኢትዮጵያ ሕዝብ በከፈለው መስዋዕትነት አሸባሪው ቡድንን ከስልጣኑ በማስወገድ የኢትዮጵያን አንድነትና ከፍታ ያረጋግጥልናል ያሉትን መንግሥት በቦታው አኑረዋል፡፡ ከውጭ ኃይሎች ፍላጎት ይልቅ የኢትዮጵያንን መሻት የሚያስቀድም አመራር ዛሬ መንግሥታዊ ኃላፊነቱን ወስዶ ጠንካራና የበለጸገች ኢትዮጵያን ለመገንባት ጥረት ጀምሯል፡፡ ይህ ደግሞ የኢትዮጵያን መበታተን ለሚፈልጉ ኃይሎች አስደንጋጭ ክስተት ነው፡፡

አገርን ለውጭ ጠላቶች አሳልፎ ለመስጠት እና ኢትዮጵያን ብዙ ቦታ በመበታተን ደካማ የአፍሪካ ቀንድ አገራትን ለመፍጠር የሚፈልጉ አገራትን ዓላማ ለማስፈጸም እንደ ተጋላቢ ፈረስ ሆኖ እያገለገለ ያለው አሸባሪው ትህነግ ዛሬ ጀንበሩ እየጠለቀች ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ያስደነገጣቸው አንዳንድ የውጭ ኃይሎች፣ አገራትና ተቋማት ግልጽ የሆነ ዘመቻ ኢትዮጵያ ላይ ከፍተዋል፡፡ የሽብር ቡድኑን ከመቃብር ለማውጣት ዘርፈ ብዙ ዘመቻዎችን ከፍተዋል፡፡ በሰብዓዊ መብት ሰበብ የኢትዮጵያን ነፃነትና ሉአላዊነት ለመዳፈር ዳር ዳር እያሉ ነው፡፡

ሆኖም የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት በሉአላዊነታቸው ላይ የሚደራደሩ ባለመሆናቸው ለየትኛውም ጣልቃ ገብነትና ማስፈራራት በር የሚከፍቱ አይደሉም፡፡ አንዳንድ የውጭ ኃይሎች፣ አገራትና ተቋማት የሽብር ቡድኑን ከመክሰም ለማዳን በከፋ መልኩ በኢትዮጵያ ላይ ያልተረጋገጡና ፖለቲካዊ ዓላማ ያላቸውን ውንጀላዎች ቢያደርጉም ኢትዮጵያ በሀሰት ፕሮፖጋንዳ የሚዝል ክንድ የላትም ፡፡

ስለሆነም ኢትዮጵያ እየተከተለችው ካለችው የሰላም አማራጭ ውጪ አሸባሪ ቡድኑን ለማዳን የሚደረገው ጥረት ከንቱ መሆኑን በመረዳት በዚሁ ተገቢ ያልሆነ ተግባር ላይ የተሰማሩ አገራት፣ ተቋማትና መገናኛ ብዙኃን ከሚያደርጉት ያልተገባ ጫናና ጣልቃ ገብነት እራሳቸውን ሊያቅቡ ይገባል፡፡ የኢትዮጵያን ሰላም፤ ልማትና ሉአላዊነት የማስከበር ብቸኛ ኃላፊነትም የኢትዮጵያ መንግሥት ብቻ ነው!

ኢፕድ

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

**ነፃ ሃሳብ**

**ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡**

## ግርግሩ ሕዝብን ከአሸባሪዎች ለመታደግ ወይስ የአሸባሪዎችን እስትንፋስ ለማስቀጠል

ሜላት ኢያሱ

አንዳንድ ምእራባውያን ሀገራት የአሸባሪው የትህነግ እስትንፋስ እንዳይቋረጥ የእርቅና ድርድር ድራማ ከመሥራታቸው በፊት ፌደራል መንግሥቱ ከልቡ አለመግባባቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ብርቱ ጥረት አድርጓል። የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት አባቶች እና የሰላም አምባሳደር እናቶች መቀሌ ድረስ በመሄድ ስለሰላም እንባ እያነቡ ተማጽነዋል። ሌላው ቀርቶ መንግሥት የአሸባሪው ትህነግ አባላት ስልጣን ላይ በነበሩ ጊዜ ስለፈጸሙት ወንጀል እና ስለዘረፉት ሀብት ተጠያቂ ሳይሆኑ በሰላም ብቻ እንዲኖሩ እድል ሰጥቷቸዋል።

አሸባሪው የትህነግ ቡድን ሰላማዊ ውይይትና ድርድር የማድረግ ፍላጎት ቢኖረው ኖሮ እነዚህን ወርቃማ ሀገር በቀል እድሎች አሻፈረኝ ብሎ በባዕዳን መዳፕት ባልፈለገ ነበር። ለነገሩ አሸባሪው የትህነግ ቡድን ከሀገሩ ሽምጋዮች ይልቅ ባእዳን ላይ ተስፋ የጣለው እስትንፋስ ዘርተው ወደ ዙፋኑ እንዲመልሱት በማሰብ ነው።

ቡድኑ እና ሀገራቱ የእከክልኝ ልከክልህ ቃልኪዳን የተግባቡት ወያኔ የደርግ መንግሥትን ለመጣል የትጥቅ ትግል ከጀመረ ጊዜ አንስቶ ነው። በወቅቱ የደርግ መንግሥት የሶሻሊስት ርዕዮተዓለም ተከታይ ሆኖ የአሜሪካ ባላንጣ ከሆነችው ሶቬየትህብረት ጋር በመወዳጀት የማርክሲስት ሌኒንስት ቲዎሪዎችን በኢትዮጵያ ለመተግበር መሞከሩ ምእራቡን አለም በተለይም አሜሪካንን አስቀይሟታል።

ሀገራቱ /በተለይም አሜሪካ በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ የጓጓችለትን ጥቅም ለማስጠበቅ ኢትዮጵያን በእጇ ማስገባት ህልሟ ስለነበር ዛሬ ጀርባዋን የሰጠችውን ሸአቢያን ጨምሮ ለወያኔ ታጣቂዎችና እና በሲያድባሬ ለሚመራው የሶማሊያ መንግሥት ድጋፍ እያደረገች የደርግ መንግሥትን አስወግዳ የእርሷን ፍላጎት የሚያስፈጽም ተላላኪ መንግሥት ለማቋቋም ለዓመታት ከኢትዮጵያ ጠላቶች ጋር ወግናለች።

እንዳሰበችውም የተለያዩ አሻጥሮችን በመሥራት የደርግ መንግሥትን አስወግዳ ጉዳይ የሚያስፈጽምላትን የማፊያ ቡድን ወደ ስልጣን በማምጣት ጥቅሟን እያረጋገጠችና በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ እንዲኖራት የምትፈልገውን የበላይነት የምታረጋግጥበትን ተስፋ አንግባ የመቀመጥ እድል አግኝታ ነበር።

ይሁንና በአስራ ሰባት ዓመት የወያኔ አገዛዝ ጫንቃው የቆሰለው የኢትዮጵያ ህዝብ የወሮ በላውን ሥርዓት ከትከሻው ላይ አሽቀንጥሮ በመጣል በአዲስ መንግሥት አዲስ የለውጥ ምእራፍ ሲጀምር በአንጻሩ አሜሪካ ያስቀመጠችው አሻንጉሊት መንግሥት በትረ ስልጣኑን መነጠቁን ተከትሎ ጥቅሟ ሲከስምና ተስፋዋ ሲጨልም እጇን ሰብስባ መቀመጥ አልፈለገችም። ብዙኋኑን ትታ በጣት ከሚቆጠሩ ወንበዴዎች ጋር የማሸርፈገዷ ምስጢርም ይሄው ነው።

ወትሮም የፀረ ሽብር ህግ አውጥታ በአሸባሪነት የፈረጀቻቸውን ቡድኖችና ግለሰቦች ከምድረ ገጽ ለማጥፋት ተኝታ የማታድረው አሜሪካ የኢትዮጵያ መንግሥት በአሸባሪነት የፈረጀውን ቡድን እንደ እንቁላል ስትንከባከበው ሲታይ ከአሸባሪው ትህነግ ጋር ያላት የጥቅም ትስስር እና ቃልኪዳን ምን ያህል ጠንካራ እንደሆነ መገመት አይከብድም።

የአሸባሪው ትህነግ አመራሮች በሞኖፖል የያዙትን ስልጣን መልቀቃቸውን ሲያረጋግጡና መቀሌ ላይ ተሰባስበው ተመልሰው ወደ ስልጣን የሚመጡበትን ሴራ ሲዶልቱ አሜሪካን አጋራቸውና ምስጢረኛቸው አድርገው ነው። መቀሌ ቁጭ ብለው ከተላላኪዎቻቸውና ከጥቅም ተጋሪዎቻቸው ጋር እየተመሳጠሩ በመላ ሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ቀውሶች እንዲፈጠሩ የሚያደርጉት በአሜሪካና የአሜሪካን ዓላማ በሚያራምዱ ምእራባውያን አይዟችሁ ባይነት ነው።

አሸባሪው የትህነግ ቡድን ከስልጣን የተወገደው የኢትዮጵያ ህዝብ ጫንቃው ላይ የተጫነበትን የጭቆና ፣ የብዝበዛና የዘረኝነት ቀንበር አሽንቀንጥሮ ለመጣል በማሰብ እንጂ ይህን ያህል የአሜሪካና የቡድኑን ጥቅማዊ ተስስር ተረድቶ አልነበረም። አሁን ግን አሜሪካና ምእራባውያኑ ለአሸባሪው ብድን የመወገናቸው ምስጢር ቁልጭ ብሎ ታይቶታል።

ቡድኑ ከተጠያቂነት ለማምለጥ እና በትግራይ ህዝብ ጉያ ውስጥ ለመሸጎጥ ሲል «ትግራዋይ ጠል አስተዳደር በመስፈኑ ተገፍተናል» የሚል ፕሮፓጋንዳ እየነዛ በአንድ በኩል ፌደራል መንግሥቱ አቅም እንዳይኖረው በሁሉም ዘርፍ የማዳከምና ሀገር እንዳይረጋጋ የማድረግ ሥራ ሲሠራ በሌላ በኩል ደግሞ የትግራይ ህዝብን በተለይም ወጣቱን ሀሰተኛ ፕሮፓጋንዳ እየጋተ የሚቃጣብህን ጥቃት ትመክታለህ በሚል እየደለለ ወታደራዊ ስልጠና ሲሰጥ አሜሪካና አጋሮቿ በይፋም በህቡእም ይደግፉት እንደነበር ዓለም የሚያውቀው ጉዳይ ነው።

ቡድኑ ከምርጫ ቦርድ እውቅና ውጭ በእንቢተኝነት ምርጫ ሲያካሂድ፤ የሰሜን እዝ ወታደር ላይ ጥቃት ሲፈጽም፤ በአማራና በአፋር ክልል በንጹኋን ዜጎች ላይ ሰቆቃ ሲያደርስ፤ እድሜያቸው ለውትድርና ያልደረሰ ህጻናትን እያስታጠቀ ለጦርነት ሲያሰልፍ ፤ ተወንጫፊ ሮኬቶችን ወደ ጎረቤት ሀገራት እና ሰላማዊ ሰው ወደሚኖርባቸው ትልልቅ ከተሞች ሲተኩስ፣ የእርዳታ እህል ጭነው የገቡ ተሽከርካሪዎችን ለወታደራዊ አገልግሎት ሲያውል፣ የእርዳታ መጋዘኖችን ሲዘርፍ፣ የጤናና የትምህርት መሰረተ ልማቶችን ሲያወድም የአሜሪካ መንግሥትም ይሁን የእርሱን ዓላማ የሚያራምዱ ምዕራባውያን ትንፍሽ ማለት አልፈለጉም። እንደውም አሸባሪው ትህነግ ሰብአዊና ቁሳዊ ውድመቶችን እያደረገ ወደ አማራና አፋር ክልል ሲያስፋፋ ምእራባውያኑ እያንቆለጳጰሱና እያጀገኑ ያወሩለታል።

የትህነግ አመራሮች በሁለተኛው ዙር ወረራቸው ገና የደቡብ ወሎ ዋና ከተማ የሆነችውን ደሴን ሲቆጣጠሩ የተናገሩትን እናስታውስ፤ ጀነራል ጻድቃን «ጦርነቱን ጨርሰናል፤ ከማን ጋር ነው የምንደራደረው? መደራደር አያስፈልገንም፤ እያሉ ሲመጻደቁ ሰምተናቸዋል» አሁንም እኮ መንግሥት ጦርነቱን ጨርሶታል ለምን ከወንበዴ ጋር መደራደር ይፈልጋል የሚል አይጠፋም።

ትህነግ ወሰኑን እያሰፋ ወደመሃል ሲገሰግስ የተባበሩት መንግስታት ድርጅትም ይሁን ምእራባውያንባለበት እንዲቆምና ድርድር እንዲያደርግ ጫና ሲፈጥሩ አልታየም። እንደውም እንደቢቢሲ፣ አልጀዚራና ሲኤን ኤንን የመሳሰሉት ሚዲያዎቻቸው ትህነግ በመቀሌ ከተማ አቅራቢያ ሲያደርግ የነበረውን እንቅስቃሴ በቪዲዮ እያሳዩ ልክ የአዲስ አበባ ከተማ በትህነግ ታጣቂዎች በከበባ ውስጥ እንዳለች በመግለጽ ህዝቡን ተስፋ ለማስቆረጥ ይጥሩ ነበር።

ዜጎቻቸው አዲስ አበባ ከተማን ለቅቀው እንዲወጡ በተለያዩ ጊዜያት ማሳሰቢያ ይሰጡ እንደነበር የምናስታውሰው ነው። ይህም ብቻ አይደለም የመንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣናትም ጥገኝነት የሚፈልጉ ከሆነ ሊያሰጧቸው እንደሚችሉ ጭምር የማግባባት ሥራዎችን ይሠሩ እንደነበር ከጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ አንደበት የሰማነው እውነታ ነው።

የእነርሱ ምኞት በህዝብ የተመረጠውን እና የኢትዮጵያን ጥቅም አሳልፎ ሊሰጣቸው የማይችለውን መንግሥት ከስልጣን አውርዶ ጥቅማቸውን የሚያረጋግጥላቸውን የትህነግ አሸባሪ ቡድን ወደ ስልጣን ማምጣት ስለሆነ ቡድኑን በተለያየ መንገድ ቢደግፉት ሊገርመን አይገባም።

ጦርነቱን ተከትሎ በሁለቱም ወገን በኩል የሚደርሰው ሰብዓዊና ቁሳዊ ጉዳት የሀገር ጉዳትነው በሚል መንግሥት ሆደ ሰፊ ሆኖ ትንሽ ርምጃውን ገታ ሲያደርግ አሸባሪው ትህነግ በበኩሉ የጦርነት ነጋሪቱን እየጎሰመ፣ ዘገሩን እየሰበቀ፣ ሰላማዊ ሰዎችን እየጨፈጨፈና መሰረተ ልማቶችን እያወደመ ወሰኑን አስፍቶ መቆሚያዬ አራትኪሎ ነው ሲል ምእራባውያኑም ሆኑ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ያበረታቱታል እንጂ አያወግዙትም።

አሸባሪው ትህነግ ድል የቀናው ሲመስለው እንደአንበሳ እያገሳ ዓለምን ያናውጣል፤ ያኔ ወዳጆቹ ጮቤ እየረገጡ ገድሉን ያወሩለታል፤ የሚደፈሩት ህጻናትና ወይዛዝርት፣ በግፍ የሚጨፈጨፉት ንጽኋን ጉዳይ ምናቸውም አይደለም። እነርሱ ህልማቸው አሻባሪውን የትህነግ ቡድን ወደ መንበረ ስልጣኑ መልሰው በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ያላቸውን ጥቅም ማስከበር ነው።

መንግሥት ርምጃውን ጠንከር ሲያደርግና በመረጡት ቋንቋ እያነጋገረ ሕግ የማስከበር ርምጃ መውሰድ ሲጀምር ደግሞ ጦረኛ ነኝ፣ ማንም አይደፍረኝም ፣ አንበሳነኝ ሲል የነበረው የወንበዴዎች ስብስብ ወዲያው ድመት ሆኖ እናገኘዋለን። የአሳዳሪዋን እግር እየላሰች ቁራሽ እንደምትለምን ድመት ሚያው... ሚያው... እያለ የጣረሞትና የድረሱልኝ ደምጽ ያሰማል። ይህን ጊዜ ወዳጆቹ ነፍሱ ከመውጣቷ በፊት ሊያድኑት ይሯሯጣሉ። አሁን በእርቅ ስም እያደረጉ ያለውም ይህንን ነው። እርቅ ፣ድርድር ፣ ሰላማዊ ውይይት የሚታያቸው መንግሥት በአሸባሪው ትህነግ ላይ የሚወስደው ርምጃ ሲበረታና የትግራይ ህዝብ በተለይም የትግራይ እናቶች እፎይ የሚሉበት ጊዜ ሲቃረብ ነው።

ለአሸባሪው የትህነግ ቡድን የችግሮች ሁሉ መውጫ መንገድ ጦርነትን ነው። ጦርነትን ልዩ መገለጫው /ብራንዱ / አድርጎ ወጣቱን እያነሳሳ ሲፈልግም እያስገደደ ወደ እሳት በመማገድ በርካታ ወላጆችን የወላድ መካን አድርጓቸዋል። ኢትዮጵያውያን በተለይም የትግራይ እናቶች ዘላቂ ሰላም የሚወርድላቸው ደቡብ አፍሪካ ላይ በተጀመረው ድርድር ቡድኑ ትጥቅ መፍታት ሲችል ፤ የቡድኑ አመራሮችም በትግራ ህዝብ ሆነ በማላው ህዝባችን ላይ ለፈጸሙት መንጀል ለፍርድ ሲቀርቡ ነው ። ድል ለመከላከያ ሠራዊታችን።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## ፋሽን- ሰው የወደደው ገበያ የለመደው

**ኃይለማርያም ወንድሙ**



በዓለማችን በአብዛኛው ለሰው ልጅ ልብስ መልበስ ሰብዓዊ፣ ሞራላዊና መንፈሳዊ ግዴታው ነው፡፡ አዳምና ሔዋንን ዕጸ በለስ አትብሉ የተባለውን ትዕዛዝ ሲጥሱ ዕርቃናቸውን መሆናቸው ታወቃቸው፤ ተፋፈሩ የበለስ ቅጠል ቀነጣጥሰው ለራሳቸው ግልድም አደረጉ፡፡ እነሆ ከዚያም በኋላ ልብስ ለሰው ልጆች ገበና ሸፋኝ ብቻ ሳይሆን ጤንነቱን የሚጠብቅበት፣ ብርድንና ሙቀትን ወይም የፀሀይ ሐሩርን የሚከላከልበት፣ ባህልና እምነቱን የሚገልፅበት ማጌጫው ጭምር ሆነ፡፡

ይህን ፅሁፍ ለማዘጋጀት ያነጋገርናቸው በፋሽን ዘርፍ የተሰማሩ ባለሙያዎች፤ ‹‹ፋሽን ሰው የወደደው፣ ገበያ የለመደው ወይም የሚስበው መገልገያ ቁሳቁስ፣ ልብስ እና ጌጣጌጥን የመሳሰሉትን ያካትታል›› ይላሉ፡፡ በሰዎች ቅቡል፣ ተመራጭና ተወዳጅ የሆነውን ዓይተው ደጋግመው የሚያመርቱትንና ለገበያ የሚያቀርቡትን ‹ፋሽን› እንደሚሉትም ይናገራሉ፡፡ ስለተሠራ ሳይሆን ሥራውን ሰው ሲወደው እና ሲለምደው ከዚያም በብዛት ሲገለገልበት ፋሽን ተብሎ ይታሰባል፡፡

‹‹የፋሽን ኢንደስትሪ በአገራችን ከውጪዎች ጋር ሲነፃፀር በዘርፉ ገና ጅማሮ ላይ ነን›› የሚሉ የዘርፉ ባለሙያዎች የፋሽን አልባሳትን የሚሰሩት በቅብብሎሽ ነው፡፡ አንድ ፋሽን ተሰርቶ ይወጣና ከ20 እስከ 30 ሺ ልብስ ይሠራና ለሽያጭ ይቀርባል፡፡ በብዛት ገበያው ሲቀበለውም ፋሽን ይሆናል፡፡

የፋሽን ንድፍ ወይም ዲዛይን ብዙውን ጊዜ አልባሳትን ከመስፋት፣ ለመዋቢያ የሚሆኑ ቁሶችን ከመቀመር፣ ከማዋቀር ፤ ከመሥራትና ለአገልግሎት ከማብቃት የዘለለ ሚና አለው፡፡ ዲዛይን በራሱ ሰገላዊ ጥበብ (scientific art) የሚታይበት ታስቦና ታልሞ የሚከወን መሆኑንበዘርፉ ባለሙያ የሆኑት ዴቪድ ካርሰን ያስረዳሉ ፡፡ ክንውኑ የታለሙ ዕሳቤዎችን ኪንን ቀምሮ የሚያካትት ነውም ይላሉ፡፡

የፋሽን ንድፍ ሰባት አላባውያን (elements) አሉት የሚሉት ዴቪድ ካርሰን ፤ እነዚህም የማንኛውም ዕይታ ንድፍ መሠረታዊ የአሠራር ዓይነቶችን የሚያካትቱ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ፋሽንና ንድፍ ሰባት አላባውያን ማለትም ቀለም፣ ቦታ /ስፋት/፣ ቅርፅ፣ መስመር / ሥሪት ወይም ዓይነት/ ዕሴትና ጥራትን ያካትታሉ ሲሉ ያስቀምጣሉ፡፡

ቀለም፣ስፋት፣ ቅርፅ፣ መስመር /ሥሪት ወይም ዓይነት/፣ ዕሴትና ጥራት የፋሽን ሥራው ንድፍ ወይም ዲዛይን በቀላሉ በሰው ዕይታ ውስጥ እንዲገባ የሚረዱ ናቸው፡፡ ዲዛይን ወይም ንድፍ ለፋሽን መሠረታዊ፤ በጣም ጠቃሚ ወይም ዋጋ እንዲኖረው የሚያግዝ ሲሆን ትኩረት የሚጭሩ እና ዕሴት የሚጨምሩ ጥበቦችም ያሉበት መሆኑን በጽሑፋቸው አስቀምጠዋል፡፡

ለዚህም ግራፊክ ዲዛይነሮች የጠቀስናቸውን የንድፍ አላባውያንን በማካተት ምስል ከሳች ሆኖ የተወሰነ ስሜት የሚፈጥር ፣ዐይንን በውስን አቅጣጫ የሚያጥር (የሚከት) ወይም በርካታ ስሜቶች የሚያጭር የፋሽን ዲዛይኖችን ይሠራል፡፡ እነዚህም የፋሽን ንድፍ አላባውያን ማንኛውም ከሳች ምስሎች የሚፈጥሩ፣ ለንድፍ አውጪዎችም በንድፍ መርሆዎች ላይ እንዲያተኩሩ የሚረዱ ናቸው፡፡በዚህም በንድፍ አላባውያን ላይ ተመሥርተው የሚሠሩ የንድፍ ባለሙያዎች ለዓይን ደስ የሚል መልክና ቅንብር የሚፈጥሩ ናቸው፡፡

ገፃዊ ዕይታ አሠራር (graphic design) ማንኛውም ምስላዊ የጥበብ ፈጠራ ሥራ ከግምት በመከተት የሚከወን ሲሆን ውስጣዊ ንድፍም ፣ አርማ ፣ማስታወቂያ ወይም የዘመናችን መረብ ዲዛይን (web design) ሚና ያለበት ነው፡፡

ቀለም ለፋሽን ንድፍ ቅንብር ስሜት የሚጭር ነው፡፡ የብርሃን ሞገዶች በአንድ ቁሳዊ ነገር ላይ ሲረጩና ተንፀባርቀው ሲመለሱ በሰው ዓይን (ኦፕቲክ ነርቭ) ላይ ስሜት ይፈጥራሉ፡፡ ይህም ቀለም የሚባለውን ወሳኝ ነገር ይከሰታል፡፡ የጥበብና የንድፍ ባለሙያዎች ቀለምን የሚጠቀሙት የፋሽን ሥራው፤ ዕይታው ውስጥ እንዲገባና እንዲገለፅ (እንዲነገር) ነው፡፡ቀለምን የንድፍ ባለሙያዎች ስሜትን ፣ ብርሃንን ፣ ጥልቀትን እና ዕይታን ሰዎችን ለመሳብ ለመማረክ ይመርጡታል።ይህም በቀለም ንድፈ ሀሳብ ተመርኩዘው የሚሠሩት ነው፡፡ ይህም ቀለሞችን በመቀላቀል ፣በማዋሃድ እና በማቀናበር - የቀለም ንድፎችን ለመፍጠር የሚረዳ ነው፡፡

መስመር ሁለት ነቁጥ (ነጥብ) የሚገናኙበት ነው፡፡ አግድማዊ፣ ሰያፍና ፣ ሽቅባዊ መስመሮች ዓይንን ወደ ተወሰነ አቅጣጫ የሚወስዱ ቅንብሮች ናቸው፡፡ በዚህም በተለያዩ መስመሮች መስተጋብር ውህደት የሚስብ ከቀጥታ መስመር ባለፈ ያማረ ጥለት ይፈጥራሉ፡፡

በንድፍ ሥራ ውስጥ ዕሴት የሚያመላክተው የፋሽን ሥራውን ብርማ (ብሩህ) እና ጸሊም ቀለማትን ነው፡፡ የቀለም ዕሴት በብዛት ቀስ በቀስ የሚከሰት ነው፡፡ የእዚህም ማሳያዎች በአንድ ቀለም ላይ ያሉ ልዩነቶችን ከቅለት እስከ ክቡድ ጽልመት የተደረደሩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ አርቲስቶች የተለያዩ የቀለም ዓይነቶችን ይጠቀማሉ፤ይህም ብዙዎችን ለማስደመምና ሥራቸው እንዲሰምርላቸውና እንዲነገርላቸው ገበያ እንዲስብላቸው ብሎም ተወዳጅነት እንዲፈጥርላቸው ነው፡፡

ሌላው ስፋት እና ቦታ የሚባለው የታሰበ የፋሽን ንድፍ ሥራን ሌሎች እንዲያዩት የሚጋብዝ ነው፡፡ አዎንታዊ ቦታ በንድፍ ቅንብር ውስጥ የሚወስደው ቦታ ነው።ቅርጽ በጣም መሠረታዊ ሆኖ ቁመትና ዓይነት የሚገለጽበት ነው፡፡ በንድፍ የታጀበ ሁለት ልኬታዊ ቦታ ነው፡፡የግራፊክ ዲዛይን ባለሙያዎች የሚጠቀሙበት መስመር፣ ቀለም፣ ዕሴትን በማካተት በሦስት አቅጣጫዊ ቅርጽ ሰዎች ቀልባቸውን እንዲስብ የሚያደርግ ነው፡፡

በሚሊተሪ ተራ ልብስ ሲገበያዩ ያገኘናቸው ወይዘሪት ለምለም ገብረእግዚአብሔር፤ ፋሽን ተከታይ ሲሆኑ የአልባሳት ምርጫቸው ላይ ቀለም እና ስፌት ላይ ያተኮረ መሆኑን ይናገራሉ፡፡ ስፌቱን መርጠው ለልብስ ሠፊ እንደሚሰጡና፤ ጊዜው ያለፈባቸው አልባሳታቸውን በብዛት ለታረዙ እንደሚሰጡ አጫውተውናል፡፡

በተመሳሳይ መገበያያ ስፍራ ያገኘናት ከድጃ ሁሴንም ምርጫዋ ቀለም ላይና ስፌት ላይ ቢሆንም ከእምነቷ ጋር በማይፃረር መልኩ ረጃጅም ቀሚሶችንና የሚዛመዱ ሻሾችን አሠርታ እንደምትጠቀም ትናገራለች፡፡ የጨርቅ ምርጫዋ በቀልም ላይ የተወሰነ ቢሆንም ተማሪ ሀቢባ ሳሊም ልዩ ልዩ ምስል ያለባቸውን ጨርቆች እንደምትመርጥና በተለይ ቁመቷ አጭር በመሆኑ፤ ከላይ ወደ ታች መስመር ያለባቸው አልባሳትን እንደምታስቀድም ጠቁማለች፡፡ ይህም ከላይ የጠቀስነው ፋሽን ሰው የወደደው ገበያ የለመደው ቁስ እና ልብስ ነው ለሚለው ማሳያ ነው፡፡

# ትዝብት/ ማረፊያ

## የእገታ ነገር

**አቤል ገ/ኪዳን**

አንዳንዴ የእኛ ነገር ያናድዳል።ዓለም ከሚሄድበት አቅጣጫ በተቃራኒው መጓዝን ፋሽን አድርገነዋል። ዓለም እየተጋገዘ እና እየተደራጀ ከአመት አመት አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ሲፈጥር እና ህይወቱን ሲያሻሽል እኛ ግን በተቃራኒው እየተደራጀን አንዳችን አንዳችንን ለማጥፋት ስንለፋ እንውላለን። ያሳፍራል። አሁን ደግሞ አዲስ የመጣው ፋሽን ሰውን ማገት እና ገንዘብ መጠየቅ ነው። አስገራሚ ነው።እንዲህ አይነት ሀሳብ እንደ ስራ ፈጠራ እና እንደ ገቢ ምንጭ አድርጎ ማሰብ አሳዛኝ ክስተት ነው።

ይህን ያልኩት የሰሞኑ የህጻን ሳሙኤል እገታ ነው።ለ11 ቀናት የቆየው እገታ በፖሊስ ጥንቃቄ የተሞላው እንቅስቃሴ መጨረሻውን አግኝቷል።አሁን ላይ ህጻኑ ወደ እናቱ እቅፍ ተመልሷል። አስገራሚው ነገር ግን በአንድ ሰራተኛ ብቻ ተፈጽሟል ብለን ያሰብነው ወንጀል ለካስ በተቀናጀ መልኩ ሶስት ሰዎች በጋራ የፈጸሙት እና ለረዥም ጊዜ ያቀዱት መሆኑ ነው።ያስገርማል።ሰው እንዴት የሰው ልጅ አግቼ ገንዘብ አገኛለሁ ብሎ ያቅዳል።ይሄ እኮ እንኳን ሊታቀድ በህልም እንኳን ሊታይ የሚገባው ነገር አልነበረም።

እዚህ ጋር የምስራቅ ጎጃም ዞን ስለ ወንጀሉ አፈጻጸም ያሰፈረውን መረጃ እናንብብ.... “የእገታ ወንጀሉን ያቀነባበረው ብሩክ/አማረ ቸኮል የተባለ እና አዲስ አበባ ውስጥ በቀን ስራ የሚተዳደር ግለሰብ ሲሆን ፤ለዚህ ሀሳብ መነሻ የሆነውም መርጌታ ሚስጥሩ ይግዛው የተባለ የስጋ ዘመዱ ከምዕራብ ጎጃም ደጋዳሞት ወረዳ ለስራ ፍለጋ ወደ አዲስ አበባ ይሄድና ከብሩክ/ አማረ ቸኮል ጋር ተገናኝቶ ስራ እያፈላለገ ለተወሰነ ጊዜ አብረው ይቆያሉ።

ከዚያም መርጌታ ያሰበውን ስራ ማግኘት አልሳካለት ሲል ስራ ጠፋ ወደ አገሬ ልመለስ ነው ብሎ ብሩክን ሲያማክረው ፤ ለምን አንድ የሀብታም ልጅ የሆነ ህፃን አግተን ብር አንቀበልምና አያልፍልንም ይለዋል ፤ መርጌታ ሚስጥሩም እንዴት አርገን በምን መልኩ ማገትና ገንዘብ መቀበል እንችላለን ሲለው ፤ቀላል ነው ከጎንደር ወይም ከጎጃም አካባቢ መጥታ አዲስ አበባ ሀብታም ቤት ውስጥ የገባች ሰራተኛ ካገኘህ አፈላልግና እሷን አግኝተን በማሳመን ህጻን ይዛ እንድትጠፋ ካደረግን በኋላ ህጻኑን ደብቀን ከቤተሰቡ ብር ተቀብለን እንለቀዋለን በሚል ይመካከሩና ይስማማሉ ፤

በስምምነታቸው መሰረትም መርጌታ ሚስጥሩ ወደ ባህርዳር ተመልሶ በፊት የሚያውቀውን አንድ ጓደኛውን አግኝቶ ሀሳቡን ግልጽ ሳያደርግ አዲስ አበባ ሀብታም ቤት ውስጥ የገባች የቤት ሰራተኛ የሚያውቃት ካለች እንዲያስተዋውቀው ወይም እንዲያፈላልግለት ይጠይቀዋል ፤ይህ የባህርዳሩ ጓደኛውም ህጻኑን ሰርቃ የተሰወረችውን ውዴን ቀድሞ ያውቃት ስለነበር ያስተዋውቀውና ስልክ እንዲለዋወጡ ያደርጋል ፤ በመቀጠል መርጌታ ሚስጥሩ ወደ አዲስ አበባ በመመለስ ከመጀመሪያው ሀሳብ አመንጭ ከብሩክ ጋር በመሆን ውዴ ላይ ይደውሉና ተቀጣጥረው መርካቶ አካባቢ አግኝተዋት ተዋውቀው የተወሰነ ከተጫወቱ በኋላ ሀሳቡን ሲነግሯት ለጊዜው ፍቃደኛ አልሆንላቸው ስትል በተለያየ መንገድ ጀንጅነው ያሳምኗታል ፤ውዴ በሀሳቡ ከተስማማች በኋላ አሁን ካለሁበት ቤት በፊት የነበርኩበት ቤት ስለሚሻል ተመልሼ ከበፊቱ ቤት ልግባና ህጻንም ስላለ እሱን ብናወጣ ይሻላል በሚል ተስማምተው ቀደም ሲል ከወጣችበት ቤት ተመልሳ በመግባት በንግግራቸው መሰረት ጥቅምት 6ቀን 2015 ዓ/ም ህጻን ሳሙየል ዩሀንስን አታላ ከቤት ይዛ ትሰወራለች ።”

እንግዲህ ከዚህ የምንረዳው ነገር የአንዳንድ ሰዎች አእምሮ ምን ያህል የተበላሸ እንደሆነ ነው።ስራ ጠፋ ሲባል ለምን ልጅ አናግትም የሚል ፤ ያለማቅማማት የሚስማማ፤ ከመስማማትም አልፋ የክፋት ሀሳብ የምታመነጭ ሴት እነዚህ ሁሉ አንድ ላይ ሆነው የፈጸሙት አስደናቂ ወንጀል ነው።ይህ ነጠላ ክስተት አይደለም።ሌሎችም እንዲህ አይነት ታሪኮች በቅርቡ በተደጋጋሚ እየሰማን ነው።ለምሳሌ ያህል በመተማ ወረዳ ይህ አይነት ዜና በቀናት ልዩነት ውስጥ ሁለቴ ተሰምቷል።የመተማ ፖሊስ የፌስቡክ ሁለቱን ታሪኮች እንደሚከተለው ይገልጻቸዋል።

የመጀመሪያው እነሆ በምዕራብ ጎንደር ዞን በመተማ ወረዳ በመቃ ቀበሌ ላይ የእገታ ወንጀል የፈፀመ ግለሰብ በፅኑ እሰራት መቀጣቱን የልዩልዩ ወንጀል መርማሪ ንዑስ ክፍል ሀላፊ ሳጅን መሀመድ ሁሴን ገለፁ።ለክፍላችን ለመተማ ወረዳ ፓሊሰ የመንግሰት ኮሚዩኒኬሽንና ሚዲያ ክፍል እንደገለፁት ተከሳሽ ጌታሁን እያየ የተባለው ካልተያዙ 3 ግብረአበሮቹ ጋር በመሆን መስከረም 27ቀን 2015ዓ.ም መተማ ወረዳ መቃ ቀበሌ ወይን አንባ ከተባለው ልዩ ቦታው ከቀኑበግምት 11:00 ሰዐት ሲሆን የግል ተበዳይ አበራ መኮነንን አግተው በመውሰድ 800,000(ሰምንት መቶ ሽህ ብር) ጠይቀው ለ4ቀናት ያህል ካቆዩ በኃላ ከቤተሰቦቹ ጋር ተደራድረው 400,000(አራት መቶ ሽህ ብር) በማስከፈል ጥቅምት 1ቀን 2015ዓ.ም ሊለቁት ችለዋል። የመተማ ፖሊስ በኋላ ላይ ባደረገው ክትትል ተከሳሹን ከዘረፈው የተወሰነ ገንዘብ ጋር ይዞት አስፈርዶበታል ፤ የተገኘውንም ብር ለባለቤቱ መልሷል።

ሁለተኛው ታሪክ ደግሞ እንዲህ ይላል “በምዕራብ ጎንደር በመተማ ወረዳ በማጠቢያ ንዑሰ ወረዳ በተደጋጋሚ ማህበረሰቡን እያገቱ ያስመረሩ ግለሰቦች በፅኑ እሰራት መቀጣታቸውን የማጠቢያ ንዑሰ ወረዳ የታክቲክ ምርመራ ክፍል ሀላፊ ረ/ኢ/ር ጌታቸው አሰረሴ ገለፁ።”ይላል። ዘገባው እንደሚያስረዳው እነዚህኞቹ ደግሞ ሰፋ ያለ የማገት ልምድ ያላቸው ናቸው።የተወሰኑት ተይዘው ፍርድ ተቀብለዋል።

ሁሉም ታሪኮች የሚያሳዩን ይህ ነገር እንደ ልማድ እየተስፋፋ መምጣቱን ነው። በየቦታው ብናየው እንዲህ አይነት ብዙ ታሪክ መኖሩ አይቀርም። አግተው ገንዘብ ባይጠይቁ እንኳ አባብለው ሰውን ለሴተኛ አዳሪነት ፤ ለጉልበት ስራ እና መሰል ነገር የሚመለምሉ በዝተዋል።ሰው ተባብሮ ሰርቶ ራሱን እና ሀገሩን ይቀይራል እኛጋ ሰዎች የሚተባበሩት ለወንጀል ሆኗል።እንደቀልድ ልናየው አይገባም።ካሁኑ በጋራ ካልታገልን ነገ ከነዚህ ወንበዴዎች ሰለባዎች መሀከል እኛም ልንገኝ እንችላለን።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

## የሀገሬ —ብሔራዊ ፈተናዎች“

የሰሞኑ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ብሔራዊ ፈተና “ግሩም!” በሚባል ስኬት ተከናውኖ የተጠናቀቀው ከጥቂት ቀናት በፊት ነው። አዲስ ዓይነት አደረጃጀት፣ ሎጅስቲክና አተገባበር በተዋወቀበት በዚህ ዓመቱ ብሔራዊ ፈተና ላይ የመቀመጥ ዕድል ያጋጠማቸው ልጆቻችን ቁጥር ከዘጠኝ መቶ ሺህ በላይ እንደነበረ በኦፊሻል ሪፖርት ተረጋግጧል።

የአስተባባሪዎቹን፣ የፈታኝ መምህራኑን፣ የድጋፍ ሰጭ ባለሙያዎችን፣ የፀጥታ ክፍሉን ባልደረቦች፣ የየክልሎቹንና የየዩኒቨርሲቲዎቹን የሰው ኃይል ቁጥር አንድ ላይ እንደምር ካልንም በፈተናው ጅረት ውስጥ ያለፈው ሠራዊት በሚሊዮኖች የሚገመት እንደሚሆን ለማመን አይከብድም። ልጆቻችን የወረቀት ፈተናውን ሲወስዱ የተቀሩትና በመቶ ሺህዎች የሚቆጠሩት የዘረዘርናቸው ድጋፍ ሰጭዎች ደግሞ ችግሮች እንዳይፈጠሩና ፈተናው በሰላም እንዲጠናቀቅ በተግባርና በሃሳብ ሲፈተኑ መክረማቸው የሚዘነጋ አይደለም።

የፈተና ሥርዓቱን በተሳካ ሁኔታ የመሩትና ያስፈጸሙት የትምህርት ሚኒስቴር መ/ቤት፣ የፀጥታ አካላትና ባለ ድርሻ ተቋማት በሙሉ የአኩሪው ውጤት ተጋሪ ናቸውና ዘግይቶም ቢሆን ከግለሰብ ዜጎች ምሥጋናና አድናቆት ቢዥጎደጎድላቸው ዘግይቷል አያሰኝም። እንደ ወላጅም እንደ ዜጋም ለልጆቻችን ከፍታ የደከሙልንን ሁሉ ክብረት ይስጥልን እንላለን።

በማኅበራዊና በተፈጥሮ ሳይንሶች ተለይቶ የተሰጠው የዚህ ዓመቱ የብሔራዊ ፈተና መርሃ ግብር በስኬት ተጠናቋል ቢባልም መቶ በመቶ ከተግዳሮት ነፃ ነበር ማለት ግን አይደለም። በዚህ ርዕስ ሥር ደግመን የማንከልሳቸው የተወሰኑ ችግሮች አጋጥመው እንደነበር በሚመለከታቸው ተቋማት በኩል በግልጽነት ሲነገር ሰንብቷል። አዳዲስ አሠራሮችን ሁሌም ለመተግበር ሲሞከር ተገማችና ያልታሰቡ ተግዳሮቶች እንደሚገጥሙ የሚጠበቅ ነው። የችግሮቹን ዝርዝር ስፋት በተመለከተ የዋነኞቹ ተቋማት መሪዎች ሲገልጹ ስለሰነበቱ የተባለውን መልሰን በመድገም አንባብያንን ለማሰልቸት አንሞክርም።

ይህንን የመንደርደሪያ ሃሳብ የምንጀምረው በምሥጋና ብቻ ሳይሆን የሚኖረውን ታሪካዊ ፋይዳ በማስታወስ ጭምር ይሆናል። በዚህ ዓመት የተጀመረው አዲስ የብሔራዊ ፈተና አሰጣጥ ተሞክሮ በሀገራችን ታሪክ የመጀመሪያ የሚባልለት መሆኑ በራሱ ስኬት ይመስለናል። የውጤቱ አንድ አካል ሆኖ መቆጠሩ ብቻም ሳይሆን የወጣኞቹና አስፈጻሚዎቹ ግለሰቦችና ተቋማትም መልካም የታሪክ ተናጋሪዎች መሆናቸውን በመጠቆም ወደ ዋናው ሃሳባችን እንዘልቃለን።

**ፈተኛ ተፈታኝ፣**

የልጆቿ ብሔራዊ ፈተና ከጉልህ ሳንካ በጸዳ መልኩ በስኬት እንዲጠናቀቅ አንጡራ ሀብቷን ያለ ስስት ሆጨጭ አድርጋና መድባ ዜጎቿንና ተቋማቷን በገፍ በማንቀሳቀስ የልጆቿን ዕውቀት ስትመዝን የሰነበተችው ኢትዮጵያ እርሷ ራሷ በርካታ ብሔራዊ ፈተናዎችን በመጋፈጥ ላይ ያለችው ጥርሷን ነክሳ ስለመሆኑ በሚገባ ይታወቃል። የፈተናዋ ግዝፈትም ልጆቿ ከወሰዷቸው የትምህርት ዓይነቶችና ብዛት በእጅጉ የተወሳሰበ ባህርይ ያላቸው ናቸው።

እንደ ልጆቿ የአካዳሚክስ ፈተና የእርሷ ዘርፈ ብዙ ፈተናዎች በቀናት ዕድሜ ውስጥ ይጠናቀቃሉ ተብሎ አይጠበቅም። በቀላሉ ለማስረዳት እንዲቻል ወቅታዊውን የሀገሬን ዋና ዋናና ጉልህ የብሔራዊ ፈተና ዓይነቶች “ተፈጥሮና ማኅበራዊ” ተብለው ከተለዩት የተማሪዎቻችን የፈተና ምደባዎች ጋር ሙሉ ለሙሉ ባይመሳሰሉም እያቀራረብን ለማሳየት እንሞክራለን።

ሀ. የማሕበራዊው ዘርፍ ብሔራዊ ፈተናዎቿ፣

አሸባሪው ትህነግ በከፈታቸው ሦስት ያህል ጦርነቶች ምክንያት የሀገሪቱ ሕጋዊና ሥርዓታዊ መቀቅር በብዙ መልኩ መፈተኑ አሌ የሚባል አይደለም። በተለይም በቀዳሚነት የሚጠቀሰውና ቁጥሩ ይህን ያህል ይሆናል ተብሎ ለማግኘት የሚያዳግተው፣ ከዚህም ሆነ ከዚያ በጦርነቱ ምክንያት የሺህ ምንተ ሺህ ንጹሐን ዜጎችን ሕይወት መቀጠፉ ዋነኛው የወቅቱ የብሔራዊ ፈተናዋ ማሳያ ተደርጎ ሊቆጠር ይችላል።

ዛሬም ድረስ ከተፋላሚዎቹ ወገንና ከንጹሐን ዜጎች ሞቱ ይቀንስ ካልሆነ በስተቀር ሙሉ ለሙሉ ቆሟል ለማለት ያዳግታል። በአጭሩ ለማለት የሚቻለው አሸባሪው ቡድን በጦር ሜዳ እና እርሱ የሚጋልባቸው አጋሰስ የጫካ ቅልብተኞቹ በበቀልና በአኩይ የግፍ ተግባሮቻቸው በአንዳንድ ክልሎች ውስጥ እጃቸውን በንጹሐን ደም እየበከሉ መሆናቸው የሀገሪዊ ፈተናውን ውስብስብነት በግልጽ የሚያመላክት ነው።

በዕቡይና በአኩይ ባህርይ አገንግነው በንጹሃን ደም የሰከሩትና የባሩድ ሽታ ወደ አውሬነት የለወጣቸው ግፈኞቹ “የቀየን ወራሾች” የንጹሐንን ነፍስ ከመቅጠፍ ጎን ለጎን በቢሊዮኖች ብር የሚገመቱ የመንግሥትንና የግለሰቦችን ንብረት አውድመዋል፣ በወረራ በያዟቸው አካባቢዎችም በቀላሉ የማይጠግግ የሥነ ልቦና ቀውስ አድርሰዋል። ሕጻናትና አዛውንት እናቶችን ሳይቀር በጭካኔ ደፍረዋል፣ አዋርደዋል። ምናልባትም በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ እንዲህ ዓይነት ግፍ በአንድ ሀገር ክልል ውስጥ “ዜጎች” በሚባሉ አውሬዎች መፈጸሙ ታሪኩን ልዩ ሳያደርገው አይቀርም።

ከትግራይ እናቶች ጉያ ሥር ልጆቻቸውን በመንጠቅ የሚፈጽሙት የጭካኔ ግፍ አልበቃ ስላላቸውም የሕዝቡን አእምሮና ስሜት በውሸት ትርክትና ፕሮፓጋንዳ በክለዋል። በአንዳንድ ክልሎች “በነፃ አውጭ” ስም ባደራጇቸው ኢጋሰሶቻቸው አማካይነትም ብሔራቸው እየተለየና በራሳቸውም ወገኖች ሳይቀር የፈጸሙትንና እየተፈጸመ ያሉት ጭካኔ የተሞላባቸው ድርጊቶች መጠናቸውም ሆነ ዓይነታቸው ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለም። ደግመን እናስምርበትና ሀገሪቱ እየተፈተነችበት ያለው ውስብስቡ የብሔራዊ ፈተናዋ ቁስል ይህንንና ይህንን ይመስላል።

በጦርነቱ እየወደመ ያለው የገንዘብና የቁሳቁስ ሀብት፣ ሀገራዊው ኢኮኖሚ እንዳይረጋጋና እንዳይረጋ በጨለማ እየተፈጸመ ያለው የጎሳና ቢስ ዜጎች ሴራና ተንኮል ሌላው የማሕበራዊ ፈተናዋ አንዱ ተግዳሮት ነው። ገበያው ጨርቁን ጥሎ ማበዱ፣ የዕለት ጉርስ ለዜጎች ፈታኝ የሆነ ደረጃ ላይ መድረሱ፣ የኑሮ አቀበት ከፍታውን ጨምሮ በዜጎች አቅም የማይገፋ መሆኑ፣ በፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ የሚስተዋለው ዳተኝነትና መጓተት፣ በተለያዩ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ሕዝቡን ለእንባና ለምሬት የሚዳርጉት ዘርፈ ብዙ ብሔራዊ ፈተናዎችም ወዘተ. እጅግ ሥር የሰደዱ ናቸው።

በብሔርና በጎጥ ወይንም በአፍቃሬ ራስነት የታጠሩት የፖለቲካ ልክፍተኞች ያልሰከነ አይዲዮሎጂና ጥያቄ፣ “የማሕበራዊ አንቂ” የሚል ስያሜ ለራሳቸው በሰጡ ሳይሞቅ ፈላ “የዘመን እንኩሮዎች” እየተፈጸሙ ያሉት ሁከቶችና መዋከቦችም ዜጎችን ከግራና ከቀኝ እየናጡ እረፍት ነስተዋል። ኢትዮጵያ በዚህም መስክ ፈተናዋ ተጠናቆ አልቋል ማለት አይቻልም። እነዚህ የውስጥ አባጮችና ሀመሞች ለሀገሪቱ እንደምን የጎን ውጋት ሆነው እንደሚያስቃስቷት በስፋት እያስተዋልን ነው።

ከውጭ የሚወረወርባት የዲፕሎማሲና የእጅ አዙር ጫናም መልኩና ዓይነቱ ዝንጉርጉር ነው። የቀጣናው ተጋሪ ባቸ ታሪካዊ ጠላቶች እንቅልፍ አልባ ትንኮሳና ሴራ፣ በሩቅ መንግሥታት የሚጠነጠኑትና የሚሰነዘሩት የጋሉ የብረት አሎሎ ማስፈራሪያዎችና ማዕቀቦች እንደ እቅዳቸው ታርጌቱን ቢመታላቸው ኖሮ የሚፈጠረው ብሔራዊ ትራጄዲ ውጤቱ ቀላል ባልሆነ ነበር። “እንኳን ከተወረወረ ከታሰበም ያድናል” እንዲሉ ኢትዮጵያን የሚጠብቀው አምላክ ሰለማይተኛና ሰለማያንቀላፋ፣ በመሪዎቻችንና ሕዝባችን ብልህ አመራርና ስክነት እንደ ምኞታቸው ሊሆንላቸው አልቻለም።

ሀገሬን ከውስጥና ከውጭ ቀስፎ የያዛት ፈተና እንዳበዛዙና እንደ ባህርይው መዥጎርጎር ቢሆን ኖሮ “ገበርኩ” ብላ በተደነቃቀፈች ነበር። ምሥጋና ለፈጣሪያችን፣ አክብሮት ለመሪዎቻችንና ለሕዝባችን ይሁንና ኢትዮጵያ ዛሬም ቢሆን ቁርጭምጭሚቷ ፀንቶ እንደቆመች ነው። የአውሎ ነፋሱ ወጀብ አላንበረከካትም፣ የጠላቶቿ የተቀናባበረ የሴራ ወጥመድም ከግቢኃቸው አልገታትም።

**ለ. ተፈጥሮ ተኮር ብሔራዊ ፈተናዋ፣**

መቼም ትዝብቱ ለራሳችን ይሁንና እንደ እኛ እንደ ኢትዮጵያዊያን ተፈጥሮ የታዘበችው ሌላ ሕዝብ ስለመኖሩ ያጠራጥራል። በውሃ ላይ ተኝቶ ስለ ጥማት የሚተርክ፣ የተባረከ አፈር ከፈጣሪ ዘንድ ተለግሶት ስለ ርሃብ የሚዘምር ሌላ የምድር ወገን ካለ ብናውቀው አይከፋም። የዓለም ማሕበረሰብ ሲረዳን የኖረውና እየረዳን ያለው በእጁ ስንዴ እየዘገነልን፣ በሆዱ እየናቀን መሆኑን በድፍረት መናገሩ ብሔራዊ ክብርን መዳፈር ተደርጎ ሊቆጠር አይገባም።

በተፈጥሮ ሳይንስ ልጆቿን የምትመዝን ሀገር ተፈጥሮን ያለማስገበሯ በተማሪ ቋንቋ ስንፍና፣ በፖለቲካ የማይደናገሪያ ቋንቋ የሥርዓቶች ብልሹነት ሲባል መክረሙ እኛንም ሌሎችንም ያሰለቸ ሰበብ ነው። የድህነትን ስም የምናነሳው ልክ እንደ ልብ ወዳጅ “ድህነታችን” በማለት እያቆላመጥን ወይንም እንደ ቅርብ ወዳጅ ቤትኛ በማድረጋችን ጭምር ነው።

ከተፈጥሮ ጋር ከመኳረፋችን የተነሳ የሚደርሱብንን የድርቅ፣ የአንበጣ ወረርሽኝ ወዘተ. እየዘረዘርን ስሙልን እየልን ማለቱ፣ “ከሰደበኝ መልሶ የነገረ ገደለኝ” ይሉት ብሂልን ስለሚያስታውሰን እንደለመድነው “ሆድ ይፍጀው” ብለን ማለፉ ይቀላል።

ሐ. “የብሔራዊ ፈተናዎቻችን” አበረታች ውጤቶች፣

የዛሬዋ ኢትዮጵያ ለከበቧትና ፊቷ ለተደረደሩት ፈተናዎች ሁሉ “አጉራህ ጠናኝ” ብላ እጇን ለካቴና አሳልፋ አልሰጠችም። እንዲያውም የሩቅ ታዛቢዎቿ ሳይቀሩ ግራ በተጋባ ስሜት የግሰጋሰዋን ፍጥነት እያስተዋሉ “ወደፊት እያስፈነጠራት ያለው ምን ይሉት ኃይል ነው?” እስከማለት መድረሳቸው ለእኛ “ኩራት” ለእነርሱ እንቆቅልሽ የሆነ ይመስላል።

“ሁሉ በእጃችን፣ ሁሉ በደጃችን” እያሉ የሚፎክሩ ሀገራት ሳይቀሩ ግራ የተጋቡበት አንዱ ጉዳይ በጦርነት መካከል ውጤታማ የልማት ተግባራት በርብርብ ማከናወናችን ነው። እዚያ ማዶ ጀግናው የሉዓላዊነታችን አለኝታ የመከላከያ ሠራዊታችንና ከጎኑ የተሰለፉት የሕዝባዊ ሠራዊት ኃይላት አብሪተኛውን የወያኔ ጀሌ እየቀጡ ግፋ በለው በማለት ወደፊት በመገስገስ አብሪነን እያስተነፈሱለት ይገኛሉ። ወዲህ ማዶ እየተመረቁ ያሉት ግዙፍ ሀገራዊ ፕሮጀክቶችና የገበሬው ማሳ ሥር የሰደዱ ብሔራዊ ፈተናዎቻችንን ድል በመንሳት ተስፋችንን እያነቃቁ ይገኛሉ። “በአንድ እጅ ጦር፣ በሌላው እጅ ማረሻ” እንዲሉ መሆኑ ነው።

ካሁን በፊት ፈዘን የምናስተውላቸው የሌሎች ሀገራት መሠረተ ልማቶች ደጃፋችን ደርሰው “ኑና እዩልን” የማለት ደረጃ ላይ ደርሰናል። “በቅርብ ዓመታት ውስጥ የኤሌክትሪክ ኃይል ለጎረቤት ሀገራት እናጋራለን” ስንል የሳቁብን ሁሉ ዛሬ አፋቸውን በእጃቸው ላይ ጭነው ተገርመዋል። “የስንዴ እርዳታችሁን መቀበሉን አቁመን ሌሎችን ለመመገብ አቅደናል” ስንል ያፌዙብንም ወደ እውነታው ስንቃረብ ተገርመው እንዳቸው ከአንዳቸው እየተጠቃቀሱ ለመንሾካሾክ በቅተዋል። አልፎም ተርፎም “ገበታችን ላይ ዳቦ ጣል እያደረጉ” ሲዲገሙን የኖሩት መንግሥታትና ዓለም አቀፍ ተቋማት “በገበታ ለሀገር ስያሜ” እየገሰገሱ ያሉ አስደማሚ ፕሮጀክቶቻችንን እንደሚያጓጉዙልን ቀኑ መድረሱን ስናረጋግጥላቸው ከመገረም አልፈው ግራ መጋባታቸው አልቀረም።

እያንዳንዱን ቀን ኢትዮጵያ እየተቀበለች ያለችው በቁዘማ ሳይሆን አንዳች አዲስ ክስተት እያስተናገደች ነው። እዚህም ልማት፣ እዚያም ልማት - ያውም በጦርነት ፍልሚያ ውስጥ ሆና። ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የምታስገባቸውን ልጆቿን በብሔራዊ ፈተና ስትመዝን የሰነበተችው ኢትዮጵያ ራሷም በፈተናዎች መከበቧ እውነት ነው። ቢሆንም ግን የእያንዳንዱ ውስብስብ ተግዳሮቶቿ ውል በሚያስደንቅ ፍጥነት እልባት እያገኘ ስለሆነ የግስጋሴዋ ፍጥነት ጨምሯል።

እስከ ዛሬ የት ነበርን? አሰኝተው ላስደመሙን መሪዎቻችን ምሥጋናችን ይድረስልን። ከዕለት ዕለት የድል ብሥራት ለሚያሰማን የመከላከያ ሠራዊታችን ሞገስ ይሁንለት። ታላላቅ ፕሮጀክቶችን ለማስፈጸም ሌት ተቀን ለሚተጉ ተቋማትና የሕዝብ ባለውለታዎች ከፍ ያለው አክብሮታችን ይድረሳቸው። ድብርት የተጫጫነው ሀገራዊ ኢኮኖሚያችን በቅርብ ጊዜ እንደሚነቃቃ በሚያውቀን የልማት ጠረን እያረጋገጥን ስለሆነ ፈጻሚዎቻችንና አስፈጻሚዎቻችን “እሰይ!” ማለቱ ያበረታታቸዋል።

ዲፕሎማሲያችን በጥበብ እየተመራ መሆኑን ስናይ ልባችን ይሞቃል። ኢትዮጵያ ስትፈተን እንደ ወርቅ እየጠራች እንደምትሔድ በብዙ ማስረጃዎች ማረጋገጥ ይቻላል። “ብዙ ከብት ለማርባት፣ አልቅትን ጠብቆ ውኃ ማጠጣት” ይላል የሀገሬ ሰው። ጥሩ የማስጠንቀቂያ ምክር ነው። የአረቦቹን አባባል ተውሰን ርዕሰ ጉዳያችንን እንደምድም፦ “ውሾቹ ይጮኻሉ፣ ግመሎቹም ይጓዛሉ!” ሰላም ይሁን!

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# የእንስሳትና ዓሳ ልማቱን በተጠናከረ መንገድ

**ስምስም መንግሥቱ**

ኢትዮጵያ አመቱን ሙሉ የሚፈሱ ትላልቅ ወንዞች እንዲሁም ሐይቆችና ለኤሌክትሪክ ሀይል ማመንጫና ለመስኖ የተገነቡ ግዙፍ ግድቦች ባለቤት ናት። እነዚህ የውሃ መገኛዎች የሀገሪቱ አሳ ሀብት ምንጮችም ናቸው።

ሀይቆቹ የአሣ ሀብት በስፋት ይመረትባቸዋል፤ ከነዚህ የውሃ አካላት ወደ 94ሺ ቶን አሣ ሊመረት እንደሚችል የቅርብ ጊዜ ጥናቶችን ዋቢ ያደረገ ከግብርና ሚኒስቴር የተገኘ መረጃ ያመለከታል። ከሐይቆች የሚመረተው አሣ ለገበያ እየቀረበ ለከተሞች ፍጆታ የሚውል ሲሆን፣የወንዞቹ ደግሞ በገጠሩ ህዝብ ለምግብነት ይውላል። የአሳ ሀብቱ በስፋት በሚገኝባቸው የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚኖረው ማህበረሰብ የአሳ ምርቱን ለምግብነት ብቻ ሳይሆን ለገበያ በማዋል በገቢ ምንጭነት ይጠቀሙበታል።

በአንድ ወቅት በጋምቤላ ክልል ያለውን ሰፊ የአሳ ሀብት ታሳቢ ያደረገ የአሳ ምርትን በፋብሪካ ደረጃ በማቀነባበር ለውጭ ገበያ የማቅረብ እቅድ እንደነበረ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በአሳ ልማት በኩል በቀጣይ በአባይ ግድብ ልማቱን ማካሄድ የሚያስችል እምቅ አቅም ስለመኖሩ ከመጠቆሙ በቀር በቀጣይ ሊካሄድ ስለሚችል ሰፊ የአሳ ልማት እስከ አሁን ብዙም የተሰማ የለም።

የአሳ ሀብትን በማልማትም ሆነ ለምግብነት በመጠቀም በኩል ክፍተቶች ሲስተዋሉ ኖረዋል። ከህዝቡ አመለካከት የተነሳ አሳ ለምግብነት የሚውልበት ሁኔታ ውስን ሆኖ ነበር፤ በእዚህ በኩል ብዙም የሚሰማ ችግር አይደለም።

አመራረቱ ግን አሁንም ስራው ከዘልማድና ባህላዊ አሰራር ብዙም እንዳልወጣ ያመለክታል። በአንዳንድ አካባቢዎች የአሳ ሀብቱን ከማልማት ይልቅ ህገወጥ አሳ አስጋሪዎች በአሳ ሀብቱ ላይ ጉዳት እያደረሱ ስለመሆናቸው ሲነገር ይደመጣል። ይህ ሁሉ ችግር ከዘርፉ ሊገኝ የሚችለውን የገቢ ምንጭ እንዳሳነሰው ነው የሚጠቆመው።

ዛሬም በዘርፉ ላይ ጎልቶ የወጣ ሥራ እየታየ እንዳልሆነ ይጠቆማል። በሀገሪቱ የአሳ ሀብት በስፋት እያለ ሀገሪቱ አሁንም የአሳ ምርት ውጤቶችን ከውጭ ሀገሮች እያስገባች ትገኛለች። ከተለያዩ ሀገራት የሚገቡ የአሣ ውጤቶችና ምርቶች እንደ ሱፐርማርኬት ባሉ በሰፋፊ መገበያዎችና ሆቴል ቤቶች የሚታየው ሁኔታም ይህንኑ ያመለክታል። ይህም በሀገር ውስጥ በዘርፉ ሥራዎች ስላለመሰራታቸው እንደ አንድ ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

ኢትዮጵያ በእንስሳት ሀብቷም ቢሆን ከአፍሪካ ቀዳሚ፣ከዓለም ደግሞ በአስረኛ ደረጃ ላይ ትጠቀሳለች። አብዛኛው የግብርና ሥራም በእንስሳት ጉልበት የሚከናወን መሆኑ ይታወቃል። የእንስሳት ሀብቱ ከዚህ በተጨማሪም ለሥጋ ምርት ይውላል። ይህ ሁኔታም የእንስሳት ሀብት በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ላቅ ያለ ድርሻ እንዲኖረው አድርጎታል።

እንዲያውም ሆኖ ግን የአሳና እንስሳት ዘርፉ ክፍለኢኮኖሚው ላይ የሚጠበቀውን ያህል ድርሻ እንዳላበረከተ ይገለጻል። በሌላ በኩልም በድንበሮች አካባቢ በሚፈፀም ህገወጥ ግብይት የተነሳ ከዘርፉ መገኘት ያለበት ጥቅም እየተገኘ አይደለም።

ኢትዮጵያ የአሳና የእንስሳት ሀብቷን በተቀናጀ አግባብ ማልማት ባለመቻሏ፣ በግብይት ላይም በሚገባ ባለመስራቷ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ቀርቶ ለዜጎቿም በበቂ ሁኔታ ማቅረብ አልቻለችም። በተለይ በእንስሳት ሀብት ላይ የሚስተዋለው ህገወጥ ንግድ ችግሩ የበለጠ እንዲባባስ አድርጓል። ይህ ሁኔታ እስከመቼ ድረስ ይዘልቃል? በሚል በብዙዎች አስተያየት ይሰጣሉ።

በግብርና ሚኒስቴር የእንስሳትና አሣ ሀብት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ፍቅሩ ረጋሣ እንደሚሉት፤ ኢትዮጵያ ካላት የውሃ ሀብት በተለያየ መልኩ ተጠቃሚ ለመሆን እየሰራች ትገኛለች። ወጣቶች ተደራጅተው በአሣ ልማት ላይ እንዲሰሩ እድል እየተፈጠረ ነው። ግብርና ሚኒስቴርም በባህርዳር፣ ሰበታ፣ ዝዋይ፣ ደቡብና ሲዳማ ባሉት የአሳ ጫጩት ማባዣ ማዕከላት የአሣ ጫጩቶችን በማባዛት በተለያዩ የውሃ አካላት ውስጥ በመጨመር ልማቱ እንዲከናወን ያግዛል።

በወንዞችና በተፈጥሮ ሐይቆች ብቻ ሲከናወን የቆየውን የአሣ ልማት በየአካባቢው ለአሣ ልማት የሚውሉ ሰው ሰራሽ ኩሬዎች(ፖንዶች) በማዘጋጀት እየተሰራ ሲሆን፣ በዚህም የአሳ ምርታማነትን መጨመር ተችሏል። ይሁንና ምርታማነቱ ቢሻሻልም ለውጭ ገበያ ማቅረብ ግን አልተጀመረም።

በዚህ ረገድ ያለው ተሞክሮ በቋንጣ መልክ (ስሞክድ ፊሽ) በሚባል ዘዴ ከጋምቤላ አካባቢ ወደ ደቡብ ሱዳንና አንዳንድ ሀገራት የመላክ ጅምር ሥራዎች ቢኖሩም፣ ስራው የተጠናከረ አይደለም። በዘርፉ ከፍተኛ ሥራ መሥራት ይጠበቃል።

በሶማሊያ ድንበር አካባቢ ያልተቀነባበረ የአሣ ምርት በህገወጥ መንገድ ወደ ኢትዮጵያ ሲገባም እንደተደረሰበት ጠቅሰው፣ ሀገሪቱ ባሏት የውሃ ሀብቶች ሁሉ አሳ የማምረት አቅሟን ካሳደገች እነዚህን ሁሉ ክፍተቶች መቅረፍ ይቻላል ነው የሚሉት።

የአባይ ግድብም ለአሣ ልማቱ ከፍተኛ ግብአት እንደሚሆን ይጠበቃል። በዚህ ረገድ የምሥራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግሥታት(ኢጋድ) ኢትዮጵያን በመግባቢያ ሰነድ ያሳተፈ «ብሉ ኢኮኖሚ ስትራተጂ» በሚል አጀንዳ ቀርጾ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። ይህን ጥረት ለማሳካት የግብርና ሚኒስቴርን ብቻ ሳይሆን የተለያዩ አስፈጻሚ ተቋማትንም የጋራ ትብብር ይጠይቃል። በዚህ መልኩ ከተሰራ ከኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ባለፈ ዜጎችን በሥርአተ ምግብ ተጠቃሚ ማድረግ የሚቻልበት ዕድል ይፈጠራል።



ኢትዮጵያ በከብት ሀብቷ ተጠቃሽ ብትሆንም ከዘርፉ ተጠቃሚ እየሆነች አይደለችም፤

**በግብርናው ሥራው በሬ ጠምዶ ከማረስ ወደ ሜካናይዜሽን ለመሸጋገር እየተደረገ ያለው ጅማሮ ተጠናክሮ ከቀጠለ ወደ 15 ሚሊየን የሚጠጋው የእንስሳት ሀብት ሙሉ ለሙሉ ለሥጋ ምርት የሚውልበት ሁኔታ ይፈጠራል፤ ያኔ ደግሞ የእንስሳት ሀብቱ በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚው ገቢ ላይ ለውጥ ያመጣል።**

በእንስሳት ሀብት ልማት በኩል ስላለውም ሚኒስትር ዴኤታው እንዳሉት፤ ኢትዮጵያ በእንስሳት ሀብቷ ትታወቃለች። ሀገሪቱ በአጠቃላይ ወደ 70 ሚሊየን የሚጠጋ የከብት ሀብት አላት። ካለው የከብት ሀብት 95 በመቶ የሚሆነው የህገረሰብ ነው። የከብት ሀብቱ በአንድ በኩል ለግብርና ሥራ ይውላል። ከዚህ አገልግሎት በኃላ ደግሞ ለሥጋ ምርት እንዲውል ይደረጋል።

ከከብት ሀብቷ መካከልም ወደ 15 ሚሊየን የሚጠጉት በሬዎች ናቸው። ይህም በእርሻ ሥራው ለሰብል ልማት በከፍተኛ ሁኔታ አስተዋጽኦ እያደረገ ነው። የተቀረው ደግሞ እንዲደልብ ተደርጎ ለገበያ እየቀረበ ለሥጋ ምግብ ፍጆታ ይውላል። ሀገሪቱ ወደ 15 ሚሊየን የሚጠጋ የወተት ላሞችም አሏት። ከነዚህ ውስጥም ወደ ሰባት ሚሊየን የሚሆኑት የሚታለቡ ናቸው።

የሀገሪቱ እንስሳት በተለያዩ ምክንያቶች የሥጋና የወተት ምርታማነታቸው ዝቅተኛ ነው። በዚህ የተነሳ በአቅርቦትና ፍላጎት መካከል ክፍተት ይታያል፤ ይህን ክፍተት ለመሙላት በመንግስት በኩል የተሻሻለ ዝርያ ያላቸው እንስሳትን በማዳቀል ምርታማነታቸውን የመጨመር ሥራ እየተሰራ ይገኛል። በተከናወነው የዝርያ ማሻሻያ ዘዴ ከአንድ ላም በአማካይ በቀን እስከ 15 ሊትር ወተት ማግኘት የሚቻልበት ዕድል እየተፈጠረ ነው።

በተለምዶ የፈረንጅ ላም የምትባለው ወይንም በተሻሻለ ዝርያ የተገኘች አንዲት ላም የምትሰጠው የወተት ምርት አስር ሀገረሰብ ላሞች የሚሰጡትን ወተት ያህላል። ይህ ትልቅ ለውጥ ነው። አሁንም ግን የተጠቃሚውን ፍላጎት ለማሟላት ብዙ መሥራት ይጠይቃል።

አሁን ባለው መረጃ በኢትዮጵያ በነፍስ ወከፍ የወተት ምርት ፍላጎት 70 ሊትር ነው። ይህ ደግሞ የዓለምጤና ድርጅት ካወጣው መስፈርት በታች ነው። በዘርፉ ያለውን ፍላጎትና የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን መሠረት በማድረግ ግብርና ሚኒስቴር ትኩረት ሰጥቶ በእንስሳት እርባታና ምርታማነት ማሳደግ ላይ እየሰራ ይገኛል።

እንስሳቱ ምርታማነታቸው እንዲጨምር የተመጣጠነ መኖ ማግኘት ይኖርባቸዋል፤ በዚህ ረገድም በትኩረት እየተሰራ መሆኑን ሚኒስትር ዴኤታው ይገልጻሉ። በጤናም የተጠበቁ እንዲሆኑ በህክምና አገልግሎቱ ላይ ክትትልና ቁጥጥሩ መጠናከሩን የጠቀሱት አቶ ፍቅሩ፤በተለይም የሥጋ ምርቶችን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ጤንነቱ የተጠበቀ የሥጋ ምርት ማቅረብ እንደአንድ መሥፈርት የሚታይ መሆኑንና የበሽታ መከላከል ሥራው አስፈላጊነትን አስረድተዋል።

እንደ ሚኒስትርዴኤታው ገለጻ፤ በግብርናው ሥራው በሬ ጠምዶ ከማረስ ወደ ሜካናይዜሽን ለመሸጋገር እየተደረገ ያለው ጅማሮ ተጠናክሮ ከቀጠለ ወደ 15 ሚሊየን የሚጠጋው የእንስሳት ሀብት ሙሉ ለሙሉ ለሥጋ ምርት የሚውልበት ሁኔታ ይፈጠራል፤ ያኔ ደግሞ የእንስሳት ሀብቱ በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚው ገቢ ላይ ለውጥ ያመጣል።

ሚኒስትር ዴኤታው ህገወጦች የቁም እንስሳ በህገወጥ መንገድ በሶማሊያ፣ በጅቡቲ፣ በኬኒያ በሌሎችም ጎረቤት ሀገሮች በኩል እንዲወጡ እያደረጉ መሆናቸውን ይገልጻሉ። እንስሳቱ በህገወጥ መንገድ ከሀገር መውጣታቸው ብቻ ሳይሆን የሚያሳስበው፣ በሌላ ሀገር የምስክር ወረቀት አማካኝነት ለመካከለኛው ምሥራቅ፣ሰሜኑ ክፍልና ለሌሎችም ሀገራት ለገበያ የሚቀርቡት ሁኔታ ነው ይላሉ። በእንስሳት ሊገኝ የሚችል ጥቅምን ከሚያሳጡ ምክንያቶች ይሄ አንዱ በመሆን ይጠቀሳል ሲሉ ያብራራሉ።

በመንግሥት ክትትልና ቁጥጥር ብቻ ይህን ተግዳሮት ማስቀረት አይቻልም ይላሉ ሚኒስትር ዴኤታው። የህዝብ ባለቤትነት፣ ተቆርቋሪነትና ተሳትፎ እንደሚያስፈልግ ያስገነዝባሉ። በመንግሥት ቁርጠኝነት እየተከናወነ እንዳለው የስንዴ ልማትና የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር በእንስሳት ልማቱም የተጠናከረ ሥራ ለመሥራት በሚኒስቴሩ በኩል ጥረት እየተደረገ መሆኑን ይገልጻሉ።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ማብራሪያ፤ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ይህን ተልእኮ ይዞ ሲነሳ የግል ባለሀብቱን በእጅጉ በማበረታታት ነው። አሁን ባለው አንቅስቃሴም በገበሬው መንደር ከሚከናወነው የእንስሳት ልማት በተጨማሪ የግሉ ዘርፉ የላቀ ሚና እየተወጣ ይገኛል።

አሁን ገበያው ላይ እየቀረበ ያለው የዶሮና ዶሮ ውጤት ምርት በግሉ ዘርፍ የሚለማ መሆኑንም ጠቅሰው፣ የግሉ ዘርፍ በስፋት ባይንቀሳቀስ ኖሮ አንድ የሀገረሰብ ዶሮ በአመት በምርታመርተው 40 እንቁላል የተጠቃሚውን ፍላጎት ለማሟላት ያዳግት ነበር ሲሉ ያብራራሉ። የተሻሻለ ዝርያ ካላት አንድ ዶሮ በአመት እስከ ሶስት መቶ እንቁላል ማግኘት እንደሚቻልም ጠቅሰው፣ይህ ጥረት ክፍተቱን በመጠኑም ቢሆን ለመቀነስ ያግዛል ይላሉ።

በወተት ልማቱም ቢሆን ተደራጅተውና በግላቸው የሚሰሩ ባለሀብቶች ናቸው ፍላጎትን ለማሟላት ጥረት እያደረጉ የሚገኙት ሲሉ ሚኒስትር ዴኤታው ይጠቅሳሉ። በቴክኖሎጂ የታገዘ የእንስሳት ልማት ለማካሄድ በመንግሥት በኩል እየተከናወነ ባለው ሥራ የወተት ላሞችን በብዛት ለማግኘት እንዲቻል ወደ 12ሺ ኮርማዎች ከውጭ ሀገር እንዲገቡ መደረጉን ይጠቅሳሉ።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ በከብት ልማቱ ላይ ለመሰማራት ለሚፈልጉም መንግሥት በተመጣጣኝ ዋጋ ጊደር እየቀረበ ይገኛል። ይህም በአዳ በርጋ፣ቻግኒ፣ወላይታሶዶ፣ወልቂጤ፣ላይ ካለፈው በጀት አመት ጀምሮ እየተከናወነ ባለው ጊደር የማባዛት ሥራ ጊደር ለሚፈልጉ በማቅረብ ፍላጎትን ለማሟላት ጥረት እየተደረገ ነው። ዘንድሮ ደግሞ ሶስት የማባዣ ማእከሎችን በመጨመር የማባዛቱን ሥራ ለማስፋት እንቅስቃሴ ተጀምሯል።

ሰሞኑን በስካይላይት ሆቴል የተከፈተው የዶሮ ኤክስፖና ሰባተኛው የእንስሳት ሀብት ዐውደርዕይ በግብርናው ዘርፍ በተለይም በእንስሳትና የእንስሳት ተዋጽኦ ልማት ላይ እየተደረገ ያለውን እንቅስቃሴና ጥረት ያመለክታል። በዚህ ዝግጅት ላይ የወተት፣ የእንቁላል ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር የሚያግዙ ቴክኖሎጂዎች የማስተዋወቅ ስራ ተካሂዷል፤ በዘርፉ በተከናወኑት ሥራዎች የተገኙ ውጤቶችን ማየት ተችሏል፤ የገበያ ትስስር ለመፍጠርም እድል የተገኘበት ነው።

በዚህ ዐወደ ርዕይ ላይ ኢትዮጵያን ጨምሮ ከ10 ሀገራት የተውጣጡ በቴክኖሎጂ፣በእንስሳትና እንስሳት ውጤት ልማት ላይ የተሰማሩ 70 የሚሆኑ ኩባንያዎች መሳተፋቸውም ለዘርፉ የተሰጠው ትኩረት አንዱ ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

መንግስት በያዘው የበጋ መስኖ ስንዴ ልማትና በመኸር እርሻ በስንዴ ልማት እየተካሄደ ባለው ርብርብ ሀገሪቱ ስኬታማ እየሆነች መጥታለች። መንግስት ይህን ልማቱን በዶሮ፣ እንቁላልና ወተት ልማት ላይም አጠናክሮ እንደሚቀጥል ማስታወቁ ይታወሳል። በመሆኑም መሰል ኤክስፖዎች በእንስሳት ሀብት ለተያዘው ምርታማነትና ምርታማነትን የማሳደግ ስራ የጎላ አስተዋጽኦ የሚኖራቸው እንደመሆኑ በስፋት ሊካሄዱ የሚችሉበት ሁኔታ መፈጠር ይኖርበታል።

ማህበራዊ

# አስኳላ

# ንባብና ቋንቋ በአዲሱ ስርዓተ ትምህርት

ጽጌረዳ ጫንያለው

ሁሉም ቋንቋዎች ከአገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ጋር በተጣጣመ መልኩ በጥንቃቄ ተጠንተው ወደ ትምህርት አገልግሎት ከተቀየሩ የቋንቋ ተናጋሪዎች የተሻለ መደበኛ ትምህርት ማግኘት እንደሚችሉ ማንም የሚያምነው ጉዳይ ነው:: ይህ ከተደረገ ጥናቶች እንደሚሉት ማህበረሰቡ ባህሉን፣ ታሪኩን እና ቅርሶቹን በቀላሉ ማስተዋወቅ እንዲችል እድል ይፈጥራል:: ለሌሎች ማንነቱን ማስተማሪያ ዘዴውም ይሆንለታል:: አስተማሪን ከተማሪዎች ጋር ለማገናኘትም ቀላል መንገድ ይፈጥራል:: እናም እንደ አገር በአዲሱ የትምህርት ስርዓት የተመረጡ የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች በትምህር አገልግሎቱ ውስጥ እንዲገቡ መደረጉ ይህንን ታሳቢ በማድረግ ነው::

እስከዛሬ እንደ አገር ለትምህርት አገልግሎት የሚውሉ የተመረጡ የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች ጥቂት ቢሆኑም አሁን ግን ሰፍተዋል:: በትምህርት ሚኒስቴር የተጠናው ጥናት እንዳመላከተው፤ ከ53 በላይ የሚሆኑት ቋንቋዎች አገልግሎቱን ይሰጣሉ:: ይህ መሆኑ ደግሞ የጥራትን ጉዳይ መፍትሄ ለማበጀት እጅግ ይጠቅማል የሚል እሳቤም አለ::

ትምህርት ሚኒስቴር ሥርዓተ ትምህርቱን ጨምሮ በተለያዩ የትምህርት ሥርዓት ጉዳዮች ላይ ብዙ ጥናቶችን አካሂዷል:: በፖለቲካ አስተዳደር እና ፖሊሲዎች ላይ የተደረጉ የጥናት ምክሮች እና ለውጦች ላይ በመመርኮዝም ብዙ ለውጦች የሚመጡበትን ሥርዓት ፈጥሯል:: አንዱ ከላይ እንዳልነው ሁሉም ቋንቋዎች ከአገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ጋር በተጣጣመ መልኩ በጥንቃቄ ተጠንተው ወደ ትምህርት አገልግሎት እንዲቀየሩ ማስቻል ነው:: በአዲሱ ስርኣተ ትምህርትም ይህ ተካቶ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተናጋሪዎች የተሻለ መደበኛ ትምህርት እንዲሰጥ እየተደረገ ነው::

የአዲሱ ስርዓተ ትምህርት በአፍ መፍቻ ቋንቋ መሰጠቱ ለምን አስፈለገ፤ እንዴት ይሰጣል፤ ከንባብ ጋር በማዋሃድ እንዴት ተማሪዎች ጋር መድረስ አለበትና መሰል ነገሮችን በማካተት ሚኒስቴሩ የተለያዩ ጥናቶችን በማድረግ የወሩ ማብቂያ በንባብ ላይ ሰፊ ሥራ ሲሰራ ከነበረው ኢትዮ ኪድስ ጋር በመተባበር በአዘጋጀው ፕሮግላም ላይ አቅርቦ ነበር:: እኛም ይህንን መነሻ በማድረግ በአዲሱ ትምህርት ስርዓት ቋንቋና ንባብ እንዴት ተግባራዊ እንደሚሆኑ ለማሳየት ወደድን::

ጥናቱ እንደሚለው፤ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሲኖር ሰዎች ባህላቸውን፣ ታሪካቸውን እና ቅርሶቻቸውን በቀላሉ ለማስተዋወቅና ለማወቅ እድል ይፈጥርላቸዋል:: ተቀራርበው እንዲሰሩም ያደርጋቸዋል:: ልዩነት ውበት መሆኑን እንዲረዱ ከማድረግ አንጻርም የማይተካ ሚና አለው:: ስለሆነም እንደ አገር ለተግባራዊነቱ በርካታ ሥራዎች ተከናውነዋል:: እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገራት ይህ ነገር ተግባራዊ መሆኑ ደግሞ አገርን ለመገንባት ሁነኛ መፍትሄ ነው::

የትምህርት ጥራት ጉዳይ እንደ አገር ችግር እየሆነ ከመጣ ሰነባብቷል የሚለው መረጃው፤ በቀላሉ ውሉን የሚያገኝበት መንገድ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ማስተማር ሲቻል ነው:: በትምህርት አቅርቦትና ተደራሽነት ዙሪያ የተፋጠነ ሥራ በመሰራቱ መሻሻሎች መጥተዋል:: በቋንቋ ላይም ይህንን ያህል ጠንክሮ ከተሰራ ለውጡን በአጭር ጊዜ ማየት እንደሚቻልም ጥናቱ ያመላክታል:: በተለይም የ21ኛው ክፍለ ዘመን ብቃቶችን ለማዳበርና ህብረተሰቡን ወደፊት እንዲያራመድ ለማስቻል ቋንቋ ሁነኛ መድህኒት እንደሆነ ያብራራል::

## በትምህርት ሥርዓት ውስጥ ቋንቋን መማር እንዴት?

**ቅድመ-መደበኛ ደረጃ፡-** በዚህ የክፍል ደረጃ ውስጥ ያሉ ሕጻናት አምስት ዓመትን የያዙ በመሆናቸው በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የቃል እና የማንበብ ክህሎቶችን እንዲያዳብሩ ተደርገው ይማራሉ:: ሁለት ዓመት ብቻ የሚቆዩበትም ይሆናል::

**አንደኛ ደረጃ፡-** በዚህ የክፍል ደረጃ ደግሞ ከቃል እና ከማንበብ አልፈው የመፃፍ ክህሎትን በተመጣጠነ መልኩ ማዳበር እንዲችሉ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንዲማሩ ይደረጋል:: ይህ መሆኑ ደግሞ ከማንበብ ተሻግረው መጻፍን እንዲለማመዱ እድል ይሰጣቸዋል::

**መካከለኛ ደረጃ፡-** በእዚህ የክፍል ደረጃ ውስጥ የቋንቋ ክህሎትን ወደ ሕይወት መመሪያቸው መለወጥ የሚለማመዱበት ጊዜ ነው:: በተጨማሪም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ዘርፎችን ለመቀጠል በሚያስችላቸው ሁኔታ ያሳድጉበታል:: ለዚህ ደግሞ ኢትዮጵያ ከ80 በላይ ቋንቋዎች የሚነገሩባት የብዙ ቋንቋ ተናጋሪ ሀገር መሆኗ እጅጉን ይጠቅማቸዋል። በቅድመ ክፍል እና በአንደኛ ደረጃ እንደ ማስተማሪያ ሚዲያ የተጠቀሙበትን ለፈጠራ ጭምር የሚጠቀሙበት ያደርጋቸዋል:: ስለሆነም በዚህ ክፍል ደረጃ ላይ የአፍ መፍቻ ቋንቋን መጠቀማቸው በየጊዜው ከፍ የሚሉበትን እድል ይሰጣቸዋል::

> **ሕጻናት አምስት ዓመትን የያዙ በመሆናቸው በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የቃል እና የማንበብ ክህሎቶችን እንዲያዳብሩ ተደርገው ይማራሉ**

በአዲሱ የአጠቃላይ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት ጋር በተጣጣመ መልኩ የተዘጋጀው አዲሱ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ሥርዓተ ትምህርትም በዚህ ደረጃ የሚሰጥ በመሆኑ ብዙ ነገሮችን በውጤታማነት ለመምራት ያስችላቸዋል:: በተለይም አለማቀፋዊነትን ከማወቅ አንጻር የማይተካ ሚና ይኖረዋል:: ምክንያቱም ትምህርቱ ሲሰጥ የመማሪያ ውጤቶች፣ የይዘት ፍሰት ቻርት፣ የሚመጥናቸውን የመማር ብቃቶች እና ሥርዓተ ትምህርትን የሚከተል ነው:: በተጨማሪም ከዘጠነኛ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ እንደ ግዴታ እንግሊዝኛ ቋንቋ የማስተማሪያ ዘዴ ይሆናልና ተማሪዎች ዘጠነኛ ክፍል ላይ ሲደርሱ መደናገር እንዳይኖርባቸው ያደርጋቸዋል::

ከቋንቋ ቀጥሎ ጥራቱ ላይ የሚያሳስበው ነገር ተማሪዎች ከንባብ ጋር ያላቸው ቁርኝት ሲሆን፤ በጥናቱ ትኩረት ከሚሹ መሰረታዊ ነገሮች መካከል አንዱ ተደርጎ ታይቷል:: ለአገሪቱ አጠቃላይ የትምህርት ሥርዓት የተዘጋጀው የሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ ዋና ዓላማም ሆኖ ወደ ትግበራው የተገባበት ሁኔታ አለ:: ይህንን የንባብ ክህሎት ከማሳደግ አኳያ ልዩ ትኩረት ተችሮታል::

‹‹ያለ ንባብ ፈጠራ፣ አምራችነት፣ ራስን መረዳትና ኃላፊነትን መውሰድ ሊመጡ አይችሉም:: ያለንባብ ኃላፊነት የሚሰማቸው ሰውም መሆን አይቻልም:: ያለ ንባብ ስለአገራዊ ልማት ማውራት አይታሰብም›› የሚለው ጥናቱ፤ በንባብ ላይ ንቁ አስተዋጾ ያላቸው ዜጎችን ለማፍራት የንባብ ክህሎትን ማሳደግ ግድ እንደሆነም አስቀምጧል::

እንደ መረጃው ከሆነ፤ ንባብን ከማሳደግ አኳያ ትልቅ ኃላፊነት የተጣለባቸው ተቋማት ትምህርት ሚኒስቴር ፣የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች፤ ከቅድመ መደበኛ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ጀምሮ ለአጠቃላይ ትምህርት ኃላፊነት የሚወስዱ አካላት ናቸው:: ስለዚህም ትምህርት ሚኒስቴር እነዚህን አካላት በማሳተፍ የ10 ዓመት የትምህርት ፍኖተ ካርታ አዘጋጅቶ ወደ ትግበራው ገብቷል:: በኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ ዋና ዋና ስትራቴጂካዊ ለውጦች ይሆናሉ ብሎ ካሰባቸው መካከልም አንዱ ንባብ ሆኗል::

## ከንባብና ከቋንቋ አንጻር ያለፈው ስርዓተ ትምህርት ምን ጉድለቶች ነበሩበት ?

ጥናቱ ጉድለቶቹን በሦስት ከፍሎ ያሳያል:: የአፍ መፍቻ ቋንቋ፣ የፌደራል ቋንቋዎች እና እንግሊዝኛን በመጥቀስ:: ከዚህ አኳያም የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሕጻናት ከባድ የቋንቋ ችግር አለባቸው ይላል:: በሁሉም ቋንቋዎች የማንበብ እና የመፃፍ መሰረታዊ ክህሎት እንደሌላቸውም ያብራራል:: በተለይም የሳይንስና ቴክኖሎጂ ቋንቋ ተደርጎ የሚወሰደው እንግሊዘኛ ለብዙ የርዕሰ ጉዳይ አስተማሪዎች እንዲሁም እንግሊዘኛን እንደ አንድ የትምህርት አይነት በሚያስተምሩ መምህራን ላይ ከባድ ፈተና እንደሆነም ተጠቁሟል።

የልጆችን የንባብ ክህሎት አፈጻጸምና የብቃት ደረጃ ጥናቱ እንዳስቀመጠው፤ በአንደኛም ሆነ በመካከለኛው የክፍል ደረጃ ላይ ያሉ ተማሪዎች ብዙ መቶኛ በዜሮ አንባቢዎች ስር ይወድቃሉ:: በተለይም የሕጻናት የማንበብ አዝማሚያ በትርፍ ሰዓት እንደሚቀንስ በደንብ ታይቷል:: ለዚህ ደግሞ ዋና ዋና ምክንያቶች ተደርገው የሚወሰዱት የትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራን እና መምህራን ብቃት፣ ሙያዊ እድገት ያለመኖርና በስልጠናዎች አለመዳበር፤ የትምህርት ቁሳቁስ (የመማሪያ መጽሀፍት፣ የአስተማሪ መመሪያ) በበቂ ሁኔታ አለመገኘት ፤ የትምህርት ቤት መገልገያዎች (ተግባራዊ ቤተ-መጻሕፍት፣ የንባብ ማዕዘኖች) ምቹ አለመሆንና ያለመኖር የሚሉት ናቸው::

ለልጆች ንባብ ድጋፍ ( ቤተሰብ፣ ትምህርት ቤቶች) የሚጠበቅባቸውን አለመስራታቸው፤ የማንበብ ክህሎት በመማር ማስተማር እና የምዘና ዘዴዎች አለመካተታቸው ከሚጠቀሱ መሰረታዊ ችግሮች መካከል መሆናቸውን ጥናቱ ያስቀምጣል:: በመሆኑም ንባብን አገራዊ አጀንዳ በማድረግ መላውን ህብረተሰብና ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ማሰባሰብ ይኖርበታል በሚል እየተሰራ እንደሚገኝ መረጃው አመላክቷል:: እንደ ትምህርት ሥርዓት ንባብ ከእነአተገባበሩ የገባበት ምክንያትም ይህ እንደሆነ አብራርቷል::

## ከመምህራን ጋር ተያይዞ ያሉ ችግሮች

በመምህራን ማሰልጠኛና በዩኒቨርሲቲ ውስጥ የማስተማር ዘዴው እንግሊዝኛ መሆን፤ በመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎችን በአፍ መፍቻ ቋንቋ ለማስተማር ተመራቂዎች የሚመረቁበት የትምህርት አይነት መለያየት፤ ተመራቂዎቹ በእንግሊዝኛ የተማሩትን ወደ አፍ መፍቻ ቋንቋ ቀይሮ ለማቅረብ መቸገራቸው፤ የአተገባበር መመሪያ አለመኖሩ የመሳሰሉት ናቸው::

## በትምህርት ልማት ፍኖተ ካርታ (2018 እስከ 2030) ለቋንቋ የታቀዱ ማሻሻያዎች ምን ይመስላሉ?

እንደ ጥናቱ ከሆነ፤ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ስርዓት (ከ1 እስከ 6ተኛ ክፍል) የልጆችን የመናገር፣ የማንበብ እና የመጻፍ ችሎታዎች ተገቢውን ትኩረት ሊሰጣቸው እና ሊጠናከሩ ይገባል። በዚህ መሠረት ተማሪዎች ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ የአፍ መፍቻ ቋንቋን እንደ ማስተማሪያ ዘዴ መጀምር አንዱና መሰረታዊ ነገር ተደርጎ ተወስዷል::

ከ1ኛ ክፍል ጀምሮ እንግሊዘኛን እንደ ትምህርት ጀማሮ ትኩረቱ በቃል/በንግግር/በማዳመጥ ጉዳዮች ላይ መሆን አለበት:: እስከ 3ኛ ክፍል ድረስ የሚዘልቅም ይሆናል:: በዚህ ክፍል ደረጃ ተማሪዎች ከፌዴራል ቋንቋዎች አንዱን ወስደው መማር ይጠበቅባቸዋል። በሚመለከታቸው የክልል ባለስልጣናት ውሳኔ መሰረት የተመረጠው የፌደራል ቋንቋ ከየትኛውም ክፍል ጀምሮ መማር መቀጠል ይገባልም:: ንባብም በዚሁ ልክ የሚተገበር ይሆናል::

## ስርዓተ ትምህርቱን የመተግበሪያ ዘዴ

ጥናቱ እንደሚለው፤ የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት የትምህርት ቋንቋን የሚያሰለጥኑበት ደረጃን ማሻሻል፤ ለወደፊት መምህራን የተለያዩ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን እንዲማሩ እድል መፍጠር፤ የእንግሊዘኛ ቋንቋዎች ሥርዓተ ትምህርት በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት መዋቅር የማዳመጥ፣ የመጻፍ፣ የመናገር እና የማንበብ ችሎታዎችን እንዲያሟሉ ማድረግ ማለትም የማንበብ ክህሎት በቅድመ እና በድህረ ንባብ እንቅስቃሴዎች እንዲሁም ተማሪዎቹ የእንግሊዘኛ ስነ-ድምጾች ከተገቢ ፊደሎች ጋር በማገናኘት እንዲለማመዱ ማድረግ በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው።

የኢትዮጵያ የትምህርትና የሥልጠና ሥርዓት ተግባራዊ ሲደረግ እያንዳንዱ ተማሪ ሊያገኛቸው የሚገቡ ልዩ ሙያዎች፣ ብቃቶችና ባህሪያትን ማዳበር የሚጠበቅበት፣ የተሟላ ብቃት ያለው፣ አምራች፣ በአገር አቀፍና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ዜጋ ሆኖ ከለውጡ ኢኮኖሚ፣ ኅብረተሰብና የቴክኖሎጂ ዕድገት ጋር መላመድ የሚችል ዜጋ እንዲሆን በሚያስችል ሁኔታ ነው። .እናም በትግበራ ዘዴው ይህ እንዲታይ ይፈለጋል::

በጥናቱ እንደተጠቆመው፤ በትምህርት ቤቶች ውስጥ ያለው ሥርዓተ ትምህርት እና የመማር ማስተማር ልምምዶች በትግበራው ወቅት ተማሪዎች ሌሎችን እንዲገነዘቡ፣ የጋራ እሴቶችን እንዲያሳድጉ፣ ብዝኃነትን እንዲያዳብሩ፣ የሰብአዊ መብቶች ግንዛቤ እንዲኖራቸው የሚያደርግ መሆን አለበት:: የተሳትፎ ክህሎትን እና ኃላፊነት የተሞላበት ተግባርን እንዲያዳብሩ ማድረግም ይጠበቅበታል።

## መሰራት አለባቸው የተባሉ ጥቆማዎች

የትምህርት ቤት አመራሮች፤ የክፍል መምህራንን እንዴት መደገፍ እንዳለባቸው በማሰልጠን ብቃታቸውን ማሳደግ አለባቸው:: ለዚህ ደግሞ የትምህርት ቤት አመራር ጥራትን ማሻሻል ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል:: ሌላው በጥናቱ የተነሳው ነገር በፍኖተ ካርታው አንዳንድ መምህራን አሁንም ያለ ምንም ስልጠና ንባብ በማስተማር ላይ ያሉ እና አብዛኛዎቹ ሰርተፍኬት የነበራቸው በመሆኑ የመምህራንን እውቀት ማሻሻል ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል የሚለው ነው።

መምህራን የተለያዩ የማስተማር እና የምዘና ዘዴዎችን ለምሳሌ፡- ማንበብን እንዴት ማስተማር እንዳለባቸው የተለያዩ ስልጠናዎችን መውሰድ አለባቸው:: የትምህርት ቁሳቁሶች (የመማሪያ መጽሀፍት፣ የመምህራን መመሪያ) እና የትምህርት ቤት ግብዓቶች (ቤተ-መጽሐፍት ወይም የንባብ ማዕዘኖች) ማሟላትም ትኩረት ሊሰጠው ይገባል:: ተግባራዊ የወላጅ-መምህር-ተማሪ-ማህበርን ማጠናከር፤ በትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ፤ ተማሪዎች እየተማሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ ፤ የትምህርት ሴክተሩን ቁርጠኝነት እና ተጠያቂነት ስርዓት መዘርጋት፤ የትምህርት መሪዎች እንደ ኮቪድ-19 ያሉ ድንገተኛ የትምህርት መቆራረጦችን እንዴት መቋቋም እንደሚችሉ ግንዛቤ መፍጠርና ለችግሩ መፍትሄ ሰጪ የሚሆኑበትን መንገድ ማሳየት፤ በየጊዜው የትምህርትና ጥራቱ ጉዳይ በምን ሁኔታ እየተጓዘ እንዳለ መገምገም እና ግብረመልሶችን መስጠት ዋነኛ ተግባራቱን ከሚያሳልጡ መካከል እንደሆኑ ጥናቱ ያስቀምጣል::

ሌላው በጥናቱ ቢሰራ ተብሎ የተጠቆመው ነገር በመምህራን ትምህርት ኮሌጆች ውስጥ የቋንቋ ትምህርት መምህራንን በትምህርት ቤት ማስተማር የሚለውም ነው:: ይህ ደግሞ አጀንዳ 2063ን ያሳካልም የሚል እምነት ተጥሎበታል:: ምክንያቱም በአጀንዳ 2063 የምንፈልጋትን አፍሪካ በቀጣዮቹ ሃምሳ ዓመታት ውስጥ ይሰጠናልና ነው:: ይህም አፍሪካን ያሳተፈ ዕድገትና ቀጣይነት ያለው ልማት ማረጋገጥ ነው:: ስለሆነም ለዚህ እቅድ መሳካት ሁሉም የበኩሉን ያበርክት በማለት ጽሑፋችንን ቋጨን::

# ወቅታዊ

# «የመከላከያ ሰራዊቱ የቆመው ለአገር ሉአላዊነት እና ለሕዝብ ሰላም ነው»

- ኮሎኔል ሙላት ደሳለኝ
በመከላከያ ሚኒስቴር ጥናትና ምርምር ማዕከል የወታደራዊ ንድፈ ሐሳብ ጥናት ዳይሬክተር



ፎቶ - ሐዱሽ አብርሃ

አስቴር ኤልያስ

**ጥቅምት 15 ቀን የመከላከያ ሰራዊት ቀን በሚል በየአመቱ እየተከበረ ይገኛል። የዘንድሮ የሰራዊት ቀንም በዚሁ ዕለት €€ሕዝባችን የጥንካሬያችን ምንጭ‹‹ በሚል መሪ ሀሳብ ተከብሮ ውሏል። በዕለቱም የሕግ ማስከበር ዘመቻን የሚዳስሰው «የእሳት ቀለበት» የተሰኘ መጽሐፍ ተመርቋል። እኛም ከመጽሐፉ ዝግጅት ኮሚቴ ዋና አስተባባሪ እና በመከላከያ ሚኒስቴር ጥናትና ምርምር ማዕከል የወታደራዊ ንድፈ ሐሳብ ጥናት ዳይሬክተር ኮሎኔል ሙላት ደሳለኝ ጋር በመጽሐፉ ይዘት እና አሸባሪው ትህነግ በሰሜን እዝ ላይ ጥቅምት 24 ቀን 2013 ባደረሰው ጥቃት ዙሪያ ቃለምልልስ አድርገናል፤ መልካም ንባብ።**

**አዲስ ዘመን፡- የመከላከያ ሰራዊት ቀን መከበር ጥቅሙ ምንድን ነው?**

**ኮሎኔል ሙላት፡-** የመከላከያ ሰራዊት ቀን የሚከበረው ለምንድን ነው ከሚለው በፊት በጥቂቱ ታሪካዊ ዳራውን ልዳስስ። በዓለም ላይ በጣም በርካታ አገራት የሰራዊታቸውን በዓል የሚያከብሩ መሆናቸውን እናስተውላለን። በዓሉ ሲከበር የሚመረጠው ቀን በሦስት ፈርጅ ውስጥ የሚታይ ሲሆን፤ አገራቱ በዓሉን እንደየአገራቸው ሁኔታ የሚያከብሩት ይሆናል። አንደኛው የጦር ሰራዊት የመሰረቱበትን ቀን መነሻ አድርገው ያከብራሉ። ሁለተኛው ደግሞ ከቅኝ ገዥዎቻቸው የተላቀቁበትን ቀን የጦር ሰራዊት ብለው የሚያከብሩ በርካታ አገሮች አሉ። ሦስተኛው አገራት በአገራቸው በተለያየ መንገድ ያገኙአቸውን የድል ቀን ለምሳሌ ከተለያዩ አገራት ጋር ጦርነት አካሂደው ድል የተደረጉበትንም አሊያም ድል ያደረጉበትን እንደ የጦር ሰራዊት ቀን አድርገው ያከብሩታል።

እኛ የጦር ሰራዊት ቀንን ስንወስድ ነፃ የወጣንበት ብለን ማለት አንችልም፤ ምክንያም እኛ በቅኝ ግዛት አልተገዛንም። ነገር ግን በቅኝ ግዛት ላለመገዛት ያደረግነው ተጋድሎ አለ፤ ይህ ተጋድሎ ደግሞ በአድዋ አሸናፊነት ተደምድሟል። የአድዋን ጦርነት የሰራዊት ቀን ብሎ ማክበር አሁን ካለው የአድዋ ድል ቀን አከባበር አንጻር ሲታይ ታሪካዊ ይዘቱን ወረድ አድርጎ መመልከት ይሆናል። ምክንያቱም የአድዋ ድል የመላ የጥቁር ሕዝቦች ድል ነው። ይህ የአድዋ ድል የኢትዮጵያ ሰራዊት ብቻ ሳይሆን የመላ አፍሪካም ጭምር በመሆኑ የአድዋ ድል ቀንን የመከላከያ ሰራዊት ቀን አድርጎ ማክበሩ ለተጋድሎ የተዋደቁትን የኢትዮጵያውያንና የጥቁር ሕዝቦችን ድል ቀነስ አድርጎ ማየት ስለሚያስመስል በአድዋ ቀን ላይ የሰራዊት ቀንን ማክበር አልተፈለገም።

ከዚህ ባሻገር በርካታ የድል ቀኖች እንደ አርበኞች፣ ሰማዕታት፣ የካራማራ ጦርነትም ሆነ ሌሎች ቀኖች አሉን። ሁሉም ቀን በራሱ ድል የተያዘ ነው። እኛ የመረጥነው ለመጀመሪያ ጊዜ የጦር ሰራዊቱ እንደ ሰራዊት ተዋቅሮ በ1900 ዓ.ም የጦር ሚኒስቴር ተብሎ የተሰየመበትን ቀን እንደ አንድ መነሻ ይዘን የመከላከያ ሰራዊት ቀን ተብሎ እንዲሰየም መደረጉ ታሪካዊ ይዘቱን የሚያሳይ ነው።

በዚህ አካሄድ የካቲት 7 የመከላከያ ሰራዊት ቀን ተብሎ ለዘጠኝ ዓመታት ያህል እያከበርን እዚህ ደርሰናል። ይህም በጎ እርምጃ መሆኑን ብናውቅም ታሪካዊ ይዘቱ ላይ ግን አላመንበትም። በዚህ ቀንም አብዛኛው የቀድሞ ሰራዊቶች እምብዛም ደስተኞች አልነበሩም። እነርሱ ካራማራን ያህል ድል አስመዝግበው እዚህ ያደረሱን ሰራዊቶች የጦሩን ቀን አብረው ካላከበሩ ልዩነት ይፈጥራልና ሁሉንም የሚያስማማ ቀን መምጣት አለበት በሚል በርካታ ጥናት አካሄደን። ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ ሆነን ለመጀመሪያ ጊዜ ጥቅምት 15 ቀን እንዲሆን ስምምነት ላይ መድረስ ችለናል።

የመከላከያ ቀን መከበሩ አሁን በዘርፉ ላለነው ለእኛም ሆነ ለተተኪው ትውልድ ከፍተኛ ጥቅም አለው። ራሳችንን የምናይበት ቀን ከመሆኑም ሌላ በዓመት አንድ ቀን ለሰራዊቱ ቀን ተሰጥቶት መከበሩ ውስጡን ለማወቅም ስለሚረዳ ቅብብሎሹ ቀጣይነት እንዲኖረው ያስችላል። በብዙ አገሮች ይህ የተለመደ ተግባር ነው። ሰራዊቱ ከሕዝቡ ጋር ያለውን ፍቅር ይበልጥ የሚያስተሳስርበት ብሎም ትውልዱም መረጃ የሚያገኝበት ነው። በተጨማሪም ወታደራዊ ገድሎች የሚተላለፉበትም ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በዚህ ዓመት የተከበረው የመከላከያ ሰራዊት ቀን መርህ ያደረገው €የጥንካሬያችን ምንጭ ሕዝባችን‹‹ የሚል ነው፤ ሰራዊቱና ሕዝቡ ያለው ትስስር ምን ይመስላል?**

**ኮሎኔል ሙላት፡-** ዘንድሮ በዓሉ የተከበረው በአገራችን በተፈጠረው ሁኔታ ተቀዛቅዞ ነው። ይሁንና የሕዝቡ አለኝታነት አልተቀዛቀዘም። መከላከያ ሰራዊት ከራሱ በፊት ቅድሚያ የሚሰጠው ለአገሩና ለሕዝብ ነው። ሰራዊቱ የሚቆመው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሰላም ወጥቶ በሰላም እንዲገባና የትኛውም ኃይል ሰላሙን እንዳያናጋበት ነው። የኃይላችን ምንጭ ሕዝባችን ነው ስንል ለእኛ የሚያደርገው እንክብካቤ በጣም ከፍተኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። እኛ ከሕዝቡ፤ ሕዝቡም ከእኛ ጋር ያለው ቁርኝት በጣም ከፍተኛ ነው። ሕዝቡም ይህን ይረዳል።

መከላከያ ሰራዊቱ በቆየባቸው የትኛዎቹም አካባቢዎች ለሕዝቡ ትምህርት ቤት፣ ንጹህ የመጠጥ ውሃ፣ ጤና ጣቢያና መሰል ልማቶች ላይ ተሳትፎው ከፍተኛ ነው። ትግራይ በነበርንበት ጊዜ እያንዳንዱ የጦር ክፍል በየራሱ ስም የክልሉ ቢሮ ከሠራው በላይ የሠራናቸው ሥራዎች በጣም ብዙ ናቸው። አሸባሪው ትህነግ አዲስ አበባ 30 ያህል ዓመት ተቀምጦ ምንም አላደረገለትም ማለት ይቻላል። ግንባር አካባቢ ያለው ሰራዊት ግን ከትግርኛ ተናጋሪው በላይ ገንዘብ እያዋጣ ለትግራይ ልማት ከፍተኛ ድርሻ ተጫውቷል። ይህንን እነርሱም የሚክዱት አይደለም። በጣም በርካታ ልማት ላለፉት ዓመታት ሠርተናል። በመሆኑም በተለይ ከትግራይ ሕዝብ ጋር ያለን ቁርኝት በዚህ ዓይነት በጎ ተግባር የሚገለጽ ነው። የመከላከያ ሰራዊቱ ሲያደርገው የነበረው በጎ ተግባር ትህነግ እንደ ሰብዓዊ ጋሻ የያዘውንም ሕዝብ ጭምር የታደገ ነው። ሰራዊቱ ከሕዝቡ ደብቆ ያስቀመጠውን እህል አውጥተን ያከፋፈልነው ለራሱ ለሕዝቡ ነው። እኛ የተቸገረን የመርዳት ተልዕኮ የለንም፤ ተልዕኳችን ሌላ መሆኑ የሚታወቅ ነው። ነገር ግን ከራሳችን ወጪ አውጥተን ያንን ሁሉ ትምህርት ቤት ስንሠራ ከዚህ በላይ በጎ ተግባር ያለ አይመስለኝም።

**አዲስ ዘመን፡- በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ለበርካታ ዓመታት የቆየው የሰሜን እዝ በቆይታው የአገር ዳር ድንበር ከማስጠበቅ ባልተናነሰ በነበረበት የትግራይ ክልል የተለያዩ የልማት ሥራዎችን ሲሠራም ነበር፤ ይሁንና ክህደት ተፈጸሞበት ከጀርባው የተወጋው በዚያው ክልል ውስጥ ነው፤ በዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

**ኮሎኔል ሙላት፡-** ይህን ክህደት ለታሪክ ሰንደነዋል። ከቀናት በፊትም ‹‹‹የእሳት ቀለበት›› በሚል ርዕስ እኔ ዋና አስተባባሪ የሆንኩበት መጽሐፍ ታትሞ ለአንባቢያን እንዲደርስ በመደረግ ላይ ነው። መጽሐፉም ሦስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን፣ የመጀመሪያው አሸባሪው ትህነግ ይህን ግፍ እንዲፈጽም የገፋፋው ምክንያት ምንድን ነው? ከሕዝብ ጋር የሚያጋጨውስ ስለምንድን ነው? የሚለውን ጉዳይ ከራሱ ከማኒፌስቶው ተነስተን ያዋቀርንበት ነው። በክፍል ሁለቱ ባለፉት 30 ያህል ዓመታት አሸባሪው ትህነግ እያደረገ ስለመጣው ጉዳይ አለፍ አለፍ ብለን ዳሰንበታል። በተለይ ከለውጡ ማግስት ጀምሮ በመላ አገሪቱ አስፋፍቶት የነበረው የጸጥታና የደህንነት ችግር መነሻው ምን እንደሆነና ከእሱ ጋር ምን ትስስር እንዳለው እንዲሁም ከማዕከላዊ መንግሥት አፈንግጦ ትግራይ ክልል ገብቶ ምሽግ እንደሠራ የሚዳስስ ክፍል ነው። ይህ ብቻ ሳይሆን ጥቅምት 24/2013 የክህደት ተግባሩን ሳይፈጽም በፊት ሰራዊቱን እንዴት ያሰቃየው እንደነበርም በመጽሐፉ ተካቷል። እኛ የብልጽግናም የትህነግም ወይም የሌላውም ፓርቲ አባል አይደለንም፤ ሕዝብ የመረጠውን መንግሥት እናገለግላለን። ሕገ

ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ

መንግሥታዊ ግዳጃችንን እንወጣለን።

አሸባሪው ትህነግ ከጥቅምት 24 እስከ ሕዳር ሁለት ድረስ ያለውን ስንመለከት ሰራዊቱን ከመውጋት ባሻገር ሰራዊቱ የእኔ ነው ብሎ እስከማወጅ የደረሰበት ጊዜ ነበር። ትህነግ ያወደመውን የመሠረተ ልማት ለመጠገን እና ለሌላም እንዲውል መንግሥት ከመቶ ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ ማድረጉም የሚታወስ ነው። ይህም ለታሪክ መቀመጥ ስለላለበት በመጽሐፉ ያካተትነው እውነት ነው።

ክፍል ሦስቱ አጠቃላይ ከጥቅምት 24 በኋላ ሰራዊቱ ወደተለያዩ አካባቢዎች እንዲወጣ ከተደረገ በኋላ ራሱን አደራጅቶ እንዴት ኦፐሬሽኑን እንደፈጸመው እንዲሁም በ17 ቀን ውስጥ ዝርዝር የውጊያ አፈጻጸሙ ምን እንደሚመስል የተካተተበት ነው። ‹የምሥራቅ አፍሪካ ልዕለ ኃይል እኔ ነኝ› ያለውን ጦር እንዴት አሽመድምደን እንደጣልነው በሚያሳይ መንገድ ተጽፏል። ሕዝቡ ደግሞ ከዚህ መጽሐፍ እውነታውን ይማራል ብዬ አስባለሁ። መጽሐፉ ወደ 360 ገጽ ያለው ሲሆን፣ 450 ብር የሚሸጥ ነው፤ ከሽያጩም የሚገኘው ገቢ በጦርነቱ ለተጎዱ ወገኖች የሚውል ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- ጥቅምት 24/2013 ሰሜን እዝ ላይ በአሸባሪው ትህነግ የደረሰውን ክህደት በመጽሐፍ ለአንባቢያን ከማድረስ በተጨማሪ በፊልም ለማዘጋጀት ሐሳቡ ይኖራችሁ ይሆን?**

**ኮሎኔል ሙላት፡-** አዎ! ታስቧል። በጋራም ተነጋግረንበታል። እንዲያውም በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲሠራም ፈልገን ነበር፤ ነገር ግን የፊልም አዘጋጆቹ በትንሹ እስከ ሦስት ወር ድረስ እንደሚጠይቅ ነግረውናል። እንዲያም ሆኖ ወታደራዊ ገድሉ ቶሎ መጻፉ እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህም በላይ በርካታ መጽሐፍ ሊወጣው የሚችል ታሪክ መሆኑ ታምኖበታል። ስለዚህ ፊልም ሠሪዎች ቢሠሩበት ያዋጣል፤ እኛም እንሠራለን ብለን እናስባለን።

**አዲስ ዘመን፡- አሸባሪው ትህነግ የሰሜን እዝን አድብቶ ሲያጠቃው ሁሉ በእጁ ሆኖ የሚዘልቅ መስሎ ተሰምቶት እንደነበር ይታወሳል፤ ሌሳ ሊመክተው የሚችል ኃይልም ቶሎ አይደርስም ብሎ ቢያስብም በቅጽበት ሌላው የሰራዊቱ ቡድን መድረስ ችሏልና ይህ አፋጣኝ እርምጃ እንዴት ነበር የተቀናጀው?**

**ኮሎኔል ሙላት፡-** ሰራዊታችን የነበረው በሰሜኑ የአገራችን ክፍል ብቻ አይደለም፤ ሰሜን ሆኖ በሁመራና በሰመራ ከዚህ በተጨማሪ በምሥራቁም ሆነ በምዕራቡ እንዲሁም በደቡቡም ሆነ በመሃል የአገሪቱ ክፍል ነበር። 80 በመቶው የጦር መሣሪያው ትግራይ ውስጥ ቢሆንም ሌላው ክፍል ያለው ግን ወዲያው መድረስ ችሏል፤ ትህነግ በትግራይ ያለው ሰራዊት እንኳ አስፈላጊውን ስልጠና እንዳይወስድ በሰበብ በአስባቡ ሲያስተጓጉለው ቆይቷል።

አንድ ሰራዊት በየጊዜው ስልጠና መውሰድ አለበት። ምክንያቱም ሊያጋጥመው ለሚችለው ችግር ውጤታማ አፈጻጸም ለማንሳት ይረዳዋልና ነው። ነገር ግን ሰራዊቱ እንዳይሰለጥን ትህነግ በየአካባቢው በሚፈጥራቸው የእርሱ ችግሮች የቤት ሥራ ስለሚሰጥ ሰራዊቱ የሚጣጣረው ያንን እሳት ለማጥፋት ነበር። እንዲያም ሆኖ ምንም እንኳን በየቦታው ያለውን ችግር ለመፍታት ቢበታተንም ሰሜን እዝ ተነካ ሲባል ግን በሚያስገርም ሁኔታ ምናልባትም በመደበኛው ጊዜ ጦሩን በሁለትና በሦስት ሳምንት ውስጥ ትግራይ ማድረስ በማይችልበት ሁኔታ በሁለትና በሦስት ቀናት ውስጥ በየቦታው ከነበረው ሰራዊት መካከል በአፋጣኝ ትግራይ መድረስ ችሏል።

አሸባሪው ትህነግ በየቦታው በታትኖት የሰላምና የደህንነት ችግሮች ባሉበት ቦታ እንዲራወጥ ያደረገውን ኃይል በሁለትና ሦስት ቀናት ውስጥ ወደትግራይ ማስገባት ተችሏል። አፈናው ያላጋጠማቸው የሰራዊቱ ክፍል እየተዋጉ ወደ ኤርትራ እንዲወጡና እዛም ተደራጅተው ማጥቃት እንዲፈጽሙ ተደርጓል።

**አዲስ ዘመን፡- ከአገር ውጪም ሆነ በአገር ውስጥ በሰላም ማስከበሩ በኩል የአገር መከላከያ ሰራዊት ያለው ስነምግባርና ጥንካሬ እንዴት ይገለጻል?**

**ኮሎኔል ሙላት፡-** መከላከያ ሰራዊት የራሱ የሆነ ዲሲፕሊን አለው፤ ይህ ዲሲፕሊን ደግሞ አሁን በለውጡ የመጣ አይደለም። መከላከያ ሰራዊት የራሱ የሆኑ ሕጎችና መመሪያዎች አሉት። በእርግጥ አሁን አሁን ከአንዳንድ የፖለቲካ ጽንፎች አላቀን አዳዲስ ሕጎች እያስተካከልን ነው። ሰራዊቱም እንዲጠቀም እየተደረገ ያለ ሒደት አለ።

መከላከያ ሰራዊት መሠረቱ ሕዝብ ነው። የመጣውም ከሕዝብ ነው። በሒደት ግን ትህነግ ራሱን ወደገዥ መደብ እየቀየረ ከሕዝብ ጋር እስከመጋጨት አድርሶታል። ከሕዝብ ጋር ሲጋጭ ደግሞ የደህንነት ጥያቄ የግድ ስለሚነሳ ይህን የደህንነት ሥራ ለመሥራት ሰራዊቱ ራሱ ከሕዝቡ ጋር የሚጋጭበት ጊዜ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው። ስለዚህ የፖለቲካ ፓርቲዎች በሚፈጥሩት ችግር ሰራዊቱ እየሄደ ከሕዝብ ጋር መጋጨት የለበትም የሚል ጥያቄ ሲነሳም ቆይቷል። ይህ በእንዲህ እያለ ሰራዊት የትኛውም የአገሪቱ ክፍል በመሄድ የተሰጠውን ግዳጅ ይፈጽማል። ግዳጅ የሚፈጽምበትም የራሱ የሆነ ዲስፕሊን አለው። ብዙ በጎ ነገሮችንም ያካተተ ነው።

እንደሚታወቀው ሕገ መንግሥቱ የደነገገው መከላከያው ከፖለቲካ ተጽዕኖ ነፃ መሆኑን ነው። ይህ በፊትም ያለ ፣ ወደፊትም የሚቀጥል ነው። ይሁንና መከላከያው በሒደት የፖለቲካ ፓርቲ አገልጋይ ሆኖ ነበር። በተለምዶ ‹ቀዩ መጽሐፍ› እየተባለ የሚጠራው የኢህአዴግ ልሳን የሆነው መጽሐፍ ‹ሰራዊቱ የመጨረሻ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ምሽግ ነው› የሚል ነበር። በዚህ አገር ውስጥ በጣም በርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎች አሉ። ሁሉም ደግሞ የየራሳቸው ተልዕኮና መርሃ ግብር አላቸው። ያንን መርሃ ግብር መከላከያ ሰራዊት ላይ መለጠፍ የለባቸውም የሚል ተቃውሞ በወቅቱ ይነሳ ነበር።

የትኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በሕዝብ ተመርጦ አሸንፎ እስከመጣ ድረስ መቀመጥ ያለበት ሊገለገልበት የሚያስችል ስትራቴጂ ነው። ትናንት ኢህአዴግ ከመንበሩ ሲወርድ ሌላው መጥቶ ደግሞ መከላከያው ላይ ሌላ ስትራቴጂ ሊቀጥልለት አይገባም። ይልቁኑ መሆን የሚገባው ቴክኖሎጂ የሚጠቀምና የዘመነ ሰራዊት በማድረግ ከትኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ነፃ የሆነ ሰራዊት መሆን ነው የሚል ጥያቄ ይነሳ ስለነበር ካለፉት ሦስት ዓመታት ወዲህ በጣም በርካታ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ሕጎች እንዲሁም የስልጠና ማንዋሎች ተቀይረዋል። የስልጠና ማኑዋሎቹ ምንም ዓይነት የፖለቲካ ይዘት ሳይኖራቸው ወታደራዊ የሆኑ ናቸው። በዚህ አካሄድ የትኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አሸንፎ ቢመጣ ተቀብሎ የሚሄድ የሚያስችለው ነው። ስለዚህ የምንመራባቸው ሰነዶች ማንም ቢመጣም በሕዝብ ተመርጦ አሸንፎ እስከመጣ ድረስ መቀበል የሚያስችል ነው። የመከላከያ ሰራዊቱ የቆመው ለአገር ሉአላዊነት እና ለሕዝብ ሰላም ነው።



> **የመከላከያ ሰራዊቱ ሲያደርገው የነበረው በጎ ተግባር ትህነግ እንደ ሰብዓዊ ጋሻ የያዘውንም ሕዝብ ጭምር የታደገ ነው።**

**አዲስ ዘመን፡- አሸባሪው ትህነግ የነበረው አቋምና በአሁኑ ወቅት ያለበት ሁኔታ ምን ይመስላል? የጭካኔ እጁስ የሚበረታው በማን ላይ ነው ይላሉ?**

**ኮሎኔል ሙላት፡-** የሀገር መከላከያ ሰራዊት ሦስተኛውን ዙር ጥቃት ከከፈተ በኋላ ባደረግነው መከላከል የሽብር ቡድኑ የትም መድረስ እንደማይችል አሳይተናል። ይህ በወታደራዊ እይታ ትርጉም ያለው ነው። እኛ ብቻ ነን ወታደራዊ ስልት አዋቂዎች ሲሉ የነበሩ ጉምቱ የአሸባሪው ትህነግ ወታደራዊ አመራሮች የትም እንደማይደርሱ እና እኛም በጣም የሰለጠነ ሰራዊት እንዳለን የተስተዋለበት ነው።

እነርሱ ለ50 ዓመታት ሕዝብን ሲያጋድሉ ቆይተዋል። ከዚህም የተነሳ ሽማግሌዎቹ ሳይሞቱ እዚህ ደርሰዋል። አዛውንቶቹ ያላቸው ትምክህት በጣም ጣራ የነካ በመሆኑ አመለካከታቸው ሁሉ ዘመኑን የሚዋጅ አይደለም። ትውልዱ እንዴት እንደተገነባና እንዴት ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም እያሽመደመዳቸው እንዳለ አሁን አሁን አሳምረው አውቀውታል።

ስለዚህ እነርሱ እንደሚሉት ‹የጦር ጠበብቶቹ› ሕዝብ በማስጨረስ ታይተዋል። ሃያ ሰው አሰልፈው የሚያስይዙት ሁለት ክላሽ ነው። ቀሪውን የጥይት ማብረጃ እያደረጉት ነው። ሲመለስ ጠብቀው ራሳቸው ይመቱታል። ድል መንሳት የፈለጉት ገበሬውን፣ ሽማግሌውን፤ ቄሱንም ሆነ ሼሁን እያሰለፉና ሕፃናቱን የጥይት ማብረጃ እያደረጉ በማዕበል ነው። ይሁንና አሳዛኙ ነገር አለመሳካቱ ነው። ሌላው ቀርቶ ትህንግ ወታደሩን ሀሺሽ (ድራግ) እያስወሰደው እንዲዋጋ ሲያስደርገው ነበር።

በየጦርነቱ ከመጀመሪያ ጀምሮ ከአንድ ቤተሰብ አንድ ሰው ተባለ፤ በአሁኑ በሦስተኛው ዙር ያዘዘው ደግሞ ሕይወት ያለው ሰው ሁሉ ተንቀሳቅሶ እንዲዋጋ ነበር። በዚህም በብዙ የሚቆጠር ወጣት የት እንዳለ የሚያውቀው ትህነግ ብቻ ነው።

አሸባሪው ትህነግ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ከፈጸመው ግፍ ይልቅ በትግራይ ሕዝብ ላይ የሰራው ደባ ይበልጣል። በእርግጠኝነት መናገር የምችለው ነገር ቢኖር የትግራይ ሕዝብ ነፃ ወጥቶ፣ በክልልም የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ገብተው ሕዝቡ እንዲናገር ቢደረግ ላለፉት 40 እና 50 ዓመታት ትህነግ የትግራይ ሕዝብ ላይ ያደረሰው መከራ ቀሪው የኢትዮጵያ ክፍል ላይ ካደረሰው አይተናነስም። ድርጅቱ ለትግራይ ሕዝብም የሚሆን አይደለም። ትህንግ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረት (ኢዲህን) አጥፍቶ ነው ለስልጣን የበቃው።

ሌላው ቀርቶ የቅርቡን መጥቀስ ቢቻል መከላከያ መቀሌን ለቆ ሲወጣ ወደ 50 አካባቢ የሚጠጉ በጊዜያዊ አስተዳደር ውስጥ የነበሩትን የገዛ ወገኖቹን የገደለ ድርጅት ነው። ድርጅቱ ለገዛ ወገኑ እንኳ የማይመለስ ነው። ከራሱ ፍላጎት ውጪ የሌላውን ፍላጎት በፍጹም የማያከብር ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት እስካሁን የመጣበት ውጣ ውረድ እንደልምድ ሲያገለግለው ይችላል?**

**ኮሎኔል ሙላት፡-** ሰራዊታችን በጣም በርካታ ነገሮችን እያሳለፈ ነው። ጦርነት ጥሩ ነው ብሎ መናገር ትክክል ላይሆን ይችላል፤ ነገር ግን ጦርነት ከተካሄደ በኋላ የሚገኘው ልምድ ግን ቀላል አይሆንም።

በዓለም አቀፍ ደረጃ የዘርፉ መድረክ ላይ ኢትዮጵያዊ ሲገኝ ለእኛ ያላቸው ከበሬታ በእጅጉ የተለየ ነው። በአፍሪካ ቀንድ ውስጥ ያለን እንደመሆናችን በርካታ ውጣ ውረዶች አሉ። ይህ ሁሉ ለሰራዊታችን ጥንካሬ ከፍ ያለ ነው። ስለሆነም ይህ ሰራዊት አግባብነት ያለው ከበሬታ የሚገባው ነው። መንግሥትም ለዚህ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ ትልልቅ ኮሌጆችን እያቋቋመ ነው። ጦሩም የተሰጠውን ግዳጅ ለመወጣት ወደኋላ የሚል አይደለም። የጥንካሬያችን ምንጭ ደግሞ ሕዝብ ነው።

በዚህ አጋጣሚ ማስተላለፍ የምፈልገው መልዕክት አለ። ይኸውም ወጣቱ ሰራዊቱን መቀላቀል አለበት፤ አገር የጋራ ነው የሚል ነው። የትውልድ ቅብብሎሽ ደግሞ መኖር አለበት። ዓለም የደረሰበትን የቴክኖሎጂ ውጤት የሚያገኝበት ግንባር ቀደሙ ተቋም መከላከያ ነውና ወጣቱ ሊቀላቀል ይገባል ባይ ነኝ፤ እኛም የምናወርሰው ለተተኪ ትውልድ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ማብራሪያ ከልብ አመሰግናለሁ።**

**ኮሎኔል ሙላት፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ዓለም አቀፍ

## አሜሪካ በጓንታናሞ ቤይ ለሁለት አስርት ዓመታት ያቆየችውን አንጋፋ እስረኛን ፈታች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አሜሪካ በጓንታናሞ ቤይ ለሁለት አስርት ዓመታት ያቆየችውን አዛውንቱን እስረኛ ፈታች። የፓኪስታን ዜግነት ያላቸው የ75 አመቱ ሳይፉላህ ፓራቻ ጥቅምት 19 ቀን 2015 ዓ.ም ወደ አገራቸው ተልከዋል።

በአውሮፓውያኑ 2001 በአሜሪካ ላይ ከደረሰው ጥቃት ከሁለት ዓመት በኋላ የታሰሩት ግለሰቡ ለመታሰራቸው ሰበብ የነበረው የአልቃይዳ ደጋፊ የሚል ነው። ሳይፉላህ የአልቃይዳን ታጣቂዎች በገንዘብ በመደገፍ የተጠረጠሩ ሲሆን፤ በእስር የቆዩት ክስም ሳይመሰረትባቸው ነው።

ሳይፉላህ ለአመታትም ንጹህ ነኝ ሲሉም ቆይተዋል። በአሜሪካ የደረሰውን ጥቃት ተከትሎ በኩባ የሚገኘው የአሜሪካ ወታደራዊ እስር ቤት በመቶዎች የሚቆጠሩ ተጠርጣሪዎች የታጎሩበት ነበር።

«በጓንታናሞ ቤይ ታስሮ የነበረው ፓኪስታናዊው ሳይፉላህ ፓራቻ ከእስር ተፈትቶ ቅዳሜ ጥቅምት 19 ቀን 2015 ዓ.ም ፓኪስታን ገብቷል» ሲል የፓኪስታን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተናግሯል።

መግለጫው አክሎም «በውጭ አገር ታስሮ የነበረ የፓኪስታን ዜጋ በመጨረሻም ከቤተሰቡ ጋር በመገናኘቱ ደስ ብሎናል» ብሏል። የሳይፉላህ ጠበቃ ክላይቭ ስታፎርድ-ስሚዝ ደንበኛቸው ለመፈታት ይህን ያህል አመታት የወሰደበትን ምክንያት ጠይቀዋል።

«ከአንድ ዓመት በፊት ነው እንዲለቀቅ የተወሰነው። እናም በዚህ ወቅት ተስፋ በመቁረጥ የኢግልስን ሆቴል ካሊፎርኒያ ይዘፍልንኝ ነበር። የዘፈኑ ግጥም መሳብኘት የምትችለው ነገር ግን መውጣት የማይቻልበትን ሁኔታ የሚያስረዳ ነው» በማለት ክላይቭ ለቢቢሲ ኒውስሃወር ፕሮግራም መናገራቸውን ዘገባው አመልክቷል።

ሳይፉላህ በቁጥጥር ስር የዋሉት የአሜሪካው የፌደራል ምርመራ ቢሮ በታይላንድ ውስጥ ባደረገው ዘመቻ ነው።

በአሜሪካ የተማሩት ሳይፉላህ ከአልቃይዳ መሪ ኦሳማ ቢን ላደን እና ካሊድ ሼክ መሀመድን ጨምሮ ከአንዳንድ ከፍተኛ ባለስልጣናት ጋር ግንኙነት አላቸው የሚል ክስ ከአሜሪካ ቀርቦባቸዋል።

መጀመሪያም በአፍጋኒስታን ባግራም በሚገኘው የአሜሪካ ወታደራዊ እስር ቤት ከ14 ወራት ቆይታ በኋላ ወደ ጓንታናሞ ቤይ እንዲዛወሩ ተደርጓል።

ምስጢራዊው የአሜሪካ ወታደራዊ እስር ቤት አሜሪካ ከሽብር ጋር በምታደርገው ውጊያ ተጠርጣሪ የሆኑ ሰዎችን ለማጎርና ለማሰቃየት የምትጠቀምበት ነው።

የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ክስ ያልቀረበባቸው እስረኞችን እንዲፈቱ እንዲሁም ከአልቃይዳ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አላቸው ተብለው የተከሰሱ ሰዎች የፍርድ ሂደቱን እንዲያሳልጡም ጥያቄዎች እየበረቱባቸው ነው።

---

**ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር**
**በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም**

## ትኩረት የተሰጠው የምርምር ጆርናሎችን ዓለም አቀፍ እውቅና የማስገኘት ስራ

**እየሩስ ተስፋዬ**

በሀገራችን የተለያዩ ምርምሮች ይሠሩ እንጂ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያገኙ የምርምር ጆርናሎች ቁጥራቸው አነስተኛ ወይም በጣት የሚቆጠሩ ናቸው ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ለዚህም እንደ ችግር ከሚጠቀሱት ምክንያቶች ውስጥ የአሠራር ሥርዓት ያለመኖር እና የጥራት ጉዳይ በዋነኝነት ይጠቀሳሉ፡፡

በከፍተኛ ትምህርትና ምርምር ተቋማት እና በሙያ ማህበራት ለሚዘጋጁ የምርምር ጆርናሎች ግምገማና እውቅና ሥርዓት በማበጀት የምርምር ጆርናሎችን ተቀባይነት፣ ጥራት እና እይታን ማሳደግ እንደሚገባም ከዚህ ቀደም ትምህርት ሚኒስቴር በብሄራዊ ምርምር ጆርናሎች ግምገማና እውቅና አሰጣጥ ሥርዓት ፣ ወቅታዊ ሁኔታና ተስፋዎቻቸው ዙሪያ አውደ ጥናት ማካሄዱ ይታወሳል፡፡

የከፍተኛ ትምህርት ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ሳሙኤል ክፍሌ፤ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ በምርምር ተቋማት እና በሙያ ማህበራት የሚሰሩ ምርምሮችን እና የጥናት ህትመቶችን ለዓለም ተደራሽ በማድረግ ቅቡልነታቸውን ማሳደግ እንደሚገባ የገለጹ ሲሆን፤ በሀገሪቱ በተለያዩ ተቋማት ላይ በምርምር ሥራ የሚሳተፉ በርካታ ምሁራንና ተመራማሪዎች ቢኖሩም በዓለም አቀፍ ምርምር ጆርናሎች ላይ የሚደረገው አስተዋጽኦ ግን አነስተኛ መሆኑን ያነሳሉ።የሀገር ውስጥ የምርምር ጆርናሎች ጥራትና ደረጃቸውን ጠብቀው በሀገሪቱ በሚቋቋም የምርምር ጆርናሎች ድረ ገጽ እና መረጃ ቋት ውስጥ እንዲመዘገቡና ተደራሽ እንዲሆኑ እየተሰራ መሆኑንም በማከል ያስረዳሉ ፡፡

በትምህርት ሚኒስቴር የሳይንስና ምርምር ጉዳዮች ዳይሬክተር ጄነራል ዶክተር ሰለሞን ቢኖር እንዳሉት፤ የምርምር ጆርናሎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ትኩረት እንዲሰጣቸው እና እውቅና እንዲያገኙ ሁለት የህግ ማዕቀፎች ተዘጋጅተው ወደ ሥራ ከተገባም ቆየት ብሏል።አንደኛው የምርምር ሥራዎች እንዴት ይፈተሻሉ?



ዶክተር ሰለሞን ቢኖር

ማን ይፈትሻል?እንዴትስ እውቅና ይሠጣል? የሚል ጠቅለል ያለ ሃሳብ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ዝርዝር ጉዳዮችን የያዘ ነው። በተለይም የጆርናል አርታኢዎች ለሚንስቴር መስሪያቤቱ ሲያስገቡ ምን መስፈርት ነው መከተል ያለባቸው የሚለውን በግልፅ የሚያሳይ እና በዝርዝር የሚያሳይ ነው ፡፡

በሀገር ውስጥ የምርምር ጆርናሎች የግምገማ እና የእውቅና አሰጣጥ ሥርዓት ከተመጀመረ ሦስት ዓመትታን እንዳስቆጠሩ ያወሱት ዶክተር ሰለሞን፤ ያለውን ጠንካራ ጎን እና ተግዳሮቶችን እንዲሁም ለወደፊት የበለጠ መግባባት እንዲኖር ለማድረግ ለዚህም ደግሞ ትልቁን ሚና ከሚጫወቱት ከኢትዮጵያ አርታኢዎች ጋር ውይይት መደረጉንም ያነሳሉ፡፡በተጨማሪም የአሠራር ሥርዓቱን ከፍ ለማድረግም የኢትዮጵያ ኤዲተርስ ጆርናል ፎረም ለማቋቋም መታሰቡንም በማከል ይገልጻሉ፡፡

እንደ ዶክተር ሰለሞን ገለጻ፤ የሀገር ውስጥ የምርምር ጆርናሎች ግምገማ እና እውቅና አሠራር ሥርዓት ተሰጠ ማለት በዓለም አቀፍ ኢንዴክሲንግ ዳታ ቤዝ ገቡ ማለት አይደለም፡፡ነገር ግን በሀገር ውስጥ እየተሠራበት ያለው ሥርዓት ምርምሮቹ በሂደት በዓለም አቀፍ ደረጃ እይታቸው እና ተነባቢነታቸው እንዲጨምር የሚያርግ ነው።ትምህርት ሚኒስቴርም የሀገር ውስጥ የምርምር እውቅና አሠራር ሥርዓት የዘረጋው ግቡም ጥራታቸውን ለማሳደግ እና ሀገሪቱ ካላት የህዝብ እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ብዛት አንጻር መታየት ያለባቸው የሀገር ውስጥ የምርምር ጆርናሎች አነስተኛ በመሆናቸው ተነባቢነታቸው እንዲጨምር ማድረግን ያካተተ ነው፡፡

‹‹የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሦስት ተልዕኮ አላቸው እነርሱም መማር ማስተማር፣ ምርምር እና የማህበረሰብ አገልግሎት ወይም ጉድኝት ናቸው፡፡›› ያሉት ዶክተር ሰለሞን፤ ከዚህ አኳያ ተቋማቱ ምርምሮችን ሲያርጉ ከዐስር ዓመቱ እቅድ ጋር ተያይዞ መሠራት እንዳለባቸው አቅጣጫ የተሠጠበት ነው፡፡ከዚህ አንጻርም ብሔራዊ የምርምር እና የትኩረት መስክ በመለየት ለከፍተኛ ትምህርት እንዲሁም ለምርምር ማዕከላት ተሰራጭቷል።በተጨማሪም በምርምር ጆርናሎች ጉዳይ የሚታዩትን ችግሮች ለመፍታት እንደ ሀገር ብዙ መሠራት እና ከሌሎች ሚኒስቴር መሥሪያቶች ጋር በትብብር እንደሚሠራም ይገልጻሉ፡፡

ዶክተር ሠራዊት ሃንዲሶ በትምህርት ሚኒስቴር የምርምር እና ስርጸት ዴስክ ኃላፊ ናቸው።እርሳቸው እንደሚሉት፤ ከምርምር ጋር ተያይዞ ሁለት ችግሮች አሉ፡፡አንደኛው ችግር ለእውቀት እና ለሳይንስ የሚደረገው አስተዋጽኦ አናሳ መሆን ሲሆን ፤ ሁለተኛው ችግር ደግሞ የምርምር ምርታማነት ብቻ ሳይሆን እውቀትን በማስፋፋት፣በማስረጽ፣ እውቀትን ለማህበራዊ፣ ለቢዝነስ እና ሌሎችም ጉዳዮች ጥቅም ላይ እንዲውል ከማድረግ አኳያ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ መገኘት ነው።

ከምርምር ስርጸት ጋር ተያይዞ ዓለም አቀፍ የጥራት እና የእይታ ጉዳይ ወሣኝ ያሉት ዶክተር ሠራዊት፤ ምርምሮች ከዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና እንዲያገኙ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ነው።ትምህርት ሚነስቴርም ሥርዓት ዘርግቶ የምርምር ጆርናሎች በተለይም አካዳሚክ ጆርናሎች እውቅና የሚያገኙበት፣ የሚፈተሹበት፣ የሚሰርጹበት፣ ጥቅም ላይ የሚውሉበት አሠራር ዘርግቶ ምዘናው እንዴት ባለ መልኩ እውቅና እንደሚያገኙም ከሚመለከታቸው ጋር መምከሩንም ያወሳሉ፡፡

ዶክተር ሠራዊት እንደሚሉት፤ በሀገራችን በርካታ ምርምሮች ይሠራሉ፤ የሚሠሩት ችግር ፈቺ ምርምሮች ሼልፍ ላይ እንዲቀመጡ አይፈልግም ይልቁንም ማህበረሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረጉ ላይ የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ በመሆኑ ምርምሮቹ ከፍ ብለው እንዲወጡ ጥራት ላይ በሚገባ መሥራት ያስፈልጋል፡፡

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

ሰኞ

# አዲስ ዘመን ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

## የወጣቷ እንቁ ህልም- ከመም እስከ ማራቶን ክብረወሰኖች

**ብርሃን ፈይሳ**

በወጣትነታቸው በስኬት የታጀበ ታሪክ ካላቸው እንቁ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች መካከል አንዷ ናት። እሷ የምትሳተፍባቸው ውድድሮች ላይ የሚነገሰው አሸናፊ ትሆናለች የሚለው ሃሳብ ሳይሆን ሰዓት አሻሽላ የክብረወሰን ባለቤት ትሆናለች የሚለው ግምት ነው። ስክነት መገለጫዋ የሆነው ትሁቷ አትሌት ለተሰንበት ግደይ፤ በ24 ዓመቷ ሦስት የዓለም ክብረወሰኖችን እንዲሁም በርካታ ዓለም አቀፍ ክብሮችን በመቀዳጀት ደማቅ ታሪክ ጽፋለች።

በወጣቶች አገር አቋራጭ ውድድር የዓለም አቀፍ የውድድር መድረኮችን በስኬት የተቀላቀለችው ለተሰንበት፣ ለቁጥር የሚታክቱ ድሎችን በዓለም አቀፍ መድረኮች አጣጥማለች። በቶኪዮ ኦሊምፒክ የ10 ሺሜትር የነሐስ ሜዳሊያ ባለቤት ስትሆን፤ ከወራት በፊት በኦሪጎን በተካሄደው እንዲሁም በዶሃው የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ደግሞ በዚሁ ርቀት የወርቅና የብር ሜዳሊያዎችን አጥልቃለች። ከሁለት ዓመት በፊት በቫሌንሲያ በተካሄደ ውድድር በ5ሺ ሜትር የዓለም ክብረወሰንን ከ4ሰከንዶች በላይ በማሻሻል የግሏ ማድረግ ችላለች። ባለፈው ዓመት ደግሞ በሆላንዳዊቷ አትሌት የተሻሻለውን የ10ሺ ሜትር ክብረወሰን ከሁለት ቀናት በኋላ ሄንግሎ ላይ በመስበር ክብሩን በእጇ አስገብታለች። በዚያው ዓመት በቫሌንሲያ ግማሽ ማራቶን ተሳትፋም ሦስተኛውን የዓለም ክብረወሰን በማስመዝገብም የዓለምን ሕዝብ አጀብ አሰኝታለች።



አትሌት ለተሰንበት ግደይ በቫሌንሲያ ያስመዘገበችውን የግማሽ ማራቶን ክብረወሰን በማራቶንም ለመድገም ተዘጋጅታለች፤

በ5ሺ እና 10ሺ ሜትር ሩጫዎች የምትታወቀው ለተሰንበት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በግማሽ ማራቶን ውድድሮች ላይ ተካፍላ ስኬታማነቷን አረጋግጣለች። አሁን ደግሞ ጊዜው ወደ ረጅሙ የአትሌቲክስ ርቀት ማራቶን የምትሸጋገርበት መሆኑን አስታውቃለች። ማራቶንን አንድ ብላ የምትጀምርበት ውድድርም አምና የክብረወሰን ባለቤት በሆነችበት ቫሌንሲያ ሲሆን፤ በቀጣዩ ኅዳር ወር 2015ዓ.ም ይካሄዳል። ይህንን ተከትሎም የስፖርት ቤተሰቡ ምን አዲስ ነገር ታሳይ ይሆን በሚል ከወዲሁ በጉጉት እየተጠባበቀ ይገኛል።

በርካታ ስመጥር አትሌቶችን ያካተተው የኤንኤን የሩጫ ቡድን አባል የሆነችው ለተሰንበት በቡድኑ ድረገጽ የሩጫ ሕይወቷን በሚመለከት እንደሚከተለው ገልጻለች። ከመነሻዋ የጀመረችው ለተሰንበት ከእናቷ ተኬን በኩረጽዮን እና ግደይ ታደሰ በትግራይ እንዳመስቀል አካባቢ እንደተወለደች ትናገራለች። አራት እህቶችና ሁለት ወንድሞችም አሏት። ተማሪ ሳለች የአውሮፕላን አብራሪ አሊያም ዶክተር የመሆን ህልም ነበራት። በዚህ ምክንያትም በሩጫ የመሳተፍ ፍላጎት እንዳልነበራት ታስታውሳለች። ነገር ግን አንድ መምህሯ መሮጥ እንዳለባትና በዚህም ከራሷ አልፋ ቤተሰቦቿንም መርዳት እንደምትችል ይነግራት ነበር። ከእሷ ባለፈም ለቤተሰቦቿ ልጃቸው ጥሩ ሯጭ መሆን እንደምትችል ሊያሳምናቸው ጥረት ያደርግ ነበር። በዚህም ተሳክቶለት ከቤተሰብ ፈቃድ አግኝታ ሩጫን ጀመረች።

በትውልድ አካባቢዋ ያሉ ሴቶች በትዳር ለመኖር እንጂ ሩጫን የሚያስቡ አልነበሩም። ማህበረሰቡ እጅግ ወግ አጥባቂና ሃይማኖተኛ በመሆኑ የተነሳም ሴት ልጅ እንኳን ቁምጣ ለብሳ ልትሮጥ ቀርቶ በሱሪ መታየቷ በራሱ ነውር ነው። ይህ ሁኔታ አስቸጋሪ ቢሆንም የተለሰንበት አባት ግን ሩጫ ሥራዋ በመሆኑ አስፈላጊውን የስፖርት ትጥቅ እንድትለብስ ይነግሯት እንደነበር ጠንካራዋ አትሌት ታስታውሳለች። አይናፋሯ ለተሰንበት ከልምምድ በኋላ በሚኖራት የእረፍት ሰዓቷ እንዲሁም እሁድ እሁድ በሃይማኖት ስፍራዎች መገኘት እንደሚያስደስታት ትናገራለች።

በርካታ ስኬቶችን ስታጣጥም ከጀርባዋ በመሆን መንገድ የሚመራት አሰልጣኟ ኃይሌ ኢያሱ ይባላል። በ2006ዓ.ም በትራንስ የአትሌቲክስ ክለብ ውስጥ ነበር የተዋወቁት። አሰልጣኝ ኃይሌ ከለተሰንበት ጋር እንደተዋወቁ የጋራ እቅድ ማስቀመጣቸውን ይገልጻል። ይኸውም የዓለም ክብረወሰንን በ5ሺ ሜትር እና 10ሺ ሜትር እስከ ማራቶን የሚል ነበር። ይህንንም አብረው ለማሳካት ያስችላቸው ዘንድ በፊርማቸው ነበር ቃል የተገባቡት። ለዚህ ምክንያት የሆነው ደግሞ ከሌሎች አትሌቶች ይልቅ እሷ ተሰጥኦ ያላት አትሌት መሆኗን ስለተመለከተ ነበር። በዚህም መሠረት በተያዘው ዓመት ማራቶንን ለመሞከር መብቃታቸውንም ይገልጻል።

ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር
ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

## ብቁና በቂ የሰለጠነ የሰው ኃይል ለአስተማማኝ የሳይበር ደህንነት

**ይበል ካሳ**

«የተቀናጀ የሳይበር ደህንነት ለአገር ሉአላዊነት» በሚል መሪ ሃሳብ ከጥቅምት 1 እስከ ጥቅምት 30 ቀን 2015 ዓ.ም ሦስተኛው ሀገር አቀፍ የሳይበር ደህንነት ወር እየተከበረ ይገኛል። በመሪ ሃሳቡ ላይ እንደተቀመጠው የዘንድሮው ሀገር አቀፍ የሳይበር ደህንነት ወር በተለየ ሁኔታ ለሀገር ሉዓላዊነት ጉዳይ ልዩ ትኩረት የሰጠ ነው።

ዓቢይ አጀንዳ ሆኖ የተመረጠውን የሀገር ሉዓላዊነትን የማስጠበቅ ጉዳይ ማሳካት ይቻል ዘንድም አራት ዋና ዋና የትኩረት መስኮችንም በግብ ማስፈጸሚያነት አስቀምጦ በአራት ሳምንታት ተከፋፍለው በሚቀርቡ ልዩ ልዩ መርሃ ግብሮች የትግበራ ጊዜውን ጠብቆ እየተካሄደ ይገኛል። የትኩረት መስኮቹም ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊናን ማሻሻል፣ የተቋማት የሳይበር ጥቃት ተጋላጭነትን መቀነስ፣ በሳይበር ደህንነት ዘርፍ የሰው ሀብት ልማትን ማሻሻልና የግሉን ዘርፍ ለሳይበር ደህንነት መጠበቅ የሚኖረውን ሚና ማሳደግ የሚሉ ናቸው።

በዚህ አግባብ ወሩን ሙሉ እየተከበረ በሚገኘው የዘንድሮው ሀገር አቀፍ የሳይበር ደህንነት ወር በየሳምንቱ በተጠቀሱት የትኩረት መስኮች ላይ ኮንፍረንሶችና አውደ ርዕዮች በማዘጋጀትና የተለያዩ ጭብጦችን ማስተላለፍ በሚያስችሉ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫና የንቃተ ህሊና መፍጠሪያ መንገዶችን በመጠቀም መርሃ ግብሮቹ እየተተገበሩ ይገኛሉ። ከዚህ ጋር በተያያዘ በወሩ ውስጥ ሦስት ትልልቅ ኮንፍረንሶችን ለማካሄድ የታቀደ ሲሆን በተያዘላቸው ዕቅድ መሠረት ሁሉም የተካሄዱ ሲሆን የሦስተኛው ሳምንት ባለተራ የሰው ሀብት ልማትን የሚመለከተው የትኩረት መስክ ነበር።

በዚህም «የሳይበር ደህንነትን ለማስጠበቅ የሚያስችል የሰው ኃይል እንዴት ማልማት ይቻላል» በሚል ርዕስ ላይ የተዘጋጀ ኮንፍረንስ በስካይ ላይት ሆቴል ተካሂዷል። ከተለያዩ ተቋማት የተውጣጡ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች፣ የፋይናንስ ተቋማት፣ የግል ተቋማት፣ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ዓለም አቀፍ ተቋማት የኮንፍረንሱ ተሳታፊ በሆኑበት በዚህ ኮንፍረንስ ከፍተኛ የመንግሥት ባለስልጣናትና ከግሉ ዘርፍ የመጡ አካላት መልዕክት አስተላልፈውበታል። በርዕስ ጉዳዩ ላይ ያተኮረ ጥናታዊ ጽሑፍ በባለሙያ ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል።

በኮንፍረንሱ ላይ ተገኝተው መልዕክታቸውን ካስተላለፉት መካከል የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ዳንኤል ጉታ አንዱ ናቸው። በንግግራቸውም ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ መወዳደሪያ መድረክ እየሆነ የመጣውን የሳይበር ምህዳር ለመጠበቅና የሳይበር ደህንነትን ለማስጠበቅ በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል ቁልፍ ጉዳይ መሆኑን ተናግረዋል።

ይሁን እንጂ አሁን ላይ በዘርፉ የበቃና የሰለጠነ የሰው ኃይል ማግኘት ለየትኛውም ሀገር ቀላል አለመሆኑን ያመላከቱት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ «እንደ ኢትዮጵያ ላሉ በሳይበር ምህዳሩ ላይ ያላቸው ድርሻ በጀማሪነት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሀገራት ደግሞ ይበልጡን ከባድ ነው» ብለዋል። ይህም የሳይበር ተጋላጭነት በከፍተኛ ደረጃ እንዲጨምር እያደረገ በመሆኑ የሳይበር ደህንነትን በብቃት የመጠበቅና የሀገርን የሳይበር ሉዓላዊነት ሙሉበሙሉ የማረጋገጥ ሥራን ፈታኝ እንዲሆን አድርጎታል።

በመሆኑም በዘርፉ ከሚያስፈልገው የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት ጋር በተያያዘ ያለውን ችግር ለመቅረፍና ከጊዜ ወደጊዜ የመጣውን የሳይበር ስጋት፣ ተጋላጭነትና ጥቃት መቀነስ፣ ቀድሞ ማስጠንቀቅ መከላከልና ተገቢ ምላሽ መስጠት የሚያስችል የሳይበር አቅም ለመገንባት እንደ ሀገር ሰፊ ሥራ መሥራት ይገባል። ለዚህም የሳይበር ደህንነት በባህርይው በመደበኛው የትምህርት ሥርዓት ሊገኝ ከሚችለው በአሻገር ልዩ ተሰጥኦና ፍላጎት ያላቸውን ታዳጊዎችና ወጣቶችን ማግኘትና ማብቃትን የሚጠይቅ በመሆኑ ለዘርፉ የሚያስፈልገውን ብቁና በቂ የሰው ኃይል ለማሟላት ከታችኛው የትምህርት እርከን ጀምሮ መሥራት ያስፈልጋል።

ከዚህ አኳያ ዘርፉን በበላይነት የመምራት ኃላፊነት የተሰጠው የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር በሳይበር ደህንነት ላይ ልዩ ፍላጎትና ተሰጥኦ ያላቸውን ታዳጊዎችና ወጣቶች በመመልመልና የታለንት ማዕከል በማቋቋም በዘርፉ የሚያስፈልገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት ሰፋፊ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል። ይሁን እንጂ በአንድ ተቋም ብቻ የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት አይቻልም። በመሆኑም ሁሉም ባለድርሻ አካላት ለዘርፉ ትኩረት ሰጥተው መሥራት ይጠበቅባቸዋል።

በዚህ ረገድ በተለይም የትምህርት ተቋማት ከአንደኛ ደረጃ እስከ ከፍተኛ ትምህርት ድረስ የሳይበር ደህንነት ካሪኩለም በማዘጋጀትና ትውልድን በመቅረጽ በዘርፉ የሚፈለገውን የሰው ኃይል ልማት በብቃትና በስፋት ለማምረት ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው። ለዚህም ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ለመወጣት የትምህርት ተቋማት ለጉዳዩ ልዩ ትኩረት ሰጥተው መሥራት የሚጠበቅባቸው መሆኑንም ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ያመላክታሉ።

ከኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ቀጥሎ የሳይበር ደህንነትንና የሀገርን የሳይበር ሉዓላዊነት የሚያስጠብቁ ብቁ ባለሙያዎችን የማፍራት ከፍተኛ ኃለፊነት የተጣለበት ትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ሳሙኤል ክፍሌ(ዶ/ር) በበኩላቸው፤ «የሳይበር ደህንነትን ለማስጠበቅና ሀገራዊ ሉዓላዊነታችን ለማረጋገጥ ብቁ የሳይበር ደህንነት ባለሙያዎችን ማፍራት ቁልፍ ሀገራዊ አጀንዳችን ሊሆን ይገባል» ይላሉ።

ከዚህ አኳያ እንደ ሀገር ብቁ የሳይበር ባለሙያዎችን በበቂ ደረጃ ለማምረትና የሳይበር ሉዓላዊነትን በማስጠበቅ የሀገርን ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ የሳይበር የሰው ኃይል ልማትን ዋነኛ ማዕከል አድርጎ መሥራት እንደሚጠይቅም ያመላክታሉ።

በዚህ ረገድ ትምህርት ሚኒስቴር ያለበትን ኃላፊነት ለመወጣት በትኩረት እየሠራ መሆኑን የጠቆሙት ሚኒስትር ዴኤታው፤ «አዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ትኩረት ካገኙ ጉዳዮች መካከል አንዱና ዋነኛው ይህንኑ የአይ.ሲ.ቲና ተያያዥ የሳይበር ጉዳዮችን የሚመለከት ነው» ብለዋል። ለዚህም ከዚህ ቀደም በሁለተኛ ደረጃ ብቻ ሲሰጥ የነበረው የአይ.ሲ.ቲ ትምህርት በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ እንዲሰጥ በካሪኩለም ተቀርጾ መዘጋጀቱንና ከአዲሱ ዓመት ጀምሮ በሙከራ ደረጃ እየተተገበረ የሚገኝ መሆኑን ይገልጻሉ።